# የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን

# በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን የአካባቢ፣የሥራ ቦታ ጤንነትና ደህንነት አጠባበቅ ማኑዋል ቁጥር 022/2012

መጋቢት 2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# ማውጫ


መ ግ ቢ ያ ........ 1

ክፍል አንድ ........ 2

ጠቅላላ ድንጋጌዎች ........ 2

1. አጭር ርዕስ ........ 2

2. ትርጓሜ ........ 2

3. የማኑዋሉ የተፈፃሚነት ወሰን ........ 5

4. የማኑዋሉ ዓላማ ........ 5

5. የአከባቢ፣ የሙያ ጤንነትና ደህንነት አጠባበቅ ማኑዋል መርሆዎች ........ 5

ክፍል ሁለት ........ 6

የአካባቢ ስነ-ምህዳር ስለመጠበቅ ........ 6

6. የውኃ ደህንነት ስለመጠበቅ፣ ........ 6

7. አፈርና ደንን ስለመጠበቅ ........ 7

8. አየርን ከብክለት ስለመጠበቅ ........ 9

9. የመሬትን ገፅታ ስለመጠበቅ ........ 10

10. ሥነ- ምህዳርን ስለመጠበቅ ........ 10

ክፍል ሦስት ........ 11

የሙያ ጤንነትና ደህንነት ........ 11

11. የሥራ ላይ አደጋዎችንና የጤና ጠንቆችን ስለመከላከል ........ 11

12. የፕሮጀክት ሳይት እና መኖሪያ ወይም የካምኘ ቦታ መረጣ ........ 13

13. ለካምኘ የሚቀርብ ውኃ ........ 13

14. የመፀዳጃ ቤቶች ........ 14

15. የፍሳሽ እና ደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ዘዴ ........ 14

16. የልብስ፣ የእጅና የገላ መታጠቢያ አገልግሎቶች ........ 15

17. የምግብ ደህንነት፣አቀማመጥና አያያዝ ........ 15

18. የምግብ ማከማቻ ወይም ማቆያ ክፍል ........ 16

19. ስለ ህክምና አገልግሎቶች ........ 16

20. ስለጽዳት ሥራና ጽዳት ሠራተኞች ደህንነትና ጤንነትን ........ 17

21. የቢሮ ሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት ........ 17

ክፍል አራት ........ 19
በግንባታ ቦታ ስለሚከናወኑ ሥራዎችና ስለ ጥንቃቄዎች ........ 19
22. በሰው ኃይል ወይም በማሽነሪ የማፍረስ ሥራ ........ 19
23. ፈንጂዎችን በመጠቀም የማፍረስ ሥራ ........ 19
24. የቁፋሮ ሥራዎች ........ 20
25. የፎርም ዎርክ (Form work) ሥራዎች ........ 21
26. የስካፎልዲንግ (Scaffolding) ሥራዎች ........ 21
27. መውደቅን ስለመከላከል (Fall Protection) ........ 23
28. የመሰላል (Ladder) ሥራዎች ........ 23
29. የክሬን (Crane) ሥራዎች ........ 24
30. የዕቃ ማንሻ (Fork Lift) ........ 24
31. በብረታብረትና በእንጨት ውጤቶች፣ በኮንክሪትና በፒቪሲ ፊሬም ማምረቻ ማዕከሎች መደረግ ያለባቸው ጥንቃቄዎች ........ 25
32. የግንባታ ተሽከርካሪዎች እና ተንቀሳቃሽ የግንባታ ግብዓት ማቀነባበሪያ ሥራዎች ........ 25
33. በግንባታ ቦታ ላይ ያሉ የኤሌክትሪክ መስመሮች፣ በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሰሩ ማሽኖችና የግንባታ መሣሪያዎች ........ 26
34. በግንባታ ቦታ ላይ ያሉ የተቀጣጣይነት ባህሪ ያላቸው ፈሳሽ ነገሮች አጠቃቀምና አቀማመጥን በተመለከተ ........ 26
35. በውኃ አካባቢ የግንባታ ሥራዎች ........ 27
36. የግንባታ ቦታዎች አጠባበቅ ........ 27
37. በግንባታ ቦታ የእሳት አደጋ እንዳይከሰት የማድረግ ሥራ ........ 28
38. የዕቃ ማመላለሻ ሥራዎች ........ 28
39. የሰው ማመላለሻ ሥራዎች ........ 29
40. የጣራ ሥራዎች ........ 29
41. የኮንክሪት ማቀነባበሪያ (bulk mixing plant) ሥራዎች ........ 30
42. በግንባታ ግብዓት ማምረቻ ቦታዎች ላይ መደረግ ያለበት ጥንቃቄ ........ 30
43. የጋራዥ ሥራዎችና መደረግ ያለባቸው ጥንቃቄዎች ........ 31
44. ተሽከርካሪን ሰርቪስ ስለማድረግና ጥገና ስለማካሄድ ........ 31
45. ሞተር ክፍል ........ 31
46. የፍሬን ፍተሻ ........ 32
47. ፍሬንና ፍሪሲዮን ሰርቪስ ማድረግ ........ 32

48. ቦዲ መሙላትና ማስተካከል ........ 33
49. የመኪና ቦዲን በአይሶሲያኔት/Isocyanates ቀለም በመርጨት/spraying መቀባት ........ 34
50. የመኪና ቀለም መበጥበጥ ወይም ማዋሃድ ወይም ማቀላቀል እና አቀማመጥ ........ 34
51. መስታወት የመግጠም ሥራ ........ 35
52. ብየዳ ክፍል ........ 35
53. የሬዲዮ፣ ኮምፒዩተር እና የመሳሰሉት ብየዳ ስራ ጋር የተያያዙ የጤና እና የደህንነት ጉዳዮች........ 36
54. ጐማ ክፍል ........ 37
55. ባትሪ ክፍል ........ 37
56. ተንቀሳቃሽ የጥገና ሥራ /Mobile Maintenance/ ........ 38
57. የተሽከርካሪ ማጠቢያ ክፍል ........ 39
58. የጠጠር መፍጫ (Stone crushers) የሥራ ቦታ ........ 40
59. ከአስፋልት ስራ ጋር የተያያዙ የጤና እና የደህንነት ጉዳዮችን በሚመለከት ........ 40
60. ከፈንጅ (BLASTING) ሥራ ጋር የተያያዙ የጤና እና የደህንነት ጉዳዮች ........ 40
61. የፍንዳታ ቦታ ........ 41
62. የማፈንጃ አካባቢ ጥበቃ ........ 41
63. ከፍንዳታ ቦታ ሰራተኞችን ስለማሸሽ ........ 41
64. በፈንጅ ስራ ላይ ተግባራዊ መደረግ የሚገባቸው የደህንነት ጉዳዮች ........ 42
65. የፈንጅዎች ቆጠራና ጥበቃ ........ 43
66. በፍንዳታ ጊዜ ሊያጋጥም የሚችል አደጋንና ጉዳትን መከላከልና መቆጣጠር ........ 44
67. በድንጋይ ማምረቻ ካባዎችና በጠጠር ማምረቻ ወፍጮዎች አካባቢ ሊደረጉ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች ........ 44
68. ከኤሌክትሪክ ሥራ ጋር የተያያዙ የደህንነትና የጤና ጉዳዮች ........ 45
69. ከነዳጅ ማደያ ሥራ ጋር የተያያዙ የደህንነትና የጤና ጉዳዮች ........ 45
70. ከምሽት ፈረቃ ወይም ትርፍ ሰዓት ሥራ ጋር የተያያዙ የደህንነትና የጤና ጉዳዮች ........ 46
71. ከከፍታ ቦታ ላይ ከሚሰሩ ሥራዎች ጋር የተያያዙ የደህንነትና ጤና ጉዳዮች ........ 46
72. ከዕቃ ግምጃ ቤት ሥራ ጋር የተያያዙ የደህንነትና ጤና ጉዳዮች ........ 47
73. ድንገተኛ የእሳት አደጋን መከላከልና መቆጣጠር ........ 47
74. የእቃ ማከማቻ መጋዘን ቦታ አመራረጥና መደረግ ያለባቸው ጥንቃቄዎች ........ 48
75. በሰው አቅም የማይንቀሳቀሱ ትላልቅ ዕቃዎችን በተመለከተ ........ 48
76. ስለ የአርማታ ብረቶች ........ 48

77. ስለ ሲሚንቶ ........ 49
78. በአስፋልት ዝግጅት ወቅት ሊደረጉ ስለሚገባ የሚደረጉ ጥንቃቄዎች ........ 49
79. ስለ ነዳጅና ታንከር ........ 50
80. የነዳጅ ጋኖች የሚቀበሩበት ቦታና የአቀባበር ሁኔታ ........ 51
81. ስለ ዘይቶችና ቅባቶች ........ 52
82. ሞተር ግሬደር ላይ አደጋን ለመከላከል ሊወሰዱ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች ........ 52
83. ቡል ዶዘሮችና ትራክተሮች ላይ አደጋን ለመካላከል ሊወሰዱ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች ........ 53
84. ክሬንና ሾቭል ላይ አደጋን ለመከላከል ሊወሰዱ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች ........ 53
85. ከባድ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎችን ለማንቀሳቀስ መወሰድ ያለባቸው ጥንቃቄዎች ........ 55
86. የመንገድ ግንባታና ጥገና በሚከናወንባቸው የሥራ አከባቢዎች ሊደረግ የሚገባ ጥንቃቄ ........ 56
87. ጥገና በሚከናወንባቸው መንገዶች ላይ ሊወሰዱ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች ........ 57
ክፍል አምስት ........ 57
የባለ ድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት ........ 57
88. የኮርፖሬሽኑ ተግባርና ኃላፊነት ........ 57
89. የዘርፍ ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት ........ 58
90. የፕሮጀክቶች ተግባርና ኃላፊነት ........ 59
91. የአካባቢ፣ የሙያ ጤንነትና ደህንነት የሥራ ክፍል ተግባርና ኃላፊነት ........ 60
92. የሠራተኛ ማህበር ተግባርና ኃላፊነት ........ 61
93. የሥራ መሪና የሠራተኛው ተግባርና ኃላፊነት ........ 62
94. በየደረጃው የሚቋቋሙ የአካባቢ፣ የሙያ ጤንነትና ደህንነት ተከታታይ ኮሚቴ አወቃቀር፣ ተግባርና ኃላፊነት ........ 63
95. የክበብ ኃላፊዎች ተግባርና ኃላፊነት ........ 65
96. የክበብ ሠራተኞች ተግባርና ኃላፊነት ........ 66
97. የፕሮጀክት ባለቤት (Client) ተግባርና ኃላፊነት ........ 66
98. የንዑስ ተቋራጮች (Sub-Contractors) ተግባርና ኃላፊነት ........ 67
ክፍል ስድስት ........ 67
ስለ ሠራተኛና ንብረት ጉዳትና የጉዳት ሪፖርት ይዘት ........ 67
99. በሠራተኛ ላይ ስለደረሰ ጉዳት የሚቀርብ ሪፖርት ይዘት ........ 67
100. በተሽከርካሪ ላይ ስለደረሰ ጉዳት ........ 68
ክፍል ሰባት ........ 69
የዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ........ 69

101. ኤች አይ ቪ በደማቸው ውስጥ ያለባቸውና የኤድስ ህሙማን የሆኑ ሠራተኞች ................ 69
102. ስለ ሴት ሠራተኞች ደህንነትና ጤና ........................................ 70
103. ስለ ወጣቶችና አካል ጉዳተኛ ሠራተኞች ደህንነትና ጤና ........................ 71
ክፍል ስምንት ........................................................ 72
ማጠቃለያ ............................................................ 72
104. የክትትል፣የድጋፍና ግምገማ ሥርዓት ........................................ 72
105. የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ስርዓት ........................................ 73
106. ማኑዋሉን የመተግበር ኃላፊነት .............................................. 74
107. ማኑዋሉ የሚሻሻልበት ሁኔታ ............................................... 74
108. ማኑዋሉ ሥራ ላይ የሚውልበት ጊዜ ........................................ 74

## መ ግ ቢ ያ

የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 366/2008 እና የማሻሻያ ደንብ ቁጥር 390/2009 የተቋቋመ የልማት ድርጅት ሲሆን በተቋቋመለት ዓላማ መሰረት በሀገሪቱ ግዙፍ የተባሉ የተለያዩ የኮንስትራክሽን ሥራዎችን እያከናወነ የሚገኝ ተቋም ነው፡፡

ሀገሪቱ የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅን በተመለከተ ያወጣቻቸውን ሕጎችና ያፀደቀቻቸውን ስምምነቶች ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ እና በኮርፖሬሽኑ ሥራ አመራር ቦርድ የፀደቀውን የኮርፖሬሽኑን የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ ፖሊሲና ስትራቴጂን ማስፈፀም ስለሚገባና ፖሊሲና ስትራቴጂውን ሊያስፈፅሙ የሚችሉ አደረጃጀቶችንና አሰራሮችን መዘርጋት አስፈላጊ ነው፡፡

በመሆኑም ኮርፖሬሽኑ በሚያከናውናቸው የኮንስትራክሽን ሥራዎች ምክንያት በአካባቢ ላይ ሊደርሱ የሚችሉ አሉታዊ ተፅዕኖችን ለመቀነስ እና ቀስ በቀስም ሙሉ ለሙሉ ማስቀረት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፣ እንዲሁም ኮርፖሬሽኑ ቀጥሮ ለሚያሠራቸው ሠራተኞች ጤንነታቸውና ደህንነታቸው ተጠብቆ ጉዳት ሳይደርስባቸው ሥራቸውን መሥራት እንዲችሉ እና ከአደጋ ነፃ የሆነ ምቹ የሥራ አካባቢ በመፍጠር የሠራተኛው የሥራ ላይ ደህንነትና ጤንነት እንዲጠበቅ ለማድረግ የተለያዩ የመከላከያ ሥራዎችን ማከናወን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ይህ የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ ማኑዋል በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ተዘጋጅቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ ማኑዋል "**የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ ማኑዋል ቁጥር** 022/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ማኑዋል ውስጥ፡-

1. "**ኮርፖሬሽን**" ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 366/2008 እና 390/2009 መሠረት የተቋቋመው የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ነው፡፡
2. "**ሠራተኛ**" ማለት በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 2 (3) መሠረት ከኮርፖሬሽኑ ጋር በቅጥር ላይ የተመሠረተ የሥራ ግንኙነት ያለው ግለሰብ ነው፡፡
3. "**የሥራ መሪ**" ማለት በኮርፖሬሽኑ የሥራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 006/2009 አንቀጽ 2(8) ላይ የተተረጎመው ነው፡፡
4. "**አካባቢ**" ማለት ማንኛውም በዙሪያችን የሚገኝ በሰው፣ በእንስሳት እና በእፅዋት ህይወትና የዘወትር እንቅስቃሴ ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር የሚችል እና የእነዚህ የእርስ በእርስ መስተጋብር ድምር ውጤት ነው፡፡
5. "**ስነ-ምህዳር**" ማለት መሬትንና በመሬት ላይ ያሉትን ተፈጥሯዊ ይዘትና ግንኙነት የሚያሳይ ነው፡፡
6. "**የጤና አገልግሎት**" ማለት በሥራ ላይ ለሚደርስ አደጋ ወይም ሕመም እና ከሥራ ውጭ ለሚደርስ የተፈጥሮ ሕመም የሚሰጥ የሕክምና አገልግሎት ነው፡፡

7. **“የሥራ አካባቢ ደህንነት”** ማለት ከአደጋ ነጻ የሆነ ምቹ የሥራ አካባቢ መፍጠር ማለት ነው፡፡

8. **“የክበብ ሠራተኞች”** ማለት በሠራተኞች የመዝናኛ ክበብ ውስጥ የሚሰሩ ሠራተኞች ሲሆኑ ምግብ አዘጋጆችን እና አስተናጋጆችን ይጨምራል፡፡

9. **“የሥራ ቦታ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ”** ማለት በመከላከል መርህ ላይ የተመሰረተ የሥራ ቦታዎች ምቹ፣ ጤናማና ከአደጋ የተጠበቁ እንዲሆኑ ለማድረግ ጤናማ የሆነ አምራች የሰው ኃይል ለመፍጠርና የሥራ ውጤትንና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችል የተደራጀ፣ በስርዓት የሚመራና በቅንጅት የሚፈፀም የልማት እንቅስቃሴ ነው፡፡

10. **“የሥራ ላይ አደጋ”** ማለት ማንኛውም ሠራተኛ ሥራውን በማከናወን ላይ እያለ ወይም ከሥራው ጋር ግንኙነት ባለው ሁኔታ ከራሱ ውጭ በሆነ ምክንያት ወይም ሥራውን ለማከናወን በሚያደርገው ጥረት ምክንያት በአካሉ ወይም ማንኛውም የሰውነት ክፍል ተፈጥሮአዊ እንቅስቃሴ ላይ በድንገት የደረሰ ጉዳት ሲሆን በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 97 ስር የተመለከቱትን ያካትታል፡፡

11. **“በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ”** ማለት ሠራተኛው ከሚሰራው ሥራ ዓይነት ወይም ስራውን ከሚያከናውንበት የሥራ አካባቢ የተነሳ በሽታው ከተከሰተበት ዕለት አስቀድሞ በነበረ የተወሰነ ጊዜ ውስጥ በፊዚካል፣ ኬሚካል፣ ባዮሎጂካልና ኢርጎኖሚካል ነገሮች አማካኝነት በሰራተኞች ወይም ስራ መሪዎች ላይ የሚደርስ የጤና መታወክ ሆኖ ስራ በሚከናወንበት አካባቢ የሚዛመቱና የሚይዙ ነዋሪ ተላላፊ በሽታዎችን የማይጨምር እና የሰራተኛ እና ማህበራዊ ሚኒስቴር በስራ ላይ የሚመጡ በሽታዎችን አስመልክቶ በሚያወጣው ሰንጠረዥ መሰረት የሚወሰን ይሆናል፡፡

12. **“የአካል ጉዳት”** ማለት የመስራት ችሎታ መቀነስ ወይም ማጣትን በሚያስከትል ሁኔታ በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ነው፡፡

13. **“ምቹ ሥራ”** ማለት ምርታማ፣ በቂ ገቢ የሚያስገኝ፣ ከአደጋና የጤና ጉዳት የተጠበቀ፣ የማህበራዊ ዋስትና አገልግሎት እንዲሻሻል የሚያግዝ፣ አመለካከትን በነፃነት የመግለጽ መብትን የሚያከብር፣ ጥቅሞችንና ፍላጐቶችን በሚመለከት

በሚሰጡ ውሳኔዎች ላይ የተደራጀና የላቀ ተሳትፎን የሚፈቅድና ለሴቶችና ለወጣቶች እኩል ዕድልና ተሳትፎ የሚያጐናጽፍ ሥራ ነው፡፡

14. **"የሥራ ቦታ"** ማለት ማንኛውም ሠራተኛ በሥራ የሚገኝበት ወይም በሥራ ምክንያት የሚሄድበት እና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በኮርፖሬሽኑ ቁጥጥር ስር የሚገኝ ስፍራ ሲሆን ኮርፖሬሽኑ በመደበው መጓጓዣ ከመኖሪያ ቤት ወደ ሥራ ቦታ ወይም ከሥራ ቦታ ወደ ቤት የሚያጓጓዝበትንም ይጨምራል፡፡

15. **"ጠንቅ (Hazard)"** ማለት ማንኛውም በንክኪ፣ በትንፋሽ ወይም በሌሎች የመጋለጫ መንገዶች ሳቢያ የህመም ወይም የአካል ጉዳት የማድረስ ወይም የሥራ አካባቢን የመበከል ውጤት ያለው ንጥረ ነገር፣ ቁስ፣ መሳሪያ ወይም ስነ ህይወታዊ ተውሳክ ነው፡፡

16. **"ማህበራዊ ምክክር"** ማለት በመንግስት፣ በሠራተኞች እና በኮርፖሬሽኑ ተወካይ መካከል ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን የሚመለከቱ የጋራ ጉዳዮች ላይ የሚደረግ ማንኛውም ምክክር ወይም የመረጃ ልውውጥ ነው፡፡ ምክክሩ በኮርፖሬሽኑ እና በሠራተኛ ተወካዮች መካከል ሲካሄድ "የሁለትዮሽ ምክክር" ሲባል ምክክሩ መንግስትን የሚጨምር ሲሆን "የሶስትዮሽ ምክክር" ይባላል፡፡

17. **"መሣሪያ/ማሽነሪ"** ማለት ለኮንስትራክሽን ሥራ የግንባታ አገልግሎት የሚሰጡ ወይም የግንባታ ውጤቶችን ለማምረቻ የሚያገለግሉ ተንቀሳቃሽ ወይም የማይንቀሳቀሱ መሳሪያዎች ወይም ማሽነሪዎች ማለት ነው፡፡

18. **"ግብዓት"** ማለት ለኮንስትራክሽን ሥራ የሚውሉ በግዥ ወይም በማምረት የሚገኙ የፋብርካ ውጤቶች ወይም የተፈጥሮ ኃብቶች ማለት ነው፡፡

19. **"ንዑስ-ሥራ ተቋራጭ"** ማለት ከኮርፖሬሽኑ የግንባታ ሥራዎች ላይ የተወሰኑ የሥራ ዓይነቶችን ወይም ከጠቅላላ ሥራው ውስጥ ከፊሉን ሥራ እንዲያከናውን በኮርፖሬሽኑ ተመርጦ የሚመደብ ህጋዊ ሰውነት ያለው የመንግስት፣ የግል፣ የአገር ውስጥ ወይም የውጭ አገር የኮንስትራክሽን ድርጅት ማለት ነው፡፡

### 3. የማኑዋሉ የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ ማኑዋል ኮርፖሬሽኑ ሥራዎቹን በሚያከናውንባቸው የሥራ ቦታዎች በሙሉ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

### 4. የማኑዋሉ ዓላማ

ይህ ማኑዋል የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. በቅድመ መከላከል መርህ ላይ የተመሰረተ ተቋማዊ ቅድመ ዝግጅትና አዳዲስ የአሠራር ዘዴዎችን ሥራ ላይ ለማዋል እና የሥራ አካባቢዎችን ምቹ በማድረግ ከአደጋ እና ከጤና ጠንቆች የተጠበቁ እንዲሆኑ የሚያስችል የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ ባህልን በዘላቂነት መተግበር፣ ማሳደግና መጠበቅ አሰራር ስርዓት መዘርጋት፤
2. የመፈጸምና የማስፈፀም አቅምን በመገንባት፣ አሳታፊና ጠንካራ የምክክር እና የህግ አፈፃፀምን በማሳደግ አስተማማኝ የአካባቢና የሠራተኛ ጤንነት እና ደህንነትን ለማስፈን የሚያስችል አሰራር መዘርጋት፤
3. በሥራ ቦታዎች ለሚከሰቱ አደጋዎችና የጤና ጉዳቶች ተገቢ የሆኑ የቅድመ እና ድህረ የሠራተኛ፣ የሙያ ጤንነትና ደህንነት እና የመሣሪያዎችንና የተለያዩ ግብዓቶችን ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስችሉ ተግባራትን ማስፈጸም የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት፤

### 5. የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ ማኑዋል መርሆዎች

ይህ ማኑዋል የሚከተሉት መርሆዎች ይኖሩታል፤

1. የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ ሥራ አመራር ሥርዓት በሁሉም የሥራ ክፍሎች ተግባራዊ ማድረግ፡፡
2. ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመበትን ዓላማ መሠረት በማድረግ የኮርፖሬት ስትራቴጂዎችንና ዕቅዶችን ሲተገብር አመራሩ፣ ሠራተኛውና ባለድርሻ አካላት ለሥራ አካባቢ ደህንነት በግልና በጋራ የሚያደርጉትን አስተዋፅኦ የአመራር ቁርጠኝነት በመገምገም ክፍተቶችን ለመሙላት በዕውቀትና በስልጠና እንዲታገዝ ማድረግ፡፡
3. የደህንነት ምልክቶችን በተገቢው የሥራ ቦታዎች ሁሉ መለጠፍና ግንዛቤ በመስጠት ደህንነቱ የተጠበቀ ሠራተኛ እንዲኖር ማድረግ እና የአደጋ ስጋቶችን ለመቀነስ

በሚቻልባቸው የሥራ ቦታዎች ሁሉ የደህንነት መጠቀሚያ ቁሶችን በመጠቀም የሠራተኞችን ደህንነት መጠበቅ፤

4. ማንኛውም በሥራ ላይ የሚደርሱ አደጋዎች እንዳይከሰቱ ኮርፖሬሽኑ መከላከልን መሰረት ያደረገ ስራ መስራት እና ከሥራ ጋር ተያይዞ የሚመጣ አደጋን በመቀነስ የሰራተኞችን ምርታማነት ማሳደግ፣
5. በኮርፖሬሽኑ የሚገኝ እያንዳንዱ ሠራተኛ ተልዕኮውን ለመወጣት በሚያደርገው የሥራ እንቅስቃሴ ጤናው የተጠበቀ እንዲሆን በሽታን በመከላከልና አስተማማኝ የጤና አጠባበቅና የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታና የህክምና አገልግሎት በሥራ አካባቢው ላይ እንዲያገኝ ማስቻል፤
6. ሥራ ላይ የሚውሉ መሣሪያዎች፣ ተሽከርካሪዎችና ማምረቻ መሣሪያዎች ጉዳት እንዳያስከትሉ ደህንነታቸው የተረጋገጠ እንዲሆን ማድረግ እና አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ መሣሪያዎችን በመተካት የሠራተኞችን ደህንነት አስተማማኝ ማድረግ፣
7. በሥራው ሂደት የተፈጥሮ አካባቢ እንዳይራቆትና እንዳይበከል ተገቢውን እንክብካቤና ጥበቃ በማድረግ የተመጣጠነ የተፈጥሮ ኃብት አጠቃቀም እንዲኖር ማስቻል፡፡
8. የጤና፤ የሠራተኛ ደህንነትና የተፈጥሮ አካባቢ እንክብካቤ ጥበቃ ሥራዎች ኮርፖሬሽኑ በመደበኛነት ከሚተገብራቸው ዓላማዎቹ ጋር ጎን ለጎን ማከናወን፡፡

## ክፍል ሁለት
## የአካባቢ ስነ-ምህዳር ስለመጠበቅ

### 6. የውኃ ደህንነት ስለመጠበቅ፣

የውኃ ብክለትን ለመከላከል የሚከተሉት የጥንቃቄ እርምጃዎች ሊወሰዱ ይገባል፡-

1. የገፀ ምድር እና የከርሰ ምድር ውኃን በየትኛውም ቦታ በአግባቡ መጠቀም፣
2. ከፈሳሽ ቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች፣ ከማስረጊያዎች፣ ከፈሳሽ ማብላያ ስፍራዎች እና ከኮርፖሬሽኑ የተለያዩ አካላት የሚወጣውን ጤና የሚጐዳ ወይም ያልታከመ ፈሳሽ ቆሻሻ ወደ ውኃ አካላት አለመልቀቅ፣
3. በኮንስትራክሽን ሥራ ላይ በከፍተኛ መጠን በግብዓትነት የሚያገለግሉት አስፋልት፣ ነዳጅና ዘይቶች፣ ወዘተ…ጥቅም ላይ ሲውሉ የሚያደርሱትን ጉዳት ለመቀነስ በአግባቡ መጠቀም የእነዚህን ግብአቶች ተረፈ ምርቶች መልሶ መጠቀም ወይም አግባብነት ባለው መንገድ ማስወገድ፣

4. የአፈር መሸርሸርን የሚያባብሱ የግንባታ አሠራሮችን ማስወገድ፣
5. የግንባታ ስራው የሚያቋርጣቸውን ወንዞች ወይም የውኃ አካላት በተቻለ መጠን ቁጥሩን መቀነስ፣
6. በተቻለ መጠን ለመጠጥ፣ ለመዋኛ፣ ለመታጠቢያ፣ ለመዝናኛ፣ ለመስኖና ለተለያዩ አገልግሎቶች ይውሉ የነበሩ የተለያዩ አካባቢዎችን ወሳኝ የውኃ አካላት (Sensitive Water body) በጣም አስፈላጊ እስካልሆነ ድረስ ለማስወገድና ለመተካት አለመሞከር፣
7. በሚሠራው ወይም በተሠራው ግንባታ እና በውኃ አካላት መካከል ያለውን ክፍት ቦታ በተቻለ መጠን በሀገር በቀል እፅዋት እንዲሸፈን ማድረግ፣
8. ግንባታ ከመሠራቱ በፊት፣ በሚሰራበት ጊዜ እና ከተሰራ በኋላ የውኃ አካላትን ሁኔታ መከታተል እና ሥነ ምህዳሩ እንዳይበክል ማድረግ፣
9. የኮንስትራክሽን ግብአት ለማውጣት የተቆፈሩ ጉድጓዶች በዝናብ ውኃ ወይም በከርሰ ምድር ውኃ ምክንያት ከተሞሉ ሥራው እስከሚጠናቀቅ በአጥር ማጠናከርና ሥራው ከተጠናቀቀ በኋላ የአካባቢውን ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ጥቅም ላይ ማዋል ወይም የማያስፈልግ ከሆነ የመሬቱን ገፅታ እንደነበረው ማድረግ፣
10. ኮርፖሬሽኑ በየትኛውም ቦታ ለሚሰሩ ሠራተኞቹ ንፅህናውን የጠበቀ የመፀዳጃ ቤት በመስራትና ፈሳሾቹ ወደ ውኃ አካላት እንዳይለቀቁ በማድረግ የገፀ ምድር ውኃ እና የከርሰ ምድር ውኃ እንዳይበከሉ ማድረግ፣
11. የግንባታ ስራውን መሀንዲሶች፣ የአካባቢና የስራ ቦታ ደህንነት ጤና ባለሙያዎች እና ሌሎቹ የሚመለከታቸው አካላቶች ተስማምተው እና ተግባብተው ስራው የአካባቢውን ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ እንዲከናወን አድርጐ መስራት፣
12. ሁሉም የስራ ቦታዎች ወጥና ዘላቂ የሆኑ የፍሳሽና የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት በመዘርጋት ከጉዳዩ ጋር ቅርበት ካላቸው የመንግስትና የግል አካላት ጋር በጋራ መስራት፣

## 7. አፈርና ደንን ስለመጠበቅ

የአፈር እና ደን ደህንነትን ለመጠበቅ የሚከተሉት የጥንቃቄ እርምጃዎች ሊወሰዱ ይገባል፡-

1. ከስራ ጋር በተያያዘ ያለአግባብ የሚደረግ የመሬት ቆረጣና ቁፋሮ እንዳይኖር መከታተልና መቆጣጠር፣

2. የተሻሻሉና ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን ለኮንስትራክሽን ሥራዎች ግብአትነት በማዋል የተፈጥሮ ሀብት ላይ የሚደርሱ አላስፈላጊ ብክነቶችን፣ የደን መጨፍጨፍ፣ የአካባቢ እና ስነ-ምህዳር መራቆትን መቀነስ፣
3. ከመንገዶች፣ ከግድቦች፣ ህንፃዎች እና ሌሎች የግንባታ ሥራዎች ዳርቻ አካባቢዎችን ካላቸው የመሬት ተፈጥሯዊ አቀማመጥ ይዞታ ጋር ተስማሚ የሆኑ አገር በቀል እፅዋቶችን አስቀድሞ በማዘጋጀት ተንከባክቦ ማቆየት፣ መልሶ መትከል እና መልመዳቸውን/መፅደቃቸውን በማረጋገጥ የአካባቢውን ሥነ ምህዳር እና ብዝሀ ህይወት እንዲጠበቅ ማድረግ፣
4. ከከፍተኛ ቦታዎች ጠንካራ የመሬት አካል ቆረጣ ሲደረግ ከላይ እየተቆረጠ የሚወርደው በታችኛው መሬት በኩል በሚገኘው ህብረተሰብ ላይ ችግር እንዳይፈጥር የቅርብና የሩቅ ተፅእኖዎቹን ለመቀነስ የሚያስችል ስትራቴጂ ነድፎ መንቀሳቀስ፤
5. ግንባታ/ጥገና በሚካሄድባቸው አካባቢዎች የደን ውድመት፣ የአፈር መሸርሸርንና የአካባቢ መራቆትን መከላከል፤
6. በግንባታው ምክንያት የተነኩ የዱር እንስሳት መኖሪያዎችን በተቻለ መጠን አገር በቀል እፅዋትን በመትከል መተካት፣
7. ከፍተኛ ዳገትና የአፈር ቁልል እንዳይፈጠር ማድረግ፣
8. የአካባቢው ህብረተሰብ አካባቢውን እንዲከባከብና እንዲቆጣጠር ማሳተፍ፣
9. ለኮንስትራክሽን ግንባታ ለማዋል ድንጋይ ወይም አፈር በሚወጣበት ጊዜ የሚፈጠረውን ገደል/ጉድጓድ ስራውን እስከሚጠናቀቅ ድረስ በአጥር ማጠርና ስራው ከተጠናቀቀ በኋላ ገደሉን መልሰን አካባቢውን ባገናዘበ ሁኔታ መሙላት፣
10. ለድልድይና ለተለያዩ የግንባታና የጥገና ስራዎች እንጨት ቆርጦ ወይም ገዝቶ እንደ መሰላል መወጣጫ (Scaffolding) አለመጠቀም፡፡ በምትኩ ለዚህ ዓላማ የተዘጋጁ ከብረት የተሰሩ ተገጣጣሚ መሰላሎችን /መወጣጫዎችን/ መጠቀም፣
11. ግንባታ በሚሰራበት አባባቢ ሁሉ በተቆረጡ እፅዋት ምትክ ባዶ ቦታዎችንና ዳገት/ቁልቁለቶችን ሳሮችንና ሃገር በቀል ችግኞችን በመትከልና በመንከባከብ የነበረውን ስነ-ምህዳር እንዲቀጥል ማድረግ፣
12. ዳገትና ቁልቁለት በበዛባቸዉ አካባቢዎች በተቻለ መጠን እርከን በመስራትና ሳር በመትከል የውኃ አወራረዱን በማስተካከል የአፈሩን መሸርሸር መከላከልና የመንገዱን ደህንነት መጠበቅ፣

13. ሥነ-ምህዳሩን ያገናዘበ የግንባታ ስራ ጊዜዎችን ወይም ወራትን በአግባቡ መምረጥ፣
14. በመጥፋት ላይ ያሉ በሃገራችን ብቻ የሚገኙ እፅዋትንና እንስሳትን በተቻለ መጠን ከሌሎቹ በተለየ መልኩ ትኩረት በመስጠት እንዳይጐዱ ማድረግ፣
15. በሥራ አካባቢው ካሉ የአካባቢና የደን ልማት ጥበቃ አካላት ጋር በጋራ መስራት እና ድጋፍ ማድረግ፣

## 8. አየርን ከብክለት ስለመጠበቅ

የአየር ብክለትን ለመከላከልና ለመጠበቅ የሚከተሉት የጥንቃቄ እርምጃዎች ሊወሰዱ ይገባል፡-

1. የተሻሻሉና ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን ለኮንስትራክሽን ሥራዎች ግብአትነት በማዋል እና በኮንስትራክሽኑ የሚገኙ ማሽኖችና ተሽከርካሪዎችን በጊዜያቸው መጠገንና ሰርቪስ በማድረግ የተፈጥሮ ሀብት ላይ የሚደርሱ አላስፈላጊ ብክነቶችን፣ የደን መጨፍጨፍ፣ የአካባቢ እና ስነ-ምህዳር መራቆትን መቀነስ፣
2. ለተሽከርከሪዎች የልቀት መቆጣጠሪያ (Emission control system) መግጠም፣
3. በኮርፖሬሽኑ የተለያዩ ኘሮጀክቶችና የስራ ክፍሎች ካለአግባብ በየቦታው የሚጣሉ ወረቀቶችን፣ ኘላስቲኮችን፣ የተሰበሩ ጠርሙሶችን፣ የአሉሙኒየም ቆርቆሮዎችን፣ ብረቶችን እና የመሳሰሉትን መልሶ መጠቀም፤ መልሶ መጠቀም የማይቻል ከሆነ ደግሞ በህግ አግባብ ማስወገድ፣
4. የአየር ንብረትን የብክለት መጠን መቀነስ የሚያስችል ጥራቱን የጠበቀ ነዳጅ (High Quality fuel) መጠቀም፣
5. ብዙ በካይ ጋዞች የሚያወጡ መሳሪያዎችን ወይም ተሽከርካሪዎችን ትንሽ በካይ ጋዞች በሚያወጡ መተካት፣
6. በስራ ቦታዎች አካባቢ እንደ ጽድ (Pine) እና ቁጥቋጦዎች (Ribes shrub) የመሳሰሉትን እፅዋቶች በመትከል የናይትሮጅን ኦክሳይድ እና ሌሎች በካይ ጋዞችን እንዲጠቀሙ የAfforestation እና የReafforestation ሥራን መስራት፣
7. ኮርፖሬሽኑ የሚገዛቸው ማሽኖች እና ተሽከርካሪዎች ከአካባቢው ጋር የተዛመዱና የአየር ብክለትን የማያስከትሉ ወይም የማያባብሱ መሆን አለባቸዉ፣
8. ኮርፖሬሽኑ በተቻለው መጠን ለማሽኖችና ለተሽከርካሪዎች ታዳሽ ኃይሎችን በኃይል ምንጭነት መጠቀም፣
9. በኮርፖሬሽኑ በየትኛውም የሥራ ቦታ ሲጋራ እንዳይጨስ መከላከል፣

10. የኮርፖሬሽኑ ሰራተኞች በብዛት ለአየር ብክለት የሚጋለጡበት የስራ ዘርፍ በተለየ መልኩ ምህንድስናዊ የቁጥጥር ዘዴ፣ አስተዳደራዊ የቁጥጥር ዘዴ እና የግል መከላከያ መሳሪያዎች እንዲጠቀሙ ማድረግ፣
11. መሀንዲሶች፣ መካኒኮች፣ የአካባቢና የስራ ቦታ ደህንነት፣ ጤና ባለሙያዎች እና ሌሎች የሚመለከታቸዉ አካላቶች ተስማምተው እና ተግባብተው የአየር ብክለት እንዳይከሰት ወይም እንዳይባባስ በትብብር መስራት፣
12. የአየር ብክለትን ለመከላከል ከሚሰሩ መንግስታዊ ከሆኑ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በትብብር መስራት፣

## 9. የመሬትን ገፅታ ስለመጠበቅ

የመሬትን ገፅታ ለመጠበቅ የሚከተሉት የጥንቃቄ እርምጃዎች ሊወሰዱ ይገባል፡-

1. የሚከናወነው የግንባታ ሥራ ነባሩን የመሬት ገፅ ያገናዘበ ወይም ታሳቢ ያደረገ እንዲሆን ማድረግ፣
2. የመዝናኛ ስፍራዎችን እና በጣም አስፈላጊ የሆኑ ቦታዎችን (Sensitive areas) በተቻለ መጠን ከግንባታ ሥራው ጋር የተያያዙ ነገሮች እንዳይነኳቸው ማድረግ፣
3. ግንባታው በሚከናወንበት ቦታ የመሬቱ ገፅታ ሙሉ በሙሉ እንዳይቀየር ወይም በዛፎች የተሸፈነ እንዲሆን ለማስቻል የአካባቢው ህብረተሰብ የችግኝ ተከላ እና እንክብካቤ እንዲያደርግ ማስተባበር፣
4. በተለየ መልኩ ታሪካዊ ይዘት ያላቸውን ቦታዎች እስከ ብዝሀ ህይወት (biodiversity) ስርጭቱ በነበረበት እንዲሆን ማድረግ፣
5. በግንባታ ስራው ላይ የሚሰሩ መሐንዲሶች (Engineers)፣ የአካባቢና የስራ ቦታ ደህንነት ባለሙያዎች፣ የመሬት ገፅ አርክቴክቶች እና ሌሎች የሚመለከታቸው ሁሉ ተናበውና ተግባብተው የመሬቱ ገጽታ በማይጐዳበት መንገድ መስራት፣

## 10. ሥነ- ምህዳርን ስለመጠበቅ

1. የአየር፣ የአፈር እና የውኃ ብክለት በኮርፖሬሽኑ የአሰራር ሂደትና ሰራተኞች ምክንያት እንዳይከሰት ማድረግ፣

2. በጣም አስፈላጊ፣ ሀገር በቀልና ለመጥፋት የተቃረቡ የሚባሉ የእፅዋት እና የእንስሳት ብዝሀ ህይወት ባሉበት ቦታ የኮንስትራክሽን ስራው ከአካባቢው ቢያንስ የ500 ሜትር ርቀት እንዲኖረው ማድረግ፣
3. የተለያዩ እንስሳትና እጽዋት በተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴ የሚደርስባቸውን ጉዳት ለመቀነስ አላስፈላጊ እንቅስቃሴዎችን መገደብ እና በመንገድ ዳር ብዙ ሃገር በቀል ዛፎችን በመትከል እንደ አጥር እንዲያገለግሉ ማድረግ፣
4. ኮንስትራክሽኑ በብሔራዊ ፓርኮች፣ በጥብቅ ደኖች፣ በእንስሳት መጠበቂያና መከላከያ ስፍራዎች ብዙ አማራጭ የመንገድ ስራዎች እንዳይኖሩ ማድረግ፣
5. አካባቢን መንከባከብ ዋና ሥራቸው ከሆኑ መንግስታዊ፣ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ከአካባቢ መስተዳደር አካላት ጋር በጋራ መስራት፣

## ክፍል ሦስት

## የሙያ ጤንነትና ደህንነት

### 11. የሥራ ላይ አደጋዎችንና የጤና ጠንቆችን ስለመከላከል

የሥራ ላይ አደጋዎችን እና የጤና ጠንቆችን ለመከላከል የሚከተሉትን ተግባራት መፈፀም ይገባል፡-

1. በማንኛውም የሥራ እንቅስቃሴዎች ውስጥ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ መሳሪያዎችን በየጊዜው ክትትል በማድረግ ከአገልግሎታቸው ማስወገድ፣ አደጋ በማያስከትሉ

መሳሪያዎች መተካት ወይም ምህንድስናዊ መፍትሄ በመጠቀም የአደጋ ስጋት መጠናቸውን መቀነስ፤

2. ሠራተኞችን ማሳተፍ፣ በደህንነት ዙሪያ እንዲወያዩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣ በጋራ በመስራት አመለካከታቸውን ማሳደግና ኃላፊነት እንዲሰማቸው ማድረግ፣
3. በቂ የሆነ ሀብት መመደብና አስፈላጊ የሆኑ የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎችንና አልባሳትን ማቅረብ፣
4. ሠራተኞች የሚቀርቡላቸውን የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎችና አልባሳት የመጠቀምና በአግባቡ የመያዝ ልምዳቸውን እንዲያዳብሩና ግዴታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ማድረግ እና ግዴታቸውን በአግባቡ በማይወጡ ሠራተኞች ላይ በማኑዋሉ መሰረት አስፈላጊው አስተማሪ የሆነ አስተዳደራዊ እርምጃ የሚወሰድበትን አሰራር መዘርጋት፣
5. የአሰራር ዘዴንና ሂደትን ማሻሻል፣ ለስራ መሪዎችና ለሠራተኞች ተገቢውን የሥራ መመሪያ መስጠት፣ የአሰራር ግልጽነት መፍጠር፣
6. ስለ አደጋዎች እና ስለመጀመሪያ ደረጃ ህክምና እርዳታ ትምህርትና ስልጠናዎችን መስጠት፣
7. ማንኛውም ሠራተኛ በተሰማራበት የሥራ መስክ የሥራ ቦታ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ላይ በሚያደርገው አስተዋጽኦ መሰረት የሚመዘንበትና ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ሠራተኞች የሚበረታቱበት በተለይ መሣሪያ አንቀሳቃሾችና አሽከርካሪዎች በመሣሪያ አጠቃቀምና አያያዝ፣ መሣሪያን ከመጠበቅና ከአደጋ ነፃ በሆነ ሁኔታ ይዞ ከመቆየት አንፃር እንዲተጉ የሚያደርግ አሰራር ማስፈን፣
8. በኮርፖሬሽኑ የስራ ቦታዎች የደረሱ አጠቃላይ ክስተቶችን፣ ጉዳቶችን፣ አደጋ ያደረሱ ሰራተኞችንና በጉዳቱ ሳቢያ የደረሰውን ኪሳራና ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎችን በመለየት መመዝገብና አደራጅቶ መያዝ፣ ሁሉም እንዲያውቀው ማድረግ፣
9. በየዓመቱ የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና ጤንነት ቀን እንዲከበር በማድረግ አደጋና ጉዳትን ቀድሞ የመከላከል እንዲሁም በተፈጥሮ አካባቢ እንክብካቤና ጥበቃ ያላቸውን አመለካከት መገንባትና ባህልን ማሳደግ፣
10. ሠራተኞችን በሥራ ቦታ ላይ መቆጣጠር፣ የስራ መገልገያ መሳሪያዎችንና የሥራ ቦታዎችን በጥንቃቄ መያዝ፣

11.የአመራር ቁርጠኝነት፣ የምክክር ዘዴ፣ አርአያ የመሆን፣ ለጉዳዩ የተጠያቂነት ስሜት ማሳየት እና ግብረ መልስ የመቀበልና የመስጠት ልምድን ማዳበር፣

## 12. የፕሮጀክት ሳይት እና መኖሪያ ወይም የካምፕ ቦታ መረጣ

የፕሮጀክት ሳይት እና የመኖሪያ ወይም የካምፕ ቦታ መረጣ ከመከናወኑ በፊት በአካባቢው የሚከተሉት ጉዳዮች መኖራቸውን ማረጋገጥ ይገባል፡፡

1. ሊገነባ የታቀደውን የግንባታ ሥራ መጠንና የቆይታ ጊዜ ያገናዘበ የዋና ካምፕና ንዑስ ካምፖች ቦታን፣
2. የድንጋይና የጠጠር ማምረቻ መሣሪያዎች የሚተከሉበትን ቦታ አመቺነት፣
3. በሥራ አካባቢ በቅርብ ሊገኙ የሚገባቸው አገልግሎቶችን፣
4. የሥራ አካባቢው ለንብረትና ለሠራተኛ ደህንነት ምቹ መሆኑን፣
5. በተፈጥሮ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ክስተቶችንና አካባቢያዊ ሁኔታዎችን፣
6. ለሠራተኛው አስፈላጊ የሆኑ ፋሲሊቲዎች በቅርቡ ማግኘት የሚቻል መሆኑን፣
7. የጉልበት ሥራን ለሚጠይቁ ሥራዎች የሰው ኃይል በአካባቢው ሊገኝ መቻሉን፣
8. ለሠራተኛ መኖሪያ፣ ለቢሮ አገልግሎት፣ ለንብረት ማከማቻና በካምፕ ውስጥ ሊከናወኑ ለሚገቡ ሥራዎች በቂ ቦታ ስለመኖሩ፣
9. በፕሮጀክት የካምፕ ቦታ መረጣ ሲከናወን ወደ ሥራ ቦታ የሚደረገው ምልልስ የሥራ ጊዜንና የትራንስፖርት ወጪን፣
10. በረዥም ርቀት በሚደረግ ጉዞ ሊኖር የሚችል የአደጋ ክስተትንና ሌሎች መሰል ተያያዥ ጉዳዮችን ባገናዘበ መልኩ መስራት፣
11. ተመጋጋቢ ሥራዎች ሊደጋገፉ በሚችልበት ቅርበትና አንዱ ሥራ በሌላው ላይ ተጽእኖ በማያደርግበት ሁኔታ ሆኖ ሊከሰት የሚችል አደጋንና ጉዳትን በማገናዘብ ለቅድመ ጥንቃቄ ትኩረት የሰጠ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## 13. ለካምፕ የሚቀርብ ውኃ

1. በቂና ንጹህ የሆነ በሚመለከተው አካል የተረጋገጠ ለመጠጥ፣ ለማብሰያ፣ ለመታጠቢያ እና ለልብስ ማጠቢያ የሚሆን ንጹህ ውኃ ለካምፑ ነዋሪዎች መቅረብ አለበት፡፡

2. በማንኛውም ሁኔታ ክፍት በሆኑና በቀላሉ ሊበከሉና ሊዝጉ በሚችሉ እንደ ብረትና በርሜል ባሉ የውኃ ማጠራቀሚያ ዕቃዎች ውስጥ የተቀመጠን ውኃ ለመጠጥ አገልግሎት ማዋል ፈጽሞ የተከለከለ ነው፡፡
3. ውኃ በታንከር የሚቀርብ ከሆነ ታንከሩ በየጊዜው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግበት ይገባል፡፡

## 14. የመፀዳጃ ቤቶች

1. በሁሉም የግንባታ ፕሮጀክት ሳይቶች ለካምኘ ነዋሪዎች የሚሆን በቂ መፀዳጃ ቤት መኖር አለበት፡፡
2. መፀዳጃ ቤቶች ሌሎችን ሰዎች በማይረብሽ መልኩ መሰራት አለባቸው፡፡
3. ሁሉም የመፀዳጃ ቤቶች ተከፋች መስኮቶች ወንፊት ወይም መረብ መሰል ከለላ ሊኖራቸው ይገባል፡፡
4. በመፀዳጃ ቤቶች ውስጥና አካባቢ ምንም አይነት ተጨማሪ ነገር ማለትም ዕቃ ማከማቸት፣ እንጨት መከመር፣ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ገንዳ እና የመሳሰሉትን ማስቀመጥ አይቻልም፡፡
5. መፀዳጃ ቤቶች ከመኝታ ቤት ከ30 - 60 ሜትር ባለው ርቀት ላይ መሆን አለበት፡፡
6. የጋራ መጠቀሚያ የሆኑ መፀዳጃ ቤቶች እስከጣሪያ በሚደርስ ከለላ ተለይተው ለሁለቱም ጾታ የተለያየ መሆን አለበት ማለትም የሴት እና የወንድ ተብሎ በፅሁፍና በስዕል መገለጽ አለበት፡፡
7. አንድ መፀዳጃ ቤት አገልግሎት መስጠት ያለበት ቢበዛ ለ15 ሰዎች ብቻ ነው፡፡
8. ለወንዶች የውኃ ሽንት አገልግሎት የሚሰጡ በቂ ውኃ ያላቸው የሽንት ሳህኖች መኖር አለበቸው፡፡
9. ሁሉም የመፀዳጃ ቤት ክፍሎች በቂና ምቹ የብርሃን ምንጭ ወይም መብራት ሊኖራቸው ይገባል፡፡
10. ሁሉም የካምኘ ነዋሪዎች በቂ የመፀዳጃ ቤት ሶፍትና ሳሙና ሊቀርብላቸው ይገባል፣
11. ሁሉም መጸዳጃ ቤቶች በቀላሉ መፀዳት የሚችሉ ሆነው በየጊዜው መጽዳት አለባቸው፡፡

## 15. የፍሳሽ እና ደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ዘዴ

1. ካምፕ ያለበት አካባቢ የፍሳሽ እና ደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ዘዴ ካለ የካምፑን ፍሳሽ በማገናኘት እና ደረቁን በማጠራቀም አካባቢውን በማይጐዳ መልኩ ማስወገድ ያስፈልጋል፡፡
2. በሥራ አካባቢው ምንም አይነት የፍሳሽ ማስወገጃ ዘዴ ከሌለ ደግሞ በጥናት በመታገዝ የሥራ አካባቢውን ተፈጥሯዊ ሁኔታና የሥራ አካባቢውን ማህበረሰብ በማይጐዳ መልኩ እንደ የወባ ትንኞች፣ ዝንብ ያሉ ነፍሳቶች እንዳይራቡ በሚያደርግ ሁኔታ መሆን አለበት፡፡

## 16. የልብስ፣ የእጅና የገላ መታጠቢያ አገልግሎቶች

እነዚህ አገልግሎቶች እንደነዋሪው/ሰራተኞች ብዛት በሚከተለው መልኩ መሆን አለባቸው፡-

1. አንድ የእጅ መታጠቢያ ሳህን አገልግሎት መስጠት ያለበት ቢበዛ ለስልሳ (60) ሰዎች ብቻ ነው፡፡
2. አንድ ሻወር ወይም የገላ መታጠቢያ አገልግሎት መስጠት ያለበት ቢበዛ ለአስር (10) ሰዎች ብቻ ነው፡፡
3. አንድ የልብስ ማጠቢያ ገንዳ ወይም መሳሪያ አገልግሎት መስጠት ያለበት ቢበዛ ለሰላሳ (30) ሰዎች ነው፡፡

## 17. የምግብ ደህንነት፣ አቀማመጥና አያያዝ

1. ሁሉንም ምግቦች በትክክለኛው የሙቀት መጠን ውስጥ ማስቀመጥ፣
2. ምግቦችን ንጽህናው የተጠበቀ መክደኛ/መሸፈኛ ባለው ማስቀመጫ/መያዣ ውስጥ ማስቀመጥ፣
3. ያልበሰሉ/ጥሬ እና የበሰሉ/ለመበላት የተዘጋጁ ምግቦችን በተለያየ ቦታ ለይቶ ማስቀመጥ፣
4. ምግቦችን በአንድ ላይ ማስቀመጥ የግድ ከሆነ ያልበሰሉ/ጥሬ ምግቦችን ከበሰሉ ምግቦች በታች ማስቀመጥ፣
5. ምግቦችን ከመጠን በላይ ደራርቦ አለማስቀመጥ፣
6. የመጠጫና የመመገቢያ ዕቃዎች ከተፀዱ በኂላ በንፁህ ቦታ/እቃ ውስጥ ማስቀመጥ፣
7. የተባይ መቆጣጠሪያ ዘዴን በመጠቀም ተባዮች ምግብ እንዳይበክሉ መከላከል፣

8. የተሰበሩ፣ የተሰነጣጠቁ፣ የዛጉ፣ የተቦረቦሩ፣ የተሸራረፉና የተጣመሙ ዕቃዎች ቆሻሻ ስለሚይዙና ለማጽዳትም ሆነ ለመጠቀም ምቹ ስላልሆኑ መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡
9. ከምግብ ጋር ንክኪ የሚኖራቸው መሳሪያዎችና እቃዎች የመዛግ ባህሪ የሌላቸው መሆን አለባቸው፡፡

## 18. የምግብ ማከማቻ ወይም ማቆያ ክፍል

1. ግድግዳው ከድንጋይ፣ ከብሎኬት፣ ከሸክላ ወይም ከሌሎች ተመሳሳይ ቁሶች የተሰራ ሆኖ በክፍሉ ሙቀት ላይ ተፅዕኖ የማያሳድር እና በቀላሉ ሊፀዳ የሚችል መሆን አለበት፡፡
2. ወለሉ በሲሚንቶ ኮንክሪት፣ ሴራሚክ ወይም ሌላ ተመሳሳይ ቁሶች የተሰራ ሆኖ በቀላሉ ሊፀዳ የሚችልና ውሃ የማያቁር መሆን አለበት፡፡
3. የክፍሉ ስፋት እንደሚከማቸው የምግብ መጠንና አይነት በቂ ሆኖ ለጊዜው ጥቅም ላይ የማይውል ምግብ ማቆያ ቦታ ያለው መሆን አለበት፡፡
4. በርና መስኮቶች ነፍሳትን፣ ቆርጣሚ እንስሳትንና ሌሎች ምግቡን ሊበክሉ የሚችሉ ነገሮችን በማያስገባ መልኩ የተሰራ መሆን አለበት፡፡
5. ጣሪያው ሙቀትን ሊቀንስ የሚችል ሆኖ ቀጥተኛ የፀሐይ ብርሃን የማያስገባ መሆን አለበት፡፡
6. ክፍሎቹ በቂ የተፈጥሮ ብርሃንና የአየር ዝውውር ያላቸው መሆን አለባቸው፡፡
7. በአጠቃላይ ክፍሉ ከሚከማቸው ምግብና የምግብ ግብዓት ባህሪ አንፃር ብክለትን የማያስከትል እንዲሁም ጥራትና ደህንነት ላይ ተፅዕኖ በማያሳድር መልኩ የተሰራ መሆን አለበት፡፡

## 19. ስለ ህክምና አገልግሎቶች

1. በኮንስትራክሽን ሥራ ወቅት የሚደርሱ ጉዳቶች አስከፊ ጉዳት እንዳያስከትሉ የመጀመሪያ እርዳታ እና ጊዜያዊ እንክብካቤ መስጠት ይገባል፡፡
2. ሁሉም ሠራተኞች ስለመጀመሪያ እርዳታ አሰጣጥ፣ ስለመሳሪያዎች አጠቃቀምና አያያዝ ተገቢ ትምህርትና ስልጠና ማግኘት እንዲችሉ በማድረግ አገልግሎቱን ተደራሽ ማድረግ ይገባል፡፡
3. የመጀመሪያ እርዳታ ሰጪ ባለሙያ የተጎዳውን የጉዳት መጠን እና ምን አይነት ጊዜያዊ እርዳታ ሊሰጠው እንደሚገባ ማወቅ እንዲሁም ተጐጅውን ማጓጓዝ አስፈላጊ

ሆኖ ከተገኘ እንዴት ያለምንም ችግርና ተጨማሪ ጉዳት መጓጓዝ እንደሚቻል ማወቅ አለበት፡፡

4. የቆሰለና የሚደማ ጉዳተኛ ከቦታ ወደ ቦታ በባለሙያ በመታገዝ እንዲንቀሳቀስ ማድረግ፤

## 20. ስለጽዳት ሥራና ጽዳት ሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት

የፅዳት ስራ ሲከናወን እና የፅዳት ሰራተኞች ስራቸውን ሲያከናውኑ ከተለያዩ አደጋና ጉዳት ለመታደግ የሚከተሉትን የቅድመ ጥንቃቄ መርሆዎች ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡-

1. የሥራ አካባቢዎችን በየእለቱ ማፅዳትና ንፅህናቸውን መጠበቅ፣
2. መፀዳጃ ቤቶችን  በየእለቱ ማፅዳትና ንፅህናቸውን መጠበቅ፣
3. ዘላቂና ወጥ የሆነ የቆሻሻ አወጋገድ ስርዓት መዘርጋት፣
4. ራሱን የቻለ ከለላ ያለው የቆሻሻ ማቆያ ጊዜያዊ ቦታ እንዲኖር ማድረግ፣
5. የተለያየ ባህሪ ያላቸውን የቆሻሻ አይነቶች ለየብቻ በተለየ ዕቃ ውስጥ ማጠራቀምና ማስወገድ፣
6. ስለ ማጽጃ ኬሚካሎች ባህርይና ሊያስከትሉ ስለሚችሉት የጤና ቀውስ የግንዛቤ ማስጨበጫ  ስልጠና መስጠት፣
7. በተቻለ መጠን ስራውን ሊያቃልሉና የአደጋ ተጋላጭነትን ሊቀንሱ የሚችሉ መሳሪያዎችን እንዲጠቀሙ ማድረግ፣
8. መከላከያ መሳሪያዎችንና አልባሳትን መጠቀም፣

   ሀ. የኘላስቲክ እና የቆዳ ጓንት፣
   ለ. የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል/Respirator፣
   ሐ. ፕላስቲክ ቦቲ ጫማ እና የደህንነት ጫማ /safety shoe፣
   መ. የአይን መከላከያ ጎግል፣
   ሠ. የፊት መከላከያ ከለላ /face shield፣
   ረ. የፀጉር መሸፈኛ

## 21. የቢሮ ሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት

1. ጠረጴዛዎችና ወንበሮች በቁመት ተመጣጣኝና ለስራም ሆነ ለደህንነት ምቹ የሆኑና ጠርዛቸው ሹልና ስለታማ ያልሆነ ለስላሳና በግጭት/በመነካካት ለጉዳት የማይዳርጉ እንዲሁም ወንበሮች እንደተጠቃሚው አካላዊ ሁኔታ መስተካከል የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡

2. የፋይል መደርደሪያና ማስቀመጫ ካቢኔቶችና መሳቢያዎች መቆለፍ የሚችሉና በሆነ አጋጣሚ ተንሸራተው/ወድቀው አደጋ የማያደርሱ መሆን አለባቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለአደጋ በሚያጋለጥ ሁኔታ ከአቅማቸው በላይ ዕቃ/ፋይል እንዲይዙ መደረግ የለበትም፡፡
3. ኮምፒዩተሮች የብርሃን መጠናቸው ለአይን በሚስማማ መልኩ መስተካከል የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡
4. የኘሪንተሮችና ፎቶ ኮፒ ማሽኖች ቶነር ሽታ፣ አቧራና ብናኝ ፈጥሮ ሰራተኞች ላይ ችግር እንዳያስከትሉ በቂ የማናፈሻ ዘዴ ባለበት አካባቢ ሊቀመጡ ይገባል፡፡
5. የስራ ክፍሉ/ቢሮው ከሚያዳልጡ፣ ከሚያንሸራትቱ፣ ከሚጠልፉና ሌሎች ተመሳሳይ ከሆኑና ጥለው ለአደጋና ለጉዳት ከሚያጋልጡ ነገሮች የፀዳ መሆን አለበት፡፡
6. የተሰበሩ፣ የተበላሹና አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የቢሮ መገልገያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች በሚመለከተው አካል እንዲወገዱ ማድረግ ይገባል፡፡
7. በቢሮ ውስጥ ያሉ የኤሌክትሪክ ማከፋፈያዎችን ለሌላ አላማ መጠቀምና ከአቅማቸው በላይ እንዲሰሩ ማድረግ ለእሳት አደጋና ለጉዳት ሊዳርግ ስለሚችል ይህንን መፈፀም ክልክል ነው፡፡ ለምሳሌ በቢሮ ውስጥ የኤሌክትሪክ ምድጃ/ስቶቭ መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡
8. በቢሮ ውስጥ ባሉ የፋይል መደርደሪያ/ማስቀመጫ ካቢኔቶችና መደርደሪያዎች ላይ ከባድና ወድቀው አደጋና ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ዕቃዎችን ማስቀመጥ የተከለከለ ነው፡፡
9. በቢሮ ውስጥ ከስራ ጋር ተያያዥነት የሌላቸውንና ለሰራተኞች ደህንነትና ጤና አስጊ የሆኑ ዕቃዎችንና ቁሳቁሶችን በጊዜያዊነትም ሆነ በዘላቂነት ማስቀመጥ የተከለከለ ነው፡፡
10. በቢሮዎች በር መግቢያና መውጫ ኮሪደሮች ላይ የሚቀመጡ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ አትክልቶችና አበባዎች የስራ እንቅስቃሴን የሚገድቡና ለአደጋ በሚያጋልጥ መልኩ ከተገቢው በላይ በብዛት ማስቀመጥ የተከለከለ ነው፡፡
11. በስራ ቦታ አካባቢና በቢሮ ውስጥ እንደ ሻማ ያሉ በግልፅ የሚበሩና ለአደጋ የሚያጋልጡ መብራቶችን መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡
12. ለቢሮ ስራ አገልግሎት ላይ የሚውሉ ስለታማና ሹል የሆኑ ነገሮች በጥንቃቄ ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታና አካባቢ መቀመጥ አለባቸው፡፡

13. በቢሮ ውስጥና አካባቢ የሚከሰቱ ነፍሳትና እንሰሳትን ሊያመጡ የሚችሉ ምግቦችንና የምግብ ትርፍራፊዎችን በቢሮ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ማስቀመጥ/መጣል የተከለከለ ነው፡፡
14. በቢሮ አካባቢ ያሉ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ዕቃዎች ተባይና ነፍሳትን እንዳያመጡ በየቀኑ ማፅዳትና መግቢያ ቦታዎች በትክክል መዘጋት አለባቸው፡፡

# ክፍል አራት

# በግንባታ ቦታ ስለሚከናወኑ ሥራዎችና ስለ ጥንቃቄዎች

## 22. በሰው ኃይል ወይም በማሽነሪ የማፍረስ ሥራ

ኮርፖሬሽኑ በሰው ኃይል ወይም ማሽነሪ በመጠቀም ለሚያከናወናቸው የማፍረስ ሥራዎች የሚከተሉት ጥንቃቄዎች ሊወሰዱ ይገባል፡-

1. የማፍረስ ሥራው እንዴት እንደሚከናውን ዝርዝር ዕቅድ ማዘጋጀት፣
2. የኤሌክትሪክ፣ የስልክ እና የሌሎች መሠረተ ልማት መስመሮች ዝርጋታ መቋረጡን ማረጋገጥ፣
3. ተገቢውን የሰው ኃይልና መሣሪያ ማዘጋጀት፣
4. የማፍረስ ስራውን የሚቆጣጠር በቂ ልምድና ክህሎት ያለው ባለሙያ መመደብ፣
5. የማፍረስ ሥራ ሲከናወን በአጐራባች ይዞታ ወይም ንብረት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ፣
6. የማፍረስ ሥራ የሚያከናውኑ ባለሙያዎች ተገቢውን የደህንነት መሣሪያ መጠቀማቸውን ማረጋገጥ፣
7. በማፍረስ ሥራ ወቅት በአቧራም ሆነ በሌላ ብናኝ አካባቢው እንዳይበከል ተገቢውን መከላከያ መጠቀም፣
8. ከፍተኛ ክብደት ያላቸው ነገሮች በሚፈርሱበት ወቅት መሬት ላይ ወድቀው ሌላ ጉዳት እንዳያደርሱ መጠንቀቅ፣

## 23. ፈንጂዎችን በመጠቀም የማፍረስ ሥራ

ፈንጂዎችን በመጠቀም በሚከናወኑ የማፍረስ ስራዎች ላይ የሚከተሉት ስራዎች ወይም ጥንቃቄዎች ሊወሰዱ ይገባል፡-

1. የፈንጅዎችን የፍንዳታ መጠን ከሚመለከተው ክፍል ማረጋገጥ፣
2. ፈንጂዎችን ከመጠቀማቸው በፊት ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት ማሣወቅ፣
3. በአካባቢው በፈንጂው በሚፈጠረው ንዝረት ጉዳት ሊደርስባቸው የሚችሉ ንብረቶች መኖራቸውን ማጣራትና ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ፣
4. ተገቢውን ጥንቃቄ ባለማድረግ በአካባቢው ባሉት ንብረቶች ላይ ጉዳት ቢደርስ የደረሰውን ጉዳት በመጠገን ወደ ነበሩበት መመለስ፤
5. በሚፈነዳበት ወቅት የድምፅም ሆነ የአቧራ ብክለት እንዳይኖር ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ፣
6. ፍንዳታውን የሚያከናውኑት ሠራተኞች ተገቢውን የደህንነት መሣሪያ መጠቀማቸውን ማረጋገጥ፣

## 24. የቁፋሮ ሥራዎች

ኮርፖሬሽኑ በሚያከናውናቸው የቁፋሮ ሥራዎች ላይ የሚከተሉትን ጥንቃቄዎች መወሰዳቸው መረጋገጥ ይኖርበታል፡-

1. ሁሉም የቁፋሮ ሥራ በተገቢው ባለሙያ መሰራቱን፣
2. የቁፋሮ ሥራ ከመጀመሩ በፊት ቁፋሮ የሚካሄድበት ቦታ ከማንኛውም የመሠረተ ልማት ዝርጋታ የፀዳ መሆኑን፣
3. ዛፎች፣ ቋጥኞች ወይም ሌሎች ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ነገሮች ከቁፋሮው ቦታ በቅድሚያ መወገዳቸውን፣
4. የግንባታ ቦታው አፈር በአግባቡ መጠናቱንና ተገቢው ጥንቃቄ መደረጉን፣
5. ሠራተኞች በአፈር መናድም ሆነ ጉድጓድ ውስጥ በመውደቅ ምንም ዓይነት ጉዳት እንዳይደርስባቸው ጥንቃቄ መደረጉን፣
6. ቁፋሮ ከመጀመሩ በፊት ቁፋሮ የሚካሄድበትን ቦታ ለይቶ መከለል፣
7. የሚቆፈረው ጉድጓድ ከ1.5 ሜትር በላይ ከሆነ ለሠራተኛ መግቢያና መውጫ መሰላል መዘጋጀቱንና መሰላሉ ከጉድጓዱ የላይኛው ጠርዝ ከ80 ሴ.ሜ በታች ዝቅ አለማለቱን፣
8. የሚቆፈረው ጉድጓድ ከ3 ሜትር በላይ ከሆነ በ$90^0$ ከመቆፈር ይልቅ አግድም (ስላይድ) አድርጐ መቆፈሩን፣

9. የቁፋሮ ስራው በሚሰራበት ወቅት አፈሩ የመናድ ባህሪ ካለውና በአከባቢው ሌሎች ግንባታዎችና የመሰረተ ልማት አውታሮች ካሉ ደህንነታቸውን ለመጠበቅ ግዜያዊ የድጋፍ መዋቅር (shoring) መሰራቱን፣
10. ቁፋሮው በሚከናወንበት ወቅት በአከባቢው ስነ ምህዳር (Ecology)፣ ታሪካዊ ቅርሶችና ሌሎች ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው ሀብቶች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ አስፈላጊው ጥንቃቄ መወሰዱን፣
11. ተቆፍሮ የሚወጣው አፈር በየጊዜው ከግንባታ ቦታ ላይ መነሳቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

## 25. የፎርም ዎርክ (Form work) ሥራዎች

ኮርፖሬሽኑ በሚያከናውናቸው የፎርም ዎርክ ሥራዎች ላይ የሚከተሉትን ጥንቃቄዎች መውሰድ አለበት፡-

1. ፎርም ዎርክ ምንም አይነት ክፍተት ሳይኖረው በአግባቡ መገጠም አለበት፡፡
2. የውስጠኛው የፎርም ዎርክ ክፍል ንፁህ እና ምንም አይነት ወጣ ገብ የሌለው መሆን አለበት፡፡
3. ፎርም ዎርክ በሚፈታበት ጊዜ በቀላሉ ከመዋቅሩ ላይ እንዲላቀቅና አደጋ እንዳያደርስ ለዚሁ አላማ የተዘጋጀ ማለስለሻ ዘይት መቀባት አለበት፡፡
4. ለስላብ የምንጠቀመው ፎርም ዎርክ ከሆነ ሁሉም በእኩል ደረጃ መደርደር አለባቸው፡፡
5. የስላብ ፎርም ዎርክ ለመደገፍ የሚቆመው ቋሚ በቂ ጥንካሬ ሊኖረው ይገባል፡፡
6. አርማታ (Concrete) በቂ ጥንካሬ እስኪኖረው ድረስ ፎርም ዎርክ መነሣት የለበትም፡፡
7. ፎርም ዎርክ መነሣት ያለበት የሚመለከተው ባለሙያ ሲፈቅድ ብቻ ይሆናል፡፡
8. ፎርም ዎርክ በሚነሣበት ወቅት አደጋ እንዳይፈጥር ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡

## 26. የስካፎልዲንግ (Scaffolding) ሥራዎች

ኮርፖሬሽኑ ስካፎልዲንጎችን በመጠቀም በሚያከናውናቸው ስራዎች ላይ የሚከተሉትን ጥንቃቄዎች መውሰድ አለበት፡-

1. ስካፎልዲንግ ጠንካራ የማይንቀሳቀስና እንዲሸከም ከታቀደለት ክብደት በላይ አራት እጥፍ መሸከም የሚችል መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡
2. ተገቢው ጥንካሬ ያላቸውን እንጨት ወይም ብረት መጠቀም አለበት፡፡
3. ከመሬት በላይ ከአምስት ወለል በላይ ለሆኑ ህንፃዎች የእንጨት Scaffolding መጠቀም የለበትም፡፡
4. ከሦስት ሜትር ከፍታ በላይ ላለ Scaffolding ቢያንስ 1 ሜትር ከፍታ ያለው የመጠበቂያ ከለላ እንዲኖረው ማድረግ ይገባል፡፡
5. ማንኛውም Scaffolding ከሚያንሸራትት ነገር እና ከፍሳሽ ነገሮች የፀዳ መሆን አለበት፡፡
6. ከ10 ሜትር በላይ ከፍታ ባላቸው Scaffolding ላይ የሚሰሩ ሠራተኞች የወገብ ቀበቶ መጠቀማቸው መረጋገጥ አለበት፡፡
7. ከ15 ሜትር በላይ ከፍታ ካለ ተገቢውን ከለላ መጠቀም አለበት፡፡
8. ሠራተኞች ተገቢውን የደህንነት መሣሪያ መጠቀማቸው መረጋገጥ አለበት፡፡
9. Scaffolding በተገቢው ሁኔታ የተገጠመ ወይም የተያያዘ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡
10. የእንጨት Scaffolding ከሆነ ከአንድ ፕሮጀክት በላይ መጠቀም የማይቻል ሲሆን የፕሮጀክቱ ጊዜ ረጅም ከሆነና የተለያዩ ወቅቶችን የሚያልፍ ከሆነ የእንጨቱ ጥንካሬ በባለሙያ ተረጋግጦ አገልግሎት የሚሰጥ ይሆናል፡፡
11. ለመቆሚያነት የሚዘጋጀው ጣውላ ወይም ብረት በቂ ጥንካሬ ያለው፣ የማያንሸራትት እና ስፋቱ ከ40 ሴ.ሜ ያላነሰ መሆን አለበት፡፡
12. ስከፎልድ ጠንካራ መሠረት (Sold Footing) ላይ መቆሙ በባለሙያ መረጋገጥ አለበት፡፡
13. ቋሚ ያልሆኑ ቁሳቁሶችን፣ ባልዲዎችን፣ ሣጥኖችን፣ ኮንክሪት ብሎኬቶችን ለስካፎልድ መደገፊያ መጠቀም የለበትም፡፡
14. ከባለሙያ ውጭ ስካፎልድ መትከል፣ ማዘዋወር፣ ማስተካከልና መነቃቀል አይቻልም፡፡
15. የስካፎልድ ተገጣጣሚዎች (Braces, Brakets, Trusses, Screw, Legs or Ladder) ሲላሉና ሲበላሹ ወዲያውኑ መተካት ወይም መጠገን አለባቸው፡፡
16. ስካፎልድ በባለሙያ በየወቅቱ መፈተሽ (ኢንስፔክት መደረግ) አለበት፡፡

## 27. መውደቅን ስለመከላከል (Fall Protection)

የሥራ ላይ አደጋን እንዳይከሰት እና መውደቅን ለመከላከል የሚከተሉት የጥንቃቄ እርምጃዎች ሊወሰዱ ይገባል፡-

1. መንገድ እና ሕንጻ ላይ ቋሚ ወይም ጊዜያዊ የመውደቅ መከላከያ፣ የደህንነት መረብ እና የቀዳዳ መሸፈኛዎች ወይም የደረጃ መውጫ መደገፊያዎች በትክክል መኖሩን ማረጋገጥ፣
2. የወለልና ጣራ ወይም ጠርዞች ላይ የመከላከያ ቁሳቁስ እና የማስጠንቀቂያ መስመሮች መደረጋቸውን ማረጋገጥ፣
3. የወለል ቀዳዳዎች መደፈናቸውን ወይም ሠራተኛው የደህንነት ቀበቶ ማድረጉን ማረጋገጥ፣

## 28. የመሰላል (Ladder) ሥራዎች

መሰላልን በመጠቀም በሚሰሩ ስራዎች ላይ የሚከተሉት ጥንቃቄዎች ሊወሰዱ ይገባል፡-

1. ሁለቱ ቋሚዎች ቀጥ ያሉና በቂ ጥንካሬ ያላቸው በቁመትም እኩል የሆኑ መሆን አለባቸው፡፡
2. አግድም የሚደረደሩት እኩል ርዝማኔ ያላቸው፣ ትይዩ የሆኑና በቂ ጥንካሬ ያላቸው መሆን አለባቸው፡፡
3. አግድም በሚደረደሩት መሀል የሚኖረው ርቀት ከ40 ሴ.ሜ መብለጥ የለበትም፡፡
4. የመሰላሉ የታችኛው መቆሚያ የማይንሸራተት መሆን አለበት፡፡
5. መሰላሉ ላይ ምንም ዓይነት ልብስ ሊይዝ ወይም ቁስል ሊፈጥር የሚችል ነገር መኖር የለበትም፡፡
6. በኤሌክትሪክ ስራ ወቅት የምንጠቀምባቸው መሰላሎች ኤሌክትሪክ ከማያስተላልፉ ቁሶች የተሰሩ መሆን አለባቸው፡፡
7. መሰላሉ በሚቆምበት ወቅት ከሚደገፈው አካል በ$30^0$ መሆን አለበት፡፡
8. የእንጨት መሰላል በሚዘጋጅበት ወቅት እንጨቶችን ቀጣጥሎ መጠቀም አይቻልም፡
9. መሰላልን ለመወጣጫ እንጂ መሰላሉ ላይ ቆሞ መስራት አይቻልም፡፡
10. መስላሎችን ከመጠቀማችን በፊት የአወቃቀር፣ የመጉበጥና የመሰበር ችግር እንዲሁም የጎደሉ መወጣጫዎች የሌሉ መሆኑ በባለሙያ መረጋገጥ አለበት፡፡

11. አቧራ፣ ቅባቶች፣ ቀለምና የሚያዳልጡ ነገሮች መስላሉ ላይ ያለመኖራውን ማረጋገጥ፣
12. በተበላሹ መስላሎች ላይ "**የተበላሸ**" የሚል ጽሑፍ መለጠፉ መረጋገጥ አለበት፡፡
13. ብረት ነክ መስላሎችን በኤሌክትሪክ መስመር አካባቢ አለመጠቀም፡፡

## 29. የክሬን (Crane) ሥራዎች

የክሬን ስራዎች በሚሰሩበት ወቅት የሚከተሉት እርምጃዎች መወሰዳቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡-

1. በሙያው ብቃት ባለው ሰው የተከላ ንድፍ የተሰራለት እና የተተከለ መሆኑን፣
2. ተገቢው የአደጋ ግምገማ እና የአተገባበር ዘዴ መግለጫ የተዘጋጀ እና የተተገበረ መሆኑን፣
3. ተገቢው የንፋስ ኃይል መለኪያ መሣሪያ የተገጠመለት መሆኑን፣
4. በጠንካራ መሠረት ላይ የቆመና በአግባቡ ከጠንካራ መዋቅር ጋር የተያያዘ መሆኑን፣
5. በክሬን የሚነሳው የእቃ ክብደት ከክሬኑ የመሸከም አቅም ጋር የተመጣጠነ መሆኑን፣
6. ክሬኑ በሚንቀሳቀስበት አካባቢ ስር ሆኖ የሚከናወን ስራ አለመኖሩንና ምንም አይነት የሚንሳቀስ ሰውም ሆነ እንስሳ አለመኖሩን፣
7. ብቃት ያለው ባለሙያ የተመደበለት መሆኑን፣
8. ለክሬኑ የተመደበው ባለሙያ ለሥራው ብቁ መሆኑን የሚያሳይ የጤና ምርመራ በማድረግ ማረጋገጫ ማቅረቡ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

## 30. የዕቃ ማንሻ (Fork Lift)

ፎርክሊፍትን በመጠቀም በሚሰሩ ስራዎች የሚከተሉት የጥንቃቄ እርምጃዎች ሊወሰዱ ይገባል፡-

1. የፎርክ ሊፍት አሽከርካሪዎች ዕድሜአቸው ከ18 ዓመት በላይ የሆኑ መሆናቸውን፣
2. የፎርክ ሊፍቱ አካል ወቅታዊ ፍተሻ የተደረገለት መሆኑን፣
3. በፎርክ ሊፍቱ አካል ላይ ቅጥያ ወይም የሞዲፊክ ሥራ አለመሠራቱን፣

4. ለማንሳት፣ ለማዘዋወርና ለማከማቸት ትክክለኛውን የአሠራር ቅደም ተከተል መጠቀም፣
5. በአንሸራታችና በተጨናነቀ ቦታ ደህንነቱ ተጠብቆ ለመሥራት በሰዓት ከ5 ኪ/ሜ በላይ አለማሽከርከር፣
6. ሁልጊዜ የደህንነት ቀበቶ ማድረግ፣
7. የኋላ ማርሽ ማሳወቂያ አላርም መስራቱንና በበቂ ሁኔታ መሰማቱን ማረጋገጥ፣

## 31. በማምረቻ ማዕከሎች መደረግ ያለባቸው ጥንቃቄዎች

1. በየማምረቻ ማዕከሉ መሠረታዊ የማሽን ክፍል ሕጎችን ለሁሉም ሠራተኞችና ጎብኝዎች በሚታይ ቦታ ማስቀመጥ፣

   ሀ/ ከባለሙያው በስተቀር ማሽን መጠቀም የተከለከለ መሆኑ፣

   ለ/ በማሽን ክፍል ውስጥ ብቻውን መሥራት የተከለከለ መሆኑ፣

   ሐ/ የሠራተኞች ፀጉር፣ የተዝረከረከ ልብስና ጌጣጌጥ ለአደጋ ሊያጋልጡ ስለሚችሉ ጥንቃቄ ማድረግ፣

   መ/ የማሽን ሥራ ከመጀመሩ በፊት የአደጋ መከላከያ ማድረግ፣

   ሠ/ ማሽን ላይ ሲሰሩ እጅና አካል ከማሽኑ ጋር ያለውን ርቀት መቆጣጠር፣

   ረ/ ማሽን ሲጠቀሙ ምንም ዓይነት ሙዚቃ አለማዳመጥ፣
2. በየማዕከሉ የእሳት አደጋ መከላከያና የመጀመሪያ ደረጃ ሕክምና መስጫ ሣጥን ከተሟላ ህክምና መስጫ ዕቃዎች ጋር በበቂ ሁኔታ ማኖር፣
3. ማዕከሉ ሁልጊዜ ከሚያዳልጡ፣ ከሚያንሸራትቱና ከሚያደናቅፉ ቁሶች የፀዳ ማድረግና የምርት ግብዓቶችን በሥርዓት ማስቀመጥ፣

## 32. የግንባታ ተሽከርካሪዎች እና ተንቀሳቃሽ የግንባታ ግብዓት ማቀነባበሪያ ሥራዎች

የማቀነባበሪያ ስራዎችን ለመስራት የሚከተሉት የጥንቃቄ እርምጃዎች ሊወሰዱ ይገባል፡-

1. ለሚሰራው ስራ የሚመጥን የግንባታ ንድፍ ያላቸው መሆኑን፣
2. ጥራት ባለው ሁኔታ የተሰሩ መሆናቸውን፣
3. ለታለመላቸው ዓላማ ብቻ መዋላቸውን፣
4. በተሽከርካሪዎቹ ማኑዋል መሰረት ወቅታዊ እድሳት የተደረገላቸው መሆኑን፣

5. አስፈላጊውን ትምህርትና ሥልጠና ወስዶና ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል ባለሙያ የሚንቀሳቀሱ መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

## 33. በግንባታ ቦታ ላይ ያሉ የኤሌክትሪክ መስመሮች፣ በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሰሩ ማሽኖችና የግንባታ መሣሪያዎች

ኮርፖሬሽኑ በሚያከናውናቸው ስራዎች ኤሌክትሪክ መስመሮችን አስመልክቶ ተከታዮቹን ጥንቃቄዎች ሊያደርግ ይገባል፡-

1. የግንባታ ሥራው ከመጀመሩ በፊትና በግንባታ ወቅት ሠራተኞችን ለኤሌክትሪክ አደጋ የሚያጋልጡ ሁኔታዎች ያለመኖራቸውን፣
2. በአካባቢው ያሉት የኤሌክትሪክ መስመሮች በግንባታው ምክንያት ምንም ጉዳት የማይደርስባቸው መሆኑን፣
3. ሁሉም ጊዜያዊ የኤሌክትሪክ መስመሮች ብቃት ባለው ባለሙያ ንድፍ የተሰራላቸውና የተዘረጉ መሆኑን፣
4. የኤሌክትሪክ ገመዶች ያልተላጡ እና የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ መሆኑን፣
5. ማንኛውም በኤሌክትሪክ ኃይል የሚንቀሳቀሱ ማሽኖች ለዚሁ ሥራ በሰለጠኑና ብቃታቸው የተረጋገጠ ባለሙያ የሚሠራባቸው መሆኑን እና ለማሽኖቹ አስፈላጊው ክትትልና ጥገና የሚደረግላቸው መሆኑን፣
6. ሠራተኞች የሚጠቀሙባቸው የደህንነት መሳሪያዎች ኤሌክትሪክ የማያስተላልፉ መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

## 34. በግንባታ ቦታ ላይ ያሉ የተቀጣጣይነት ባህሪ ያላቸው ፈሳሽ ነገሮች አጠቃቀምና አቀማመጥን በተመለከተ

በግንባታ ቦታ ላይ ያሉ የተቀጣጣይነት ባህሪ ያላቸው ፈሳሽ ነገሮች አጠቃቀምና አቀማመጥ በተመለከተ የሚከተሉት ጥንቃቄዎች ሊወሰዱ ይገባል፡-

1. የተቀጣጣይነት ባህሪ ያላቸው ፈሳሽ ነገሮች ጥቅም ላይ ሲውሉ ወይም ሲቀመጡ አደጋ በማያስከትሉና የሥራ አካባቢን በማይበክሉ መልኩ መሆኑን፣
2. ተቀጣጣይ ቁሶች በተከማቸበት ቦታ ከእሳት ጋር የተያያዘ ሥራ እንዳይሰራ መከላከልና ይህንኑ የሚያሳይ ምልክት ማስቀመጥ፣

3. ተቀጣጣይ ቁሶች ያሉበት መጋዘን ምቹ በሆነ ቦታ ላይ በቂ የእሳት ማጥፊያ መሣሪያ የተቀመጠ መሆኑን፣
4. ለአንድ ቀን ፍጆታ ብቻ የሚውል ከመጋዘን እንዲወጣ መደረጉን፣
5. የተቀጣጣይነት ባህሪ ያላቸው ፈሳሽ ነገሮች በጥቅም ላይ በሚውሉበት ጊዜ የደህንነት ባለሙያ በቦታው ላይ መገኘቱን፣
6. በደንብ በተከደነ እቃ የተቀመጡ መሆኑንና ካለቀ መያዣው በአግባቡ የተወገደ መሆኑን፣
7. በቆርቆሮ የታሸጉ ከሆኑ ፈሳሹ ሲያልቅ መያዣው እቃ በተገቢው መንገድ የተወገደ መሆኑን፣
8. ምንም ዓይነት እሳት ሊያስነሱ የሚችሉና የተቀጣጣይነት ባህሪ ያላቸው ሌሎች ነገሮች አለመኖራቸው መረጋገጥ አለበት፡፡

## 35. በውኃ አካባቢ የግንባታ ሥራዎች

ግንባታው የሚከናወነው በውኃ ላይ ወይም ለውኃ ቅርበት ባለው አካባቢ ከሆነ፣

1. በግንባታ ስራው ምክንያት ውኃው ሊበከል እንደማይችል፣
2. ሰዎች ወደ ውኃ እንዳይወድቁ መከላከያ የተሰራ መሆኑን፣
3. የመስጠም አደጋ ሲያጋጥም ወዲያውኑ ተገቢውን እርዳታ ማድረግ የሚችል የህይወት አድን ባለሙያ የተመደበ መሆኑን፣
4. ከመስጠም የሚከላከል በቂ መሣሪያ ለሠራተኞች የተዘጋጀ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡

## 36. የግንባታ ቦታዎች አጠባበቅ

የግንባታ ቦታውን ጥበቃ ቀጥሮ የማስጠበቅ ኃላፊነት ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1. የግንባታ ግብዓቶች በሙሉ በአግባቡ የተቀመጡ መሆኑን፣
2. የግንባታ ተረፈ ምርቶች በአግባቡ የተወገዱ መሆኑን፣
3. የግንባታ ግብዓቶች የግንባታ ስራን በማያውክ እና በሰዎችና በእንስሳት ላይ ጉዳት በማያደርሱበት መልኩ የቀመጡ መሆኑን፣
4. ግንባታ ላይ የማይውሉ ነገሮች በተገቢው ጊዜ የሚወገዱ መሆኑን፣

5. የግንባታ ተረፈ ምርት ወይም ፍርስራሽ ከከፍታ ቦታ ሲወገድ በተገቢው ጥንቃቄ የሚወገዱ መሆኑን፣
6. የግንባታ ቦታው በአግባቡ የታጠረ መሆኑን፣
7. ከሥር ሰዎች የሚተላለፉበት ቦታ ላይ ከላይ ግንባታ የሚካሄድ ከሆነ ተገቢውን መከላከያ የተገነባ መሆኑን መረጋገጥ አለበት፡፡

## 37. በግንባታ ቦታ የእሳት አደጋ እንዳይከሰት የማድረግ ሥራ

በግንባታ ቦታዎች ላይ የእሳት አደጋ እንዳይከሰት የሚከተሉት ጥንቃቄዎች መደረጋቸው መረጋገጥ አለበት፡-

1. የእሳት አደጋ እንደይከሰት አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ፣
2. የተቀጣጣይነት ባህሪ ላላቸው ነገሮች በቂና ምቹ ቦታ ማዘጋጀት፣
3. ዝግ በሆኑ አካባቢዎችና ሌሎች የእሳት አደጋ ሊከሰት በሚችሉባቸው ቦታዎች ላይ ያሉ የኤሌክትሪክ መስመሮች በአግባቡ መከላከያ የተደረገላቸው መሆኑን እንዲሁም ምንም ዓይነት ተቀጣጣይነት ባህሪ ያላቸው ነገሮች ወይም እሳት ሊያስነሱ የሚችሉ ነገሮች አለመኖራቸውን፣
4. አገልግሎት መስጠት የሚችል ምቹና በቂ የእሳት ማጥፊያ በተገቢው ቦታ መኖሩን፣ የእሳት ማጥፊያ መሣሪያዎቹ በየጊዜው ፍተሻ የሚደረግላቸው መሆኑን፣
5. በቂ ቁጥር ያላቸው ሠራተኞች የእሳት ማጥፊያ መሣሪያ አጠቃቀም በቂ ሥልጠና የተሰጣቸው መሆኑን፣
6. የእሳት አደጋ ሲከሰት ከአደጋ ማምለጫ አቅጣጫ ጠቋሚ ምልክት የተቀመጠ መሆኑን፣
7. በአደጋ ጊዜ የማምለጫ መንገዶች ጽዱና በቂ ስፋት ያላቸው መሆኑን መረጋገጥ አለበት፡፡

## 38. የዕቃ ማመላለሻ መሣሪያዎች ወይም ማሽኖች

የዕቃ ማመላለሻዎች ወደ ላይና ታች በሚመላለሱበት ወቅት፡-

1. በቂ ልምድና ክህሎት ያለው ባለሙያ የመመደብ፣
2. በጠንካራ ገመድ የተንጠለጠሉ መሆናቸውን የማረጋገጥ፣
3. ማመላለሻ ማሽኖቹ ከሚችሉት አቅም በላይ እቃ እንዳይጫን የማድረግ፣

4. በማመላለሻ ማሽኖቹ አካባቢ ሌሎች ሠራተኞች እንዳይኖሩ የማድረግ፣
5. ድንገት የገመድ መበጠስ አጋጥሞ አደጋ እንዳያደርስ ተገቢውን ጥንቃቄ የማድረግ፣
6. ሠራተኞች ተገቢው የደህንነት መሣሪያ መጠቀማቸውን የማረጋገጥ፣
7. መሣሪያዎቹን በየወቅቱ እድሳት እንዲደረግላቸው የማድረግ፣
8. የዕቃ ማመላለሻ ማሽኖች ተገቢው ጥንካሬ እንዳላቸው መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

## 39. የሰው ማመላለሻ መሣሪያዎች ወይም ማሽኖች

የሰው ማመላለሻ ማሽኖች ሥራ ላይ በሚውሉበት ወቅት፡-

1. በቂ ልምድና ክህሎት ያለው ባለሙያ የተመደበ መሆኑን፣
2. የሰው ማመላለሻ ማሽኖች ተገቢው ጥንካሬ እንዳላቸው ማረጋገጥ፣
3. የማንጠልጠያ ገመዶች ጥንካሬን በየወቅቱ መፈተሽ፣
4. ማሽኖቹ በሚንቀሳቀሱበት ወቅት እንቅስቃሴውን የሚያውክ ነገር አለመኖሩን፣
5. ለመሣሪያዎቹ በየወቅቱ ተገቢውን ጥገና ማድረግ፣
6. ከማመላለሻ ማሽኖቹ አቅም በላይ ሰው እንዳይጫን ጥንቃቄ ማድረግ፣
7. የማመላለሻ ማሽኖቹ እስከ 1.5 ሜትር ድረስ የተሸፈኑ መሆኑን፣
8. ማመላለሻ ማሽኖቹ በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሰሩ ከሆነ አማራጭ የኃይል ምንጭ መዘጋጀቱን ማረጋገጥ አለበት፡፡

## 40. የጣራ ሥራዎች

የጣራ ስራ ሲሰራ (ለመሥራት) ሊወሰዱ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች፡-

1. የጣራ ስራውን የሚሰሩ ሠራተኞች በአካል ብቁ የሆኑ፣ አስፈላጊው እውቀት እና ልምድ ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ፣
2. ከፍተኛ የንፋስ ፍጥነት እና ከባድ ዝናብ ባለበት የአየር ጠባይ ሁኔታ ውስጥ የሠራተኞች ደህንነት ስለማይጠበቅ የጣራ ሥራ ማስቆም፣
3. በጣሪያ ጠርዝ አካባቢ ለሚሰሩ ሠራተኞች የደህንነት ቀበቶ ወይም እሱን ሊተካ የሚችል የደህንነት መጠበቂያ መሣሪያ ማቅረብ እና ሠራተኞቹ እንዲጠቀሙ ማድረግ፣
4. ለጣሪያ መውጫ የሚጠቀሙበት መሰላል፣ መተላለፊያ መንገዶች አስተማማኝ መሆናቸውን እና በትክክል ከመዋቅሩ ጋር መያያዛቸውን ማረጋገጥ፣

5. ጉድለት ያለው የጣራ ሥራ ሲሰራ ብቁ እና አስተማማኝ የሆነ የመረማመጃ ጣውላ ወይም መሰላል ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ መዘጋጀቱን ማረጋገጥ፣
6. የሚሰበር የጣራ መዋቅር ያለው የግንባታ ሥራ ሲሰራ ቋሚ የሆኑ የአደጋ ማስጠንቀቂያ ፅሁፍ በጣሪያው አቅራቢያ መቀመጡን፣
7. የጣሪያ ክንፎች ከጣሪያው ግድለት (slope) የሚጣጣሙ ሆነው አስተማማኝ እና ጠንካራ በሆነ ድጋፍ መደገፋቸው መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

## 41. የኮንክሪት ማቀነባበሪያ (bulk mixing plant) ሥራዎች

የኮንክሪት ማቀነባበሪያ (bulk mixing plant) ሥራዎች ሲሰሩ (ለመሥራት) ሊወሰዱ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች፡-

1. በኮንክሪት ማቀነባበሪያ በቂ እውቀትና ልምድ ያለው ባለሙያ መመደብ፣
2. በኮንክሪት ማቀነባበሪያ ላይ ለሚመደቡ ሠራተኞች አደጋን ከመቀነስ አንፃር በቂ ሥልጠና መስጠት፣
3. ኮንክሪት ማቀነባበሪያውን ከተመደቡለት ባለሙያዎች ውጭ ማንም ሰው እንዳይነካ ጥንቃቄ ማድረግ፣
4. አንድ የኮንክሪት ማቀነባበሪያ ማሟላት ያለበትን መስፈርት አሟልቶ መገኘቱን ማረጋገጥ፣
5. ኮንክሪት ማቀነባበሪያ የተገነባበት ቦታ በቀላሉ ተደራሽ የሆነ እና አደጋዎችን ለመከላከል ምቹ መሆኑን ማረጋገጥ፣
6. የሚጠቀማቸው የኮንክሪት ማቀነባበሪያዎች ጥራታቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣
7. የኮንክሪት ማቀነባበሪያው ወቅቱን የጠበቀ ጥገና በትክክለኛ ባለሙያ ማድረግ አለበት፡፡

## 42. በግንባታ ግብዓት ማምረቻ ቦታዎች ላይ መደረግ ያለበት ጥንቃቄ

1. በግንባታ ግብዓት ማምረቻ ቦታ ላይ ለሚሰሩ ሰራተኞች እንደ ስራው ዓይነት ከላይ በግንባታ ቦታ ለሚሰሩ ሰራተኞች መደረግ ያለበት ጥንቃቄ በሙሉ መደረግ አለበት፡፡
2. የግብዓት ማምረቻ ቦታዎች የማምረት ተግባር በሚጠናቀቅበት ወቅት በአግባቡ ማስተካከልና የተቆፈሩ ጉድጓዶች ካሉ መልሰው በመድፈንና በደንብ በመጠቅጠቅ ለሚመለከተው ክፍል ማስረከብ ይኖርበታል፡፡

## 43. የጋራዥ ሥራዎችና መደረግ ያለባቸው ጥንቃቄዎች

በጋራዥ አከባቢና የጋራዥ ስራ በሚሰራበት ወቅት ሊወሰዱ የሚገቡ ጥንቃቄዎች፡-

1. የስራ አከባቢውን ከተቃጠለ ዘይት፣ ለስራ ከማያስፈልግ ግሪስ እና ሌሎች ሊያንሸራትቱ ከሚችሉ ቅባቶች ማፅዳት፣
3. ስለታማና ሹል የሆኑ ነገሮችን ከስራ ቦታው ላይ ማስወገድ፣
4. ለስራው የሚያስፈልገውን አለባበስና በኮርፖሬሽኑ የሚቀርቡ የአደጋ መከላከያዎችን በአግባቡ መጠቀም፣
5. በተቻለ መጠን የመትነን፣ የመሸተትና የመብነን ባህሪ ያላቸውን ኬሚካሎች መቀነስ ወይም መከላከያ መጠቀም፣
6. የሚጠገኑ ተሽከርካሪዎችና ማሽኖች ተስተካክለው የጥገና ቦታቸውን መያዛቸውን ማረጋገጥና የጥገና ስራው ከተጀመረ በኋላ እንዳይንሸራተቱ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ፣
7. የእሳት አደጋ እንዳይከሰት የቅድመ ጥንቃቄ ስራ መስራትና እሳት ሊያስነሱ የሚችሉ ስራዎችን ከነዳጅና ሌሎች ተቀጣጣይ ነገሮች ነጥሎ መስራት፣
8. ክብደት ያላቸውን ነገሮች እንዳስፈላጊነቱ በጋራ ወይም በማሽን ሀይል ማንቀሳቀስ፣
9. በብየዳ ወቅት የኤሌትሪክ አደጋ እንዳይፈጠር ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ፣

## 44. ተሽከርካሪዎችን፣ የግንባታ እና የማምረቻ መሣሪያዎችን ሰርቪስ ስለማድረግና ጥገና ስለማካሄድ

ተሽከርካሪዎችን፣ የግንባታ እና የማምረቻ መሣሪያዎችን ሰርቪስ እና ጥገና የሚሰሩ ሰራተኞች የሚከተሉትን ጥንቃቄዎች ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው፡፡

1. አላስፈላጊ የሆነ ንክኪን ማስወገድ፣
2. ደህንነቱ የተረጋገጠ የአሰራር ዘዴን መጠቀም፣
3. የሚቀርቡላቸውን ተገቢ የግል የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችንና አልባሳትን በአግባቡ መጠቀም፣
4. የግል ንጽህናን መጠበቅ፣
5. የስራ ቦታውንና የአካባቢውን ንፅህና መጠበቅና መከታተል፣

## 45. ሞተር ክፍል

1. ሞተር ክፍሎች (ሾፖች) ጭስ ለማውጣት የሚያስችል እና በቂ አየር ማስገባት የሚያስችሉ ሆነው ሊሰሩ ይገባል፡፡
2. ሞተር ክፍሎች በተጨማሪም በቂ የማናፈሻ ዘዴ/ቬንትሌተር እንዲኖራቸው ተደርጎ ሊሰሩ ይገባል፡፡

## 46. የፍሬን ፍተሻ

ሮሊንግሮድ መሳሪያ የሚያንቀሳቅሱ ሰራተኞች በስራው የሰለጠኑ እና በቂ ልምድ ያላቸው ሊሆን የሚገባ ከመሆኑም በተጨማሪ፡-

1. በስራው ላይ ጀማሪ ባለሙያዎች በቂ ስልጠና እና ልምድ እዲኖራቸው ማድረግ፡፡
2. መፈተሻ/መሞከሪያ መሳሪያዎች በአግባቡ ተስተካክለው መገጠማቸውንና በትክክል እየሰሩ መሆኑን ማረጋገጥ፣
3. በሚሽከረከረው ክፍል በኩል በቂና አስተማማኝ ከለላ እንዲኖር ማድረግ፣
4. ለሥራ በማያስፈልጉበት ወቅት በተለየ ክፍል ሽፍኖ ለብቻቸው በጥንቃቄ እንዲቀመጡ ማድረግ፣
5. ሥራ በሚከናወንበት ክፍል ውስጥ ሌሎች ጉዳዩ የማይመለከታቸው ሰዎች እንዳይገቡ መከልከል እና ይህንኑ የሚያመለክት የማስጠንቀቂያ ምልክት ማድረግ፣
6. ከጐማ ከሚወጡ ባዕድ ነገሮችና ከሚፈናጠሩ ጠጣር ነገሮች ራስን መጠበቅና መጠንቀቅ፣
7. የሥራ ክፍሉን የተለየ ማድረግና ሌሎች ሰዎችም በአካባቢው እንዳይደርሱ መከለል፣
8. የድምፅና የጭስ ልቀትን ከምንጩ መቆጣጠር፣

## 47. ፍሬንና ፍሪሲዮን ሰርቪስ ማድረግ

ከፍሬንና ከፍሪሲዮን የሚወጡ አቧራዎች እና ብናኞች ከፍተኛ የጉጅነት ባህሪና ኃይል ያላቸው በመሆኑ የሚከተሉትን ቅድመ ጥንቃቄዎች ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

1. በአቧራ/ብናኝ ማስወገጃ ንፋስ በመጠቀም ቆሻሻውን ወደ ከባቢ አየር አለመልቀቅ፣
2. አቧራው ወደ ከባቢ አየር በመግባት ጉዳት እንዳያስከትል ተገቢ የማጽጃ መሳሪያ (ወደ ውስጥ ስቦ በመያዝ የሚያፀዳ መሳሪያ (Vaccum Cleaner)) በመጠቀም ማጽዳትና በተገቢው መንገድ ማስወገድ፣

3. ድራሙን ለማጽዳት ርጥበታማ የማጽጃ መሳሪያ በመጠቀም ማጽዳትና ቆሻሻውን በኘላስቲክ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ዕቃ ውስጥ በማስቀመጥ በወቅቱ ከአካባቢ እንዲወገድ ማድረግ፣
4. የአስቤስቶስ ቆሻሻን ለማስወገድ የተቀመጡ ሀገር አቀፍና አለም አቀፍ ህግና ደንብን መከተል፣

## 48. ቦዲ መሙላትና ማስተካከል

ቦዲ የመሙላት እና የማስተካከል ስራን ለማከናወን ጥቅም ላይ የሚውሉ ግብአቶች ለጤና እና ለደህንነት አስጊ በመሆናቸው እስከተቻለ ዝቅተኛ የጉጅነት ባህሪ ያላቸውን ማቴሪያሎች መጠቀም፣ ካልተቻለ ደግሞ የሚከተሉትን ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡-

1. ለጉጅ ነገሮች ያለውን ተጋላጭነት ለመቀነስና ለመቆጣጠር በቂ ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ የማናፈሻ ዘዴዎችን/ቬንቲሌተር መጠቀም፣
2. የአደጋ መከላከያዎችን መጠቀም፣
3. በስራ ቦታ ለአቧራ፣ ብናኝና ጪስ የሚጋለጡ ሰራተኞችን ቁጥር መቀነስ፣
4. አቧራ መቀነስ የሚያስችሉ ዘዴዎችን መጠቀም፡፡ ለምሳሌ ቬንቲሌተር ወይም የጭስ፣ አቧራ፣ ብናኝ ማስወጫ (ስበው ወደ ውጭ የሚያስወግዱ) መሳሪያዎችን መግጠም፣
5. የሚያስጠነቅቁ፣ መረጃ የሚሰጡና የሚከለክሉ ምልክቶችና ጽሁፎችን በአካባቢው እንዲኖሩ ማደረግ፣
6. ለክፍሉ ሰራተኞች የሚሆን ራሱን የቻለ የልብስ መቀየሪያና የተሟላ መታጠቢያ ክፍል፣
7. የግል የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችን መጠቀም፣
   ሀ. የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል/Respirator፣
   ለ. የአይን ጉግል/መነጽር፣
   ሐ. የጆሮ ማፈኛ/ውታፍ /Ear muffs/Plugs፣
   መ. ቆዳ/ናይትራይን/ኘላስቲክ የእጅ ጓንት፣
   ሠ. ጋዋን፣
   ረ. የደህንነት ጫማ /Safety Shoes

## 49. የመኪና ቦዲን በአይሶሲያኔት/Isocyanates ቀለም በመርጨት/spraying መቀባት

የመኪና አካል/ቦዲ ቀለም መቀቢያ ክፍሎች የሚከተሉትን ሁኔታዎች ባሟላ እና በሚስማማ መልኩ መሰራት አለባቸው፡-

1. ትነት ወይም ብናኝ ወደ ውጭ ወይም ከባቢ አየር የማያስወጣ፣
2. ወደ ውጭ የሚወጣውን አየር በትክክል ማጣራት፣
3. ክፍሉ በሚፀዳበት ወቅት መገልገያ መሳሪያዎችን ጨምሮ ሁሌም/በወቅቱ በደንብ ማፅዳት፣
4. አይሶሲያኔት ያለባቸውን ቀለሞች በመጠቀም ምንም ዓይነት የማናፈሻ ዘዴ በሌለበት ሁኔታ በተዘጋ ክፍል ውስጥ አየር ማጣሪያ/መጋቢ መሳሪያ ሳይጠቀሙ መስራት ለጉዳት ያጋልጣል፣
5. በአይሶሲያኔት ቀለም ስንሰራ በቆየንበት አካባቢ ስራ ጨርሰናል ብለን የመከላከያ መሳሪያዎችን ማውለቅ አይገባም፡፡ ምክንያቱም አይሶሲያኔት ለረጅም ሰዓት በብዛት በአካባቢው ላይ ተሰራጭቶ ስለሚቆይ በተመሳሳይ ሁኔታ ጉዳት ሊያስከትልብን ስለሚችል ስለዚህ ወደ መልበሻ ክፍል ገብተን በአግባቡ የተጠቀምንበትን ልብስና መሳሪያ ማውለቅ አለብን፡፡

## 50. የመኪና ቀለም መበጥበጥ ወይም ማዋሃድ ወይም ማቀላቀል እና አቀማመጥ

የመኪና ቀለምና ማሟሙያ (ማቅጠኛ ወይም ማዋሃጂያ) ቀለሞች ከፍተኛ ጉዳት የማስከተል አቅም ስላላቸው የሚከተሉት ከፍተኛ ትኩረትና ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡-

1. ቀለም የሚቀላቀልበት/የሚዋሃድበት/የሚበጠበጥበት ክፍል እሳትን መቋቋም የሚችልና በቂ የማናፈሻ ዘዴ ያለው መሆን አለበት፣
2. የመኪና ሰውነት/ቦዲ ቀለምም ሆነ የቀለም ማቅለሚያ ኬሚካሎች ለአገልግሎት በማይፈልጉበት ጊዜ በትክክል ተከድነው ለእሳት አደጋ በማያስጉበትና በጤና ላይ ጠንቅ በማይፈጥሩበት ሁኔታ ጥሩ የማናፈሻ ዘዴ/ventilation system ባለበት ቦታና አካባቢ በጥንቃቄ መቀመጥ አለባቸው፣
3. ችግሩን ለመከላከል ከላይ የተጠቀሱትን ቅድመ ጥንቃቄዎች እንዲሁም የግል የአደጋ መከላከያ አልባሳትና መሳሪዎችን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

## 51. መስታወት የመግጠም ሥራ

የመኪና መስታወት የመግጠም ስራ የሚያከናውኑ ባለሙያዎች የሚከተሉትን የግል የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና አልባሳትን መጠቀም አለባቸው፡-

1. ሴፍቲ ጫማ/የደህንነት ጫማ/safety shoes፣
2. ረዥም እጅጌ ያለውና በስለታማ ነገሮች መቆረጥን የሚከላከል ጠንካራ ሸራ/ቆዳ የእጅ ጓንት፣
3. ጐግል/ የአይን መከላከያ መነጽር፣
4. ኬሚካል መቋቋም የሚችል የእጅ ጓንት፣

## 52. ብየዳ ክፍል

በብየዳ ስራ ላይ ለተሰማሩ ሰራተኞች የሚከተሉትን የመከላከያ መሳሪያዎች እና አልባሳት ማቅረብ አስፈላጊ ነው፡፡

1. ጠንካራ ኘላስቲክ ቆብ/ Helmets/፣
2. የጆሮ ውታፍ /Ear plugs/ ወይም የጆሮ ማፈኛ /Ear Muffs/፣
3. የአይን መነጽር ወይም ጐግል፣
4. በእጅ የሚያዝ የፊትና የአይን መከላከያ ከለላ /Face shield ወይም ከባርኔጣ/ቆብ/ Helmets ጋር አብሮ የተሰራ ከለላ፣
5. የደህንነት ጫማ (Safety shoes)፣
6. ቱታ ወይም ጋዋን፣
7. ከቆዳ የተሰሩ የእጅ ጓንቶችን /Welding Gloves/፣
8. ከቆዳ የተሰራ ሙሉ ሽርጥ /Leather aprons/፣እና
9. ከቆዳ የተሰራ የእግር /ቅልጥም መከላከያ ገንባሌ ተጠቃሽ ምሳሌዎች ናቸው፡፡
10. እነዚህ መሳሪያዎችና አልባሳት በቀላሉ በእሳት ተቀጣጥለው ለከፋ አደጋና ጉዳት እንዳይዳርጉ ከዘይት፣ ከነዳጅ፣ ከግሪስና መሰል ተቀጣጣይ ንጥረ ነገሮች የፀዱ ማድረግ፣ ቱታ ወይም ጋዋን እጅጌያቸው ሙሉ/ረዥም የሆነ፣ ሽርጡም ቆዳ ሆኖ ሙሉ የፊት ለፊት ሰውነትንና ደረትን መሸፈን የሚችል እና ሰውነትን የማያጨናንቁ /ጥብቅ የማያደርጉ ለስራ ምቹ መሆን ይገባቸዋል፡፡
11. በተለይ ቱታ በሚለበስበት ወቅት በእግር ጫማ ውስጥ መከተት የለበትም፣ ከጫማው በላይ መለበስ አለበት፡፡

12.በምንጠቀማቸው መከላከያ ልብሶች ኪስ ውስጥ በቀላሉ ሊቀጣጠሉ፣ ሊቀልጡ ፣በቀላሉ ከሰውነት ጋር ሊጣበቁ የሚችሉና እሳት ሊያስነሱ የሚችሉ እንደ ክብሪት፣ የሲጋራ ማቀጣጠያ ላይተር/Lighters እና መሰል ነገሮች መቀመጥ የለባቸውም፡፡

## 53. የሬዲዮ፣ ኮምፒዩተር እና የመሳሰሉት ብየዳ ስራ ጋር የተያያዙ የጤና እና የደህንነት ጉዳዮች

ሊድን/እርሳስን (Lead) በመጠቀም ብረት በሚበየድበት ወይም በሚቆረጥበት ወቅት የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ ይቻል ዘንድ የሚከተሉትን የቅድመ ጥንቃቄ ዘዴዎች ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡

1. ስራው በሚከናወንበት አካባቢ በምንም ዓይነት ሁኔታ ምግብ መመገብ፣ ውሃ መጠጣት፣ ሲጋራ ማጨስ ወይም ማስቲካ ማኘክ እንዲሁም ምግብን ማስቀመጥ ተገቢ አይደለም፣
2. ስራ እንደጨረሱ እጅን በሳሙና እና በወራጅ ውሃ በደንብ መታጠብና በጥፍር ውስጥ የእርሳስ ቅሪት አለመኖሩን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፣
3. መከላከያ አልባሳትንና መሳሪያዎችን በዚያው በስራ ቦታ ቀይሮ ለብቻ ማስቀመጥና ንፅህናቸውን ጠብቆ መጠቀም፣
4. ክፍሉ በቂና ተገቢ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ የማናፈሻ ዘዴ እንዲኖረው ማድረግ፣
5. የስራ ቦታን በውሃ በማርጠብ በአየር ማፅጃ (ወደ ውስጥ ስቦ በሚያፀዳ /vaccum cleaner) ማፅዳት፣
6. ከክፍሉ የሚወጣውን ተረፈ ምርትና ቆሻሻ ለብቻው በማስቀመጥ በአግባቡና በወቅቱ ማስወገድ፣
7. የሚከተሉትን የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና አልባሳት መጠቀም
   - ሀ/ የፊት መከላከያ ያለው ኘላስቲክ ባርኔጣ /helmet/፣
   - ለ/ የአይን ጉግል፣
   - ሐ/ የቆዳ ጓንት፣
   - መ/ የደህንነት ጫማ /Safety shoes/፣
   - ሠ/ ሙሉ የቆዳ ሽርጥ /Leather apron/ፊት ለፊት ያለውን የሰውነት ክፍል ሙሉ ለሙሉ የሚሸፍን፣
   - ረ/ ረጅም እጅጌ ያለው ቱታ/ጋዋን፣
   - ሰ/ የጆሮ ውታፍ /ear plug/ ወይም የጆሮ ማፈኛ /ear muff/፣
   - ሸ/ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል /respirator/ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

## 54. ጐማ ክፍል

1. ጐማ ከቦታ ቦታ ለማንቀሳቀስ አጋዥ መሳሪያዎችን ለምሳሌ እንደ ጋሪ የሚገፉ መሳሪያዎችን /trolly/፣ የዕቃ ማውረጃና መጫኛ ተሽከርካሪ /Forklift/ መጠቀም ፡፡
2. አየር የሚያሞቀው መሣሪያ Air Compressor የአየር መያዣውን በየዓመቱ ግፊት ፍተሻ ሊደረግለት ይገባል፡፡
3. በንፋስ/በግፊት የማጽጃ መሳሪያ ተጠቅመን በምንሰራበት ወቅት ከጐማው ጋር የተጣበቁ እንደ ሚስማር ያሉ ብረትና ባዕድ ነገሮች ተፈናጥረው አደጋ/ጉዳት ሊያስከትሉ ስለሚችሉ መከላከያ መሳሪያዎችን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ ሌላ ሰው ላይም ችግር እንዳይፈጥር በቂ የማናፈሻ ዘዴ ባለው ክፍል ውስጥ ስራው መከናወን አለበት፣
4. አቧራ/ብናኝ ለማስወገድ ወደ ውስጥ ስቦ የሚያስቀር/Vaccum Cleaner/ መሳሪያ መጠቀም፣
5. በአየር ግፊት/Air pressure/ በሚሰራ መሳሪያ ተጠቅመን በምናፀዳበት ጊዜ ከጐማው ላይ የተበጣጠሱ ትንንሽ ጐማዎችና ባዕድ ነገሮች አይን ላይ ከፍተኛ ጉዳት/አደጋ ሊያስከትሉ ስለሚችሉ የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችንና አልባሳትን በአግባቡ መጠቀም ያስፈልጋል፣
6. በጽዳት ወቅት የጐማ ብናኝ፣ አቧራ፣ ትነትና ሽታ ስለሚፈጠር የስራ ክፍሉ በቂ ተፈጥሯዊም ሆነ ሰው ሰራሽ የማናፈሻ ዘዴ ሊኖረው ይገባል፡፡
7. የሚከተሉትን የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና አልባሳት መጠቀም ያስፈልጋል፡-
   - ሀ/ ጉግል/የአይን መከላከያ መነጽር፣
   - ለ/ ኘላስቲክ/ቆዳ የእጅ ጓንት፣
   - ሐ/ የጭንቅላት መከላከያ ጠንካራ ኘላስቲክ ቆብ/ሔልሜት፣
   - መ/ የድምጽ መከላከያ የጆሮ ውታፍ/ማፈኛ /Ear plugs/muff፣
   - ሠ/ የደህንነት መጠበቂያ ጫማ/safety shoes፣
   - ረ/ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል/ማስክ፣

## 55. ባትሪ ክፍል

ከባትሪ ስራ ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ የጤና እና የደህንነት ጠንቆች ለመከላከል መደረግ ያለባቸው ጥንቃቄዎች፡-

1. የስራ አካባቢው በቂና ተገቢ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ብርሃንና የማናፈሻ ዘዴ እንዲኖረው ማድረግ፣
2. የቤቱን/የስራ ክፍሉን ንፅህና በሚገባ በመጠበቅ በየዕለቱ መከታተልና ቁጥጥር ማድረግ፣
3. ሰራተኞች የግል ንፅህናቸውን መጠበቅ እንዲችሉ አስፈላጊ ነገሮችን ማሟላት (የመታጠቢያ ሻወር፣ ሳሙና፣ ፎጣና የመሳሰሉትን መሰረታዊ ነገሮች)፣
4. የተለያዩ ብረት ነክ የሆኑ እንደ ሰዓት፣ ቀለበት፣ የአንገት ሀብልና ጌጣጌጦችን በስራ ጊዜ አለመጠቀም፣
5. ማንኛውም ሰራተኛ ከስራው ጋር ተያይዞ ሊገጥመው የሚችለውን የደህንነትና የጤና ችግር አውቆ እንዲጠነቀቅ ማድረግ፣
6. የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና መስጫ መሳሪያዎች በክፍሉ እንዲኖሩ ማድረግ፣
7. በሥራ አከባቢው አገልግሎት መስጠት የሚችሉ የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሣሪያዎች እንዲኖሩ ማድረግ፣
8. የአሲድ መፍሰስ ሊከሰት ስለሚችል በቂ ነጹህ ውኃ ወይም የማያቋርጥ የውኃ መስመር እንዲኖር ማድረግ፣
9. የሚያስተምሩ፣ የሚያስጠነቅቁና የሚከለክሉ ምልክቶችና ጽሑፎች እንዲኖሩ ማድረግ፣
10. ተገቢና በቂ የግል የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችንና አልባሳትን መጠቀም፡-
    ሀ. የፊት መሸፈኛ /face shield/፣
    ለ. የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል/የአሲድና ቤዝ ትነትን የሚከላከል፣
    ሐ. አሲድን መቋቋም የሚችል ሙሉ ሽርጥ/apron/፣
    መ. የደህንነት ጫማ /Safety shoes/፣(አሲድን መቋቋም የሚችል ፕላስትክ ጫማ)
    ሠ. ሙሉ እጅጌ ያለው ቱታ/ጋዋን፣
    ረ. የአይን መከላከያ ጉግል፣
    ሸ. የራስ መከላከያ ጠንካራ ፕላስቲክ ሄልሜት፣
    ቀ. ፕላስቲክ የእጅ ጓንት፣

## 56. ተንቀሳቃሽ የጥገና ሥራ /Mobile Maintenance/

በተንቀሳቃሽ የጥገና ስራ ላይ የተሰማሩ ሰራተኞች ጋር በተያያዘ ሊወሰድ ስለሚገባው የቅድመ ጥንቃቄ/መከላከያ ዘዴዎች፡-

1. የሚጠገነው ተሽከርካሪ ወይም የግንባታ መሣሪያ የቆመበትን አካባቢ በደንብ ማጥናትና አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ፣
2. አካባቢው ለስራም ሆነ ለጤና አስቸጋሪና አስጊ ከሆነ ወደ ሌላ የተሻለ የሥራ አካባቢ መቀየር፣
3. የማስጠንቀቂያ ምልክቶችን በቅርብ ርቀት ማስቀመጥ፣
4. የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና መስጫ መሳሪያ /first aid kit፣
5. የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሣሪያ፣
6. በቅርብ ርቀት የሚከታተልና በአደጋ ጊዜ ሊደርስ የሚችል ሰው በሥራ አካባቢው እንዲኖር ማድረግ፣
7. የግል የአደጋ መከለከያ መሳሪያዎችን መጠቀም፡-
   ሀ. ከሥራ አካባቢው የአየር ፀባይ ጋር ተስማሚ የሆነ /weather proof/ ልብስ መልበስ፣
   ለ. የደህንነት ጫማ/Safety Shoe፣
   ሐ. ኘላስቲክና ቆዳ የእጅ ጓንት፣
   መ. የዝናብ ልብስ፣
   ሠ. ጠንካራ ኘላስቲክ ቆብ/ባርኔጣ/ሔልሜት፣
   ረ. የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል ማስክ፣

## 57. የተሽከርካሪ ማጠቢያ ክፍል

ከተሽከርካሪ እጥበት ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ ችግሮችን ለመከላከልና ጉዳቱን ለመቀነስ የሚከተሉትን የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና አልባሳትን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

1. የራስ መከላከያ ኘላስቲክ ቆብ/ሄልሜት፣
2. ውሃ መቋቋም የሚችል ሙሉ ቱታ/ሸርጥ፣
3. የላስቲክና የቆዳ ጓንት (ረዥምም እጅጌ ያለው ንዝረትን መቋቋም የሚችል)፣
4. ጉግል/የአይን መከላከያ መነጽር፣
5. የአፍና የአፍንጫ መከላከያ ጭምብል/ማስክ፣
6. የደህንነት ጫማ/safety shoes፣
7. የድምጽ መከላከያ የጆሮ ማፈኛ/ውታፍ /ear muff/plug፣

## 58. የጠጠር መፍጫ (Stone crushers) የሥራ ቦታ

በጠጠር መፍጫ የስራ ቦታዎች ላይ፡-

1. ለሠራተኞች ተገቢ የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችንና አልባሳትን ማቅረብና ሰራተኞቹም እንዲለብሱ ማድረግ፡፡
2. አስተዳደራዊ የመቆጣጠሪያ ዘዴዎችን፣ የሥራ መቀየርንና የፈረቃ ሥራን ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## 59. ከአስፋልት ስራ ጋር የተያያዙ የጤና እና የደህንነት ጉዳዮችን በሚመለከት

ከአስፋልት ስራ ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ በርካታ የጤና ጠንቆች፣ የደህንነት ችግሮችና ጉዳቶች ለመከላከል፡-

1. የተለያዩ የቅድመ ጥንቃቄና የደህንነት መርሆችን ተግባራዊ ማድረግና ተገቢ የግል የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡
2. አስፋልት ስራ ላይ የተሰማሩ ሰራተኞችን ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች ለመከላከል የግል የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችንና አልባሳትን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

## 60. ከፈንጅ (BLASTING) ሥራ ጋር የተያያዙ የጤና እና የደህንነት ጉዳዮች

የፈንጅ አጠቃቀምና ሊወሰዱ የሚገባቸው የጥንቃቄ እርምጃዎች፡-

1. የፈንጂ አቀማመጥ፣ አያያዝና አጠቃቀም በከፍተኛ ጥንቃቄ መሆን አለበት፣
2. የፍንዳታ አካባቢዎችን በጥንቃቄ መጠበቅ፣
3. የማፈንጃ መጠለያ/ወይም ከለላ መስራት ያስፈልጋል፣
4. የፍንዳታ ቅደም ተከተላዊ አካሄድን መከተል ይገባል፣
5. በፍንዳታ ለሚደርሱ ጉዳቶችና አደጋዎች የሚወሰድ እርምጃ፡-

   ሀ. ፈንጅ የሚቀበርበትን አካባቢ በትክክል ማወቅና በሚገባ መከለል፣

   ለ. በአካባቢው ምንም ዓይነት ነገር እንዳይኖር ማድረግ፣

   ሐ. ፍንዳታውን በትክክል መቆጣጠር የሚያስችል ሁኔታ መፍጠር፣

   መ. በቂና ተገቢ የማፈንጃ መጠለያ መስራት፣

   ሠ. በቂ የመረጃ ልውውጥና የግንኙነት መረብ እንዲኖር ማድረግ፣

   ረ. በቂና ተገቢ ስልጠናዎችን መስጠት፣

## 61. የፍንዳታ ቦታ

የማፈንጃ ቦታንና አካባቢን አደጋ/ጉዳት በማያስከትልና የሚፈለገውን ውጤት ብቻ ማስገኘት በሚያስችል ቦታ ላይ ለመምረጥ የሚከተሉት ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ መግባት ይኖርባቸዋል፡-

1. የመሬቱ ተፈጥሮ ወይም የማዕድን ይዘቱ፣
2. የፍንዳታ ንድፍ፣
3. የጉድጓድ ጥልቀት፣ ስፋትና ማዕዘን፣ የሚያርፍበት ጭነት አይነት፣
4. የመሬቱ የፍንዳታ ባህሪይ፣
5. የቆይታ ዘዴ፣
6. የፈንጅው አይነት፣ መጠን እና የፈንጅው አንጓ አይነትና ብዛት፣

## 62. የማፈንጃ አካባቢ ጥበቃ

በማፈንጃ ቦታው አካባቢ መደረግ ካለባቸው ዋና ዋና የጥንቃቄ ተግባራት መካከል፡-

1. የሚበሩ ወይም የሚፈናጠሩ ድንጋይና ባዕድ ነገሮች ተፈናጥረው ወይም በርረው ሊደርሱ የሚችሉበትን ርቀትና ፍንዳታውን ከተጠበቀው በላይ ሊያባብሱ የሚችሉ ሁኔታዎችን አስቀድሞ መገመት፣
2. በሥራ አካባቢው የሚገኙ ሁሉንም ሰራተኞች፣ የስራ ተቆጣጣሪዎችንና ጉብኝዎችን ከሥራ አካባቢው እንዲርቁ ማድረግ፣
3. መረጃ የሚሰጡ፣ የሚያስጠነቅቁና የሚከለክሉ ምልክቶችንና ጽሁፎችን በሥራ አካባቢው መትከል፣
4. ፍንዳታውን ለሚያከናውነው ባለሙያ በቂ የማፈንጃ መጠለያ ቦታ መስራት፣
5. ፍንዳታውን የሚያከናውነው ባለሙያ የሚጠቀመው ፈንጅ እስከምን ያህል ርቀት ድረስ አደጋና ጉዳት ሊያስከትል እንደሚችል ማወቅና የፍንዳታ ክልሉን ርቀት መወሰንና መከለል ይኖርበታል፡፡
6. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የቅርብ ግንኙነትና በቂ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር ማድረግ፣

## 63. ከፍንዳታ ቦታ ሰራተኞችን ስለማሸሽ

1. ፍንዳታ በሚከናወንበት አካባቢ ለስራ የተሰማሩ ሰራተኞች ካሉ እንዲሁም በፍንዳታው ሊጐዱና ሊወድሙ የሚችሉ ንብረቶች ካሉ በሙሉ ከአካባቢው ማሸሽ/ማራቅ ያስፈልጋል፡፡
2. ከፍንዳታ አካባቢ ሰራተኞችን በወቅቱ ለማሸሽና ከአደጋ ለመጠበቅ ኃላፊነቱን የሚወስድ አካል ኮርፖሬሽኑ ይመድባል፡፡
3. ፍንዳታ ከመፈፀሙ በፊት ሰራተኞች ከአካባቢው ተጠቃለው መውጣታቸውንና ከፍንዳታ ክልሉ መራቃቸውን የሚያሳውቅ ምልክት ወይም ደወል መኖር አለበት፡፡
4. በፍንዳታ ጊዜ ተመልሶ ወደ ፍንዳታ ክልሉ የሚገባ ሰራተኛና ለመውጣት የዘገየ ሰራተኛ እንዳይኖር ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ አለበት

## 64. በፈንጅ ስራ ላይ ተግባራዊ መደረግ የሚገባቸው የደህንነት ጉዳዮች

1. የፈንጅ ክትትልና ቁጥጥር ባለሙያ ሁሉንም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የፍንዳታ ስራዎችን (ማጓጓዝ፣ አያያዝ፣ አቀማመጥ እና አጠቃቀም) ጠንቅቆ ማወቅና በጥንቃቄ ማከናወን ይኖርበታል፡፡
2. ማንኛውም የስራ ክፍል በስራው ላይ ፈንጅን እንደ አንድ ግብዓት የሚጠቀም ከሆነ በስራ ክፍሉ ስትራቴጂካዊና አመታዊ እንዲሁም ዕለታዊ ዕቅድ ውስጥ በማካተት የፍንዳታ ዝርዝር የአፈፃፀም መርሃ ግብርና የትግበራ ማኑዋል ሊኖረው ይገባል፡፡
3. ዕቅዱ በዋናነት የሚከተሉትን መረጃዎች ማካተት አለበት፡-
   ሀ. የማጓጓዣ ዘዴውንና የማጓጓዣ መሳሪያውን (የፈንጅውንና የማፈንጃውን)፣
   ለ. የማከማቻ/ማስቀመጫ ቦታውን አይነት፣ ያለበትን አካባቢና አመችነት፣
   ሐ. የፈንጅውንና የማፈንጃውን አይነትና ብዛት፣
   መ. የሰራተኞች የግንዛቤ ስልጠና መርሃ ግብር፣
   ሠ. የሰራተኞችን ህይወትና ንብረትን ከአደጋና ከጉዳት መከላከያ መሳሪያዎችንና አልባሳትን አይነትና ብዛት መለየትና ማቅረቢያ ጊዜን፣
   ረ. ፈንጅ የሚቀበርበትን ጉድጓድ ስፋት፣ የሚያርፍበትን ክብደት፣ የቆይታ ጊዜውንና ሌሎችን አስፈላጊ መረጃዎችን የያዘ የዕለት የፍንዳታ ዕቅድን ለሚመለከታቸው አካላት መስጠትና ማሳወቅ፣

ሰ. የፈንጅ አወጋገድና ተያያዥ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ዝርዝር ጉዳዮችንና ማኑዋሎችን ለሚመለከታቸው አካላት መስጠትና ማሳወቅ፡፡

## 65. የፈንጅዎች ቆጠራና ጥበቃ

1. ፍንዳታ ከመከናወኑ በፊት ፍንዳታውን የሚያከናውነው ባለሙያና ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ስለ ደህንነት አጠባበቅ እና መወሰድ ስለሚገባቸው ቅድመ ጥንቃቄ ዘዴዎች ፍንዳታው ከመካሄዱ ቢያንስ ከ24 ሰዓት በፊት መታወቅ ይኖርበታል፡፡
2. የፈንጅ መሳሪያዎች በተቀመጡበት፣ በሚጓጓዙበትና አገልግሎት በሚሰጡበት አካባቢ እሳትን ሊያስነሱ ወይም ሊፈጥሩ የሚችሉ እንደ ሲጋራ ማጨስ፣ ከብሪት ወይም የኤሌክትሪክ ምድጃና የመሳሰሉት የእሳት አደጋና ተያያዥ ጉዳቶችን እንዳያደርሱ በአካባቢው እንዳይኖሩ ወይም እንዳይከናወኑ በጥብቅ መከልከል አለበት፡፡
3. ፈንጅዎች በሚቀመጡበት መጋዘን ቤት አካባቢ እና ፈንጅዎችን ጭኖ በሚያጓጉዘው መኪና ላይ በቂና ተገቢ ምልክቶችንና ማስጠንቀቂያ ጽሁፎችን መትከል ወይም መለጠፍ እንዲሁም በ31 ሜትር ርቀት ላይ ሲጋራ ማጨስና ሌሎች እሳት ሊያስነሱ የሚችሉ አቀጣጣይ ነገሮችን መያዝም ሆነ መጠቀም እንደማይገባ መከልከልና ሊያስቀጣ እንደሚችልም ማሳወቅ ያስፈልጋል፡፡
4. በዝናብ ወቅት ወይም የመብረቅና የሰማይ ጉርምርምታ በሚኖርበት ጊዜ ፈንጅዎችን ከመጠቀም መቆጠብ ይገባል፡፡
5. ባልታወቀ ሁኔታ ወይም አጋጣሚ እንዲህ አይነቱ ስህተት ከተፈጠረ ሁሉም ሰራተኞች በፍጥነት አካባቢውን ለቀው እንዲወጡና ደህንነቱ ወደ ተጠበቀ አካባቢ እንዲሸሹ ማድረግ ይገባል፡፡
6. ፈንጅዎችን ሙያው በሚፈቅደው ዲስፕሊን መሰረት በጥንቃቄ መያዝ፣
7. ከስርቆት መጠበቅ፣ የጠፋ ፈንጅ ካለ ወዲያውኑ ለሚመለከተው አካል በማሳወቅ አስቸኳይ መፍትሄ እንዲሰጠው ማድረግ፣
8. በስራ ቦታ የተከማቹ ፈንጅዎችን በየወቅቱ መቁጠርና በትክክል መዝግቦ መያዝ፣

## 66. በፍንዳታ ጊዜ ሊያጋጥም የሚችል አደጋንና ጉዳትን መከላከልና መቆጣጠር

1. ፍንዳታ ወደ ሚካሄድበት አካባቢ የሚወስዱ መንገዶች ላይ እና በቅርብ ርቀት ባሉ ቦታዎች ላይ የተለያዩ የሚያስጠነቅቁና የሚከለክሉ ምልክቶችንና መረጃ የሚሰጡ ጽሁፎችን በግልፅና በበቂ ሁኔታ መታየት በሚችሉበት ቦታ ላይ መትከል ወይም መለጠፍ ያስፈልጋል፡፡
2. በፍንዳታ ወቅት ከሚከሰቱ የድንጋይና ሌሎች ጠጣር ነገሮች ፍንጣሪዎች ራስን ከጉዳትና ከአደጋ ለመከላከል መከላከያ ምንጣፍ /Blasting mats/ መጠቀም ይገባል፡፡

## 67. በድንጋይ ማምረቻ ካባዎችና በጠጠር ማምረቻ ወፍጮዎች አካባቢ ሊደረጉ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች

1. ድንጋይ ለማምረት የሚከናወነው ስርሠራ በማቴሪያል ኘሮዳክሽን የአሰራር ስርአት መሠረት የስርሠራ አቅጣጫዎች፣ ባንድ ፍንዳታ እንዲገኝ የሚፈለገውን የድንጋይ ብዛትና የወረደውን ድንጋይ ለማንሳት በሚያመች መልክ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡
2. የድንጋይ ስርሠራ ስራ በእያንዳንዱ ቀዳዳ ስፋት፣ ጥልቀት፣ ርቀትና ጥቅም ላይ ከሚውለው የፈንጂ ባህርይና መጠን ጋር በማጣጣም ሳይንሳዊ ስሌትን መሰረት በማድረግ በቂ ሙያዊ ዕውቀት ባለው ሰራተኛ መከናወን አለበት፡፡
3. የድንጋይ ስርሠራ ክንውን ሲጀመር በቀጣይነት የስርሠራና የማምረት ስራው ሊቀጥል የሚችልበትን ምቹ አቅጣጫ ሊይዝ ይገባል፣
4. የድንጋይ ስርሠራው ስራ በጉድጓድ ጥልቀት ስፋትና በእያንዳንዱ መካከል ሊኖር የሚገባው ርቀት ላይ ተመስርቶ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ መከናወን ይኖርበታል፣
5. በድንጋይ መሰርሰሪያ መሳሪያ ላይ የሚሰሩ ባለሙያዎች ስለሚሰሩት ስራና ሊያጋጥማቸው ስለሚችለው አደጋ በቂ ዕውቀት እንዲኖራቸው ማድረግና ጥንቃቄ እንዲያደርጉ እገዛ ይደረግላቸዋል፡፡
6. የተሰረሰሩ የፈንጂ ማስቀመጫ ቀዳዳዎች ጥቅም ላይ እስኪውሉ ድረስ ውሃና አፈር እንዳይገባባቸው በአግባቡ ሊሸፈኑና ሊከደኑ ይገባል፣
7. በእያንዳንዱ ቀዳዳ ጥቅም ላይ የሚውለው ፈንጅ በጉድጓዶቹ ርቀት ተመስርቶ እንዲመረትና እንዲወርድ የሚፈለገው መጠንና አቅጣጫ ያገናዘበ መሆን ስለሚገባው ለፌሲንግ ስራ ልዩ ትኩረት ይሰጣል፡፡

8. የተዘጋጀውን ጉድጓድ በፈንጂ የመሙላት ስራ በሚከናወንበት ወቅት የድንጋይ ማምረቻውን አካባቢ ሙሉ በሙሉ በመቆጣጠር እንስሳት እና የአካባቢው ህብረተሰብ ወደ ሥራ አካባቢው እንዳይገቡ መደረግ አለበት፡፡
9. በካባው ስራ ላይ የሚገኙ መሳሪያዎች ተገቢውን ከለላ ሊያገኙ ወደ ሚችሉበት አካባቢ በማስጠጋትና በማራቅ አካባቢው ሙሉ በሙሉ ነፃ መሆኑ ከተረጋገጠ በኂላ ፍንዳታውን ማከናወን፣ በፍንዳታ ወቅት ጥቅም ላይ እንዲውሉ የተዘጋጁ የማቀጣጠያ ካፕሶች የት እንዳሉ በማስታወስ የከሸፈ ካለ በማቀጣጠያ ሽቦ አማካይነት ፍተሻ ማከናወንና ያልፈነዱ ማቀጣጠያዎች ድንጋይ ለመሰብሰብ የሚሰሩ መሳሪያዎች ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ በቅድሚያ መፈተሽ፣
10. ድንጋይ ማምረቻ ካባዎች አገልግሎት ከሰጡ በኂላ የውኃ ማቆሪያና ማጠራቀሚያ ሆነው በአካባቢው ህብረተሰብ ላይ ለጤና ጠንቅ ምክንያት እንዳይሆኑ መልሶ ማስተካከል፣
11. በካባና በወፍጮ አካባቢ የሚሰሩ ሰራተኞች የደህንነት መጠበቂያና የአደጋ መከላከያ አልባሳትንና መሳሪያዎችን እንዲጠቀሙ ማድረግ፣

## 68. ከኤሌክትሪክ ሥራ ጋር የተያያዙ የደህንነትና የጤና ጉዳዮች

1. የኤሌክትሪክ አስተላላፊ መሳሪያዎች የተቀመጡ ህግና ደንቦች እንደዚሁም ስታንዳርዶችን የሚያሟሉ መሆን አለባቸው፡፡
2. ኤሌክትሪክ አስተላላፊ መሳሪያዎች ከአቅም በላይ በመስራት ፍንዳታ እንዳያስከትሉ ክትትል ይደረጋል፡፡
3. የኤሌክትሪክ መስመሮች በሚዘረጉበትና በሚጠገኑበት ወቅት አስተላላፊ መሳሪያዎቹ የተቀመጠው ህግ፣ ደንብና ስታንደርድ የሚያሟሉ መሆናቸው በባለሙያ መረጋገጥ አለበት፡፡

## 69. ከነዳጅ ማደያ ሥራ ጋር የተያያዙ የደህንነትና የጤና ጉዳዮች

1. የነዳጅ ማደያውን ራሱን እንዲችል ተደርጎ ሰው፣ ተሽከርካሪ እና ንብረት በማይበዛበት አካባቢ ደረጃውን ጠብቆ መገንባት፣

2. በቂ ጣሪያና ከለላ እንዲኖረው ማድረግ፣
3. ዙሪያውን በማጠር ቋሚ ጠባቂና የዕለት ተዕለት ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግ አካል መመደብ፣
4. በአካባቢው የሚከለክሉ፣ የሚያስጠነቅቁና ትምህርት/መረጃ የሚሰጡ ጽሁፎችና ምልክቶች በበቂ ሁኔታ ሁሉም ሰው ሊያየው በሚችልበት አካባቢ ሁሉ እንዲኖሩ ማድረግ፣
5. የነዳጅ ማደያው ግቢ በአስፋልት ወይም በስሚንቶ እንዲሰራ ማድረግ፣
6. በነዳጅ ማደያው ግቢ ውስጥ የድንገተኛ እሳት አደጋ መከላከያ በአሸዋ የተሞሉ ጉርድ በርሜሎች ከአካፋ ጋር እና የጅምር እሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች/Fire extinguishers ማስቀመጥና የክፍሉ ሰራተኞች ስለ አጠቃቀሙ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ፣
7. ነዳጅ በሚሞላበትና በሚቀዳበት ወቅት መደረግ ያለበትን ጥንቃቄ ተግባራዊ ማድረግ፣
8. ለሰራተኞች የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና አልባሳት ማቅረብና እንዲጠቀሙ ማድረግ፣

## 70. ከምሽት ፈረቃ ወይም ትርፍ ሰዓት ሥራ ጋር የተያያዙ የደህንነትና የጤና ጉዳዮች

1. የሥራ አካባቢውን የሚያሳዩ ከፍተኛ አቅም ያላቸው (ፖውዛ) በቂ መብራቶች በአንፀባራቂ ምልክቶች የታገዙ መሆን አለባቸው፣
2. ህዝብ በሚበዛባቸው የሥራ አካባቢዎች የሚከናወኑ ተግባራት በአካባቢው ህብረተሰብ ላይ የድምፅ ብክለትን ለመቀነስ ጥረት መደረግ አለበት፣
3. በሰራተኞች ላይ አደጋና ጉዳት እንዳይደርስ ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ያስፈጋል፡፡
4. የግድ የምሽት ሥራ የሚካሄድ ከሆነ ከአካባቢው ማህበረሰብና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር በቅድሚያ እንዲያውቁት መደረግ አለበት፣

## 71. ከከፍታ ቦታ ላይ ከሚሰሩ ሥራዎች ጋር የተያያዙ የደህንነትና ጤና ጉዳዮች

1. በከፍታ ቦታ ላይ ሊያሰሩ የሚችሉ ሁኔታዎችን መቀነስ፣

2. ከከፍታ ቦታ ላይ ሆኖ ለመስራት የሚያስችሉ መሳሪያዎች ተገቢ መሆናቸውንና ለአደጋ የማያጋልጡ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣
3. በማንኛውም ሁኔታ በጥንቃቄ ጉድለት አደጋ ቢከሰት ለከፋ ጉዳት የሚዳርግ ሁኔታ በስራ አካባቢው አለመኖሩን ማረጋገጥ ካለም ከአካባቢው ማራቅ ወይም ማፅዳት፣
4. ስራው በሚከናወንበት ጊዜ ሁኔታውን የሚከታተል ሰው እንዲኖር ማድረግ/ብቻን አንድ ሰው ብቻውን አለመስራት ወይም እንዲሰራ አለማድረግ፣
5. አደጋው ቢከሰት ጉዳቱን ሊቀንሱ የሚችሉ የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችንና አልባሳትን መጠቀም፣

## 72. ከዕቃ ግምጃ ቤት ሥራ ጋር የተያያዙ የደህንነትና ጤና ጉዳዮች

በዕቃ ግምጃ ቤት አካባቢ የሚፈጠሩ አደጋዎችን ለመከላከልና ለመቀነስ ቀጥሎ የተመለከቱት የጥንቃቄ ርምጃዎች ይወሰዳሉ፡-

1. በዕቃ ግምጃ ቤቱ አካባቢ ለአደጋ ሊያጋልጡ የሚችሉ ሁኔታዎች አለመኖራቸውን ማረጋገጥ፣
2. የአደጋ ስጋቶችን ማስወገድ ወይም መቀነስ የሚቻልባቸውን ዘዴዎች መቀየስ፣
3. የቁጥጥርና የክትትል ስርዓት መዘርጋት፣
4. ሰራተኞች በዕቃ ግምጃ ቤቱና በግምጃ ቤቱ ውስጥ ስላሉ ዕቃዎች በቂ ግንዛቤና እውቀት እንዲኖራቸው ማድረግ፣
5. አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ነገሮችን በሌላ መተካት ወይም መቀየር፣
6. ችግሩን ወይም ጉዳቱን የሚያባብሱ ነገሮችን መቆጣጠር ወይም ማቃለል፣
7. ለአደጋ የተጋለጡ የእቃ ግምጃ ቤት ክፍሎችንና የስራ ክፍሎችን መለየትና መቆጣጠር፣
8. ዕቃ ግምጃ ቤቶችን ለአደጋ በማያሰጉና የከፋ ጉዳት በማያስከትሉበት የሥራ አካባቢ እንዲሰሩ ማድረግ፣

## 73. ድንገተኛ የእሳት አደጋን መከላከልና መቆጣጠር

1. የእሳት አደጋን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ መሳሪያዎች የአደጋ ስጋት ባለባቸው ቦታዎችና የሥራ አካባቢዎች እንዲተከሉ ይደረጋል።

2. መሳሪዎቹ በሚተከሉበትና ጥቅም ላይ በሚውሉበት ጊዜ አደጋ እንዳያስከትሉ ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል፡፡
3. የእሳት አደጋ መከላከያና መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች ወደ ሀገር ውስጥ ሲገቡ፣ ሲተከሉ፣ ሲጠገኑም ሆነ ሲሞሉ የሚመለከታቸውን አካላት ትብብር መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡

## 74. የእቃ ማከማቻ መጋዘን ቦታ አመራረጥና መደረግ ያለባቸው ጥንቃቄዎች

1. እንደ ዕቃዎቹ መጠን፣ አይነትና ውስጣዊ ባህርይ መሰረት ያደረገ የአከመቻቸት ስርዓት ተግባራዊ በማድረግ ንብረቶቹን ማስቀመጥ፤
2. የእቃዎችን አደረጃጀት፣ አከመቻቸትና የስርጭት ስርዓትን በሚመለከት በባለሙያዎች የተቀመጠውን ማኑዋል ተግባራዊ ማድረግና አፈፃፀሙን መከታተል፣
3. የሚታዩ ክፍተቶችን ለማስተካከል በስራው ላይ ለተሰማሩ ባለሙያዎች ተገቢውን ስልጠና በየጊዜው በመስጠት የአሰራር ማኑዋሉን ጠንቅቀው በማወቅ ከዘልማዳዊ አሰራር እንዲወጡና ሙያዊ ግንዛቤያቸው ዳብሮ ዘመናዊና ቀልጣፋ የአገልግሎት አሰጣጥ እንዲያሰፍኑ የሚመለከታቸው አካላት እንቅስቃሴ ማድረግ፣

## 75. በሰው አቅም የማይንቀሳቀሱ ትላልቅ ዕቃዎችን በተመለከተ

1. የክብደት መጠናቸው ከሰው የጉልበት አቅም በላይ የሆኑና የዕቃ ማንሻ መሳሪያ የሚጠይቁ ንብረቶችን ለማውረድ ወይም ለመጫን የዕቃ ማንሻ መሳሪያ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡
2. እቃዎቹ የሚቀመጡበት መጋዘን ቢያንስ የሶስት ወገን የኋላ፣ የቀኝና የግራ ግድግዳ እና ጣሪያ ይኖረዋል፡፡
3. መጋዘኑ ለመሳሪያዎች በቂ መግቢያና መውጫ በር፣ ከውስጥ ለመሳሪያዎቹ በቂ መንቀሳቀሻ ቦታ ሊኖረው ይገባል፡፡
4. መጋዘኑ በወንፊት መሰል ሺቦ የሚዘጋ፣ በቂ የአየር መዘዋወሪያ ያለው፣ የዝናብ ተፋሰስ ወደ ውስጥ የማያስገባ መሆን አለበት፡፡

## 76. ስለ የአርማታ ብረቶች

1. የአርማታ ብረቶች አቀማመጥ ለዝገት የተጋለጠ እንዳይሆን ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

2. የአርማታ ብረቶች ግዥ አፈፃፀም በስራ ላይ የሚውለውን መጠንና ስራ ላይ የሚውልበትን ግዜ ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፡፡

## 77. ስለ ሲሚንቶ

1. የመጋዘኖች አቀማመጥ የዝናብ ፍሰትን/ወጨፎን/ የንፋስ አቅጣጫን ያገናዘበ ሆኖ ለአቀማመጣቸው ተገቢውን ትኩረት በመስጠት በዝናብ ወቅት ለጎርፍ እንዳይጋለጡ የሚከማቹበትን/የሚቀመጡበትን ቦታ ከመሬት በቂ ከፍታ ያላቸው አድርጎ በመስራት ከማንኛውም እርጥበት ሊጠበቁ ይገባል፡፡
2. መጋዘኖቹ ውስጣቸው እርጥበት ሊፈጥር በማይችል ሁኔታ ወለሉ በሲሚንቶ የተዘጋጀና፣ እንደአካባቢው ሁኔታ ጣራው ከፍታ እና በቂ ክፈፍ ያለው እንዲሆንና ከጣራው የሚፈሰው ውሃ ከአካባቢው እንዲወገድ የሚያስችል ቦይ የተዘጋጀለት ሊሆን ይገባል፡፡
3. ሲሚንቶ በቆይታ ለብልሽት የሚጋለጥ በመሆኑ ቀድሞ የገባውን ቀድሞ ስራ ላይ ማዋል /First in First out/ በሚያስችል ሁኔታ እንዲከማች ለማድረግ ሲሚንቶ ከመኪና ተራግፎ ወደ መጋዘን የሚገባበትን በአንድ አቅጣጫ፣ ወጪ የሚሆንበትን በሌላ በር በማድረግ ለጥበቃ በሚያመች ሁኔታ መዘጋጀት አለበት፡፡
4. መጋዘኖቹ ጭነት ለማራገፍና ለመጫንም በሚያመች ቦታ ላይ ሊገነቡ ይገባል፡፡ ጭነቱ በሚራገፍበትም ሆነ በሚጫንበት ወቅት ንብረቱን ከጉዳት ለመጠበቅ ተገቢው ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

## 78. በአስፋልት ዝግጅት ወቅት ሊደረጉ ስለሚገባ ጥንቃቄዎች

1. በታቻለ አቅም በአስፋልት መርጫ መሳሪያ ታንከሮች ወይም ኬትሎች ውስጥ የቀለጠ አስፋልት እንዳያድር ስራ በሚታቀድበት ወቅት ጥንቃቄ ማድረግ፣
2. አስፋልት የነዳጅ ውጤትና ለእሳት የተጋለጠ በመሆኑ የመርጫ መሳሪያዎች ምንጊዜም አካላቸው በንፅህና መያዝ አለበት፣
3. የአስፋልት መርጫ መሳሪያ የማፍሰሻ ቱቦዎች በየስራ ክንውኑ መጨረሻ ላይ ሊፀዱና የረጋ አስፋልት በውስጣቸው እንዳይኖር መደረግ አለበት፣
4. የመርጫ መሳሪያዎች በውስጣቸው ያለውን አስፋልት በራሳቸው የማሞቂያ መሳሪያ የማቅለጥ ስራ በሚያከናውኑበት ወቅት ከመኖሪያ ሰፈሮች፣ ከመሳሪያዎች ተለይተውና

የነፋስ አቅጣጫን በመጠበቅና አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሁሉ በማድረግ አስፋልቱን የማሞቅ ስራ ማከናወን አለባቸው፣

5. የአስፋልት መርጫ መሳሪያዎች አስፋልት በማሞቅ ስራ ላይ በሚሆኑበት ወቅት በስራው ላይ የተመደበው ሰራተኛ ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ አለበት፣
6. መሳሪያዎቹ ምን ጊዜም ከእሳት ጋር የተያያዘ ስራ የሚያከናውኑ በመሆኑ በቂ የእሳት ማጥፊያ መሳሪያ እንዲኖራቸው ሊደረግ ይገባል፣
7. በአስፋልት ስራ ላይ ተመድበው የሚሰሩ ሰራተኞች የሚያስፈልገው የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና አልባሳትን እንዲያገኙ፣ ስለ ሞቃት ነገሮች፣ ስለ አስፋልት አያያዝና አጠባበቅ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ፣
8. በቀለጠና ከፍተኛ ሙቀት ባለው አስፋልት ውስጥ የውሃ መግባት ከፍተኛ አደጋን የሚያስከትል በመሆኑ በአስፋልት ውስጥ ውሃ እንዳይገባ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፣
9. አስፋልት የያዙ በርሜሎች የሚጠራቀሙባቸው ቦታዎች በርሜሎቹ በቀጥታ መሬት ላይ እንዲቀመጡ ከማድረግ ጠጠርና አሸዋ በሚዘጋጅበት ቦታ ላይ ቢሆኑ ፍሰታቸው በቀጥታ ወደ መሬት ዘልቆ ከመግባት ይልቅ ጠጠሮችና አሸዋዎቹን ይዞ እንዲቀር በማድረግ እንዳይሰርግ ማድረግ፣
10. የአስፋልት ማከማቻና ማቅለጫ ቦታዎችን በውስን አካባቢዎች ብቻ ማድረግና ቦታዎቹን ወደ ነበሩበት መመለስ፣

## 79. ስለ ነዳጅና ታንከር

1. ሁሉም የነዳጅ ታንከሮች ከመቀበራቸው በፊት ዝገትን መቋቋም የሚያስችል መከላከያ ውጫዊ አካላቸው እንዲቀባና ነዳጅ የመያዝ አቅማቸው የሚታወቅና የጥልቀት መለኪያ ያላቸው ሆነው በሚመለከተው ተቆጣጣሪ አካል የተረጋገጠ ሊሆን ይገባል፡፡
2. የነዳጅ ታንከሮች በወገባቸውና በቁመታቸው አማካይ ላይ እስከ 60 ሳ.ሜ የክብ ግማሽ (Diameter) ስፋት ያለው ቀዳዳ ከ10 እስከ 20 ሳ.ሜ ከጋኑ አካል ከፍ ያለ አንገትና በቡሎን ታሳሪ የሆነ ክዳን ያላቸው ሆኖ በዚህ ትይዩ በግራ/በቀኝ/ ጠርዝ ላይ የአየር ማስተንፈሻ ቀዳዳ ብረት ሊታሰርበት በሚችል ሁኔታ የተዘጋላቸው ሆነው የተሰሩ መሆን አለባቸው፡፡

3. በእያንዳንዱ የታንከር አንገት ላይ የመያዝ መጠኑ (Capacity) ሊጠፋ በማይችል ሁኔታ የታተመበት፣ እያንዳንዱ ታንከር የየራሱ የጥልቀት መለኪያ ወደ ውስጥ ጠልቆ የሚቆምና የሚታሰር ሆኖ ሊዘጋጅ ይገባል።

## 80. የነዳጅ ጋኖች የሚቀበሩበት ቦታና የአቀባበር ሁኔታ

1. የነዳጅ ታንከሮች የሚቀበሩበት ቦታ ውሃማና ረግረጋማ ያልሆነ፣ ታንከሮቹ በአግባቡ ሚዛናቸውን ጠብቀው የተገነቡና በብረት የሚታሰሩ ሆነው የውሃ ፍሰት/ወይም ጎርፍ/ በማያጠቃው በተስተካከለ ቦታ ላይና ነዳጅ የጫኑ ተሽከርካሪዎች ለማራገፍም ሆነ ለመሳብ መጠጋትና መዞር የሚችሉበት ቦታ መሆን አለበት።
2. ለከፍተኛ የነዳጅ ማከማቻነት የሚዘጋጁ ታንከሮች የተቀመጠውን መስፈርቶች ያሟሉ ሆነው ጎን ለጎን እንዲደረደሩና በጣም ባልረዘመ የጣሪያ ከፍታ ከለላ የተሰራላቸው፣ ረጃጅም ተሽከርካሪዎች እንደልብ ተጠግተው ጭነታቸውን አሟጠው ማራገፍ የሚችሉበትን አቀማመጥ ያገናዘበ በደልዳላና በተስተካከለ ቦታ ላይ እንዲሆኑ መደረግ አለበት።
3. የነዳጅ ታንከሮች በየዓመቱ በሚመለከተው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ልኬታቸው እንዲፈተሽና እንዲረጋገጥ በማድረግ የማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መያዝ ይገባል።
4. የማከማቻ ታንከሮች ወደ ተቀበሩበት ቦታ ለመሳብ ወይም ለማራገፍ እንዲጠጉ ከሚፈቀድላቸው የነዳጅ ቦቴዎችና ሰራተኞች በስተቀር ማንም የማይገባበትና በባለወንፊት መሣይ የሽቦ አጥር ዙሪያው የታጠረ ለመግቢያና መውጫ በሚያመች ሁኔታ በሁለት ተቃራኒ አቅጣጫ የሚከፈትና የሚዘጋ እንዲሆን መደረግ ይኖርበታል።
5. በነዳጅ ሳቢያ ሊፈጠር የሚችል እሳት በሰውና በንብረት ላይ አደጋ እንዳያደርስ መከላከያ የሚሆኑ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ የእሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች በተገቢው መጠንና ብዛት በዙሪያው ማድረግ፣ በአካባቢው ምንም አይነት የነዳጅ ፍሰት እንዳይኖር ማድረግና በአሸዋ የተሞሉ ጉርድ በርሜሎች ከአካፋ ጋር ማስቀመጥ ያስፈልጋል።
6. በፕሮጀክት ካምፕ ተገኝተው የነዳጅ እደላ ለሚሰጣቸው ተሽከርካሪዎች፣ የግንባታና የግብዓት ማምረቻ መሳሪያዎች የሚዘጋጀው የነዳጅ ማደያ ከላይ የተጠቀሰውን

መስፈርቶች ባሟላ ሁኔታ ታንከሮቹ እንዲቀበሩና የነዳጅ መቅጃ ዲስፔንሰር የተተከለባቸው ሊሆኑ ይገባል፡፡

7. የነዳጅ እደላ ሰራተኛም እደላውን መከታተል፣ ማየትና መቆጣጠር የሚችልበት ለእይታ ምቹ የሆነ ቢሮ በቅርብ ርቀት ይዘጋጅለታል፡፡
8. በማደያ ቦታዎች የሚታየው የነዳጅ ፍሰት ከነዳጅ ብክነት ባለፈ ለአካባቢ ብክለትና ለሰራተኛ ጤና ችግር መንስኤ ሊሆን ስለሚችል ፍሰቱን መቆጣጠርና አሰራሩ ስርዓት እንዲይዝ ይደረጋል፡፡

## 81. ስለ ዘይቶችና ቅባቶች

1. ዘይቶችንና ቅባቶችን ከብልሽትና ከብክነት ለመጠበቅ የሚከማቹባቸው መጋዘኖች ደረጃቸውን የጠበቁ ይሆናሉ፤ አቀማመጣቸውም በአግባቡና በጥንቃቄ ይሆናል፡፡
2. ዘይቶችና ቅባቶች በቀላሉ መለየት እንዲቻል በአይነት በአይነታቸው ተለይተው እንዲቀመጡ ይደረጋል፡፡
3. የዘይቶች እደላ በሚከናወንበት ወቅት ብክነትና ብክለትን ለማስወገድ ከበርሜል ስቦ ለመቅዳት በሚያመች ሁኔት መቅጃ መሳሪያዎች (አነስተኛ የእጅ ፓምፖች) ጥቅም ላይ ሊውሉ ይገባል፡፡

## 82. ሞተር ግሬደር ላይ አደጋን ለመከላከል ሊወሰዱ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች

1. የሞተር ግሬደር አሽከርካሪዎች የመንግዱን ቀኝ መስመር ይዘው መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል፡፡ በግንባታ ወቅት አስቸኳይ ሁኔታ ተፈጥሮ የትራፊክ ፍሰቱን ማስቆም ሲያስፈልግ በቅድሚያ በአራጋቢ ወይም በአውለብለቢና መንገዱን ማገጃ ምልክት በመጠቀም በመንገዱ ለሚጠቀሙ ተሽከርካሪዎች ማስጠንቀቂያ መስጠት ያስፈልጋል፡፡
2. የግሬደሩ ኦኘሬተር በምንም አይነት የግሬደሩ ምላጭ ተነስቶ እያለ ከግሬደሩ መውረድ የለበትም፡፡
3. የኃይል መቆጣጠሪያውን ሌቨር በመሪ ለመጠቀም መሞከር አይገባም፡፡
4. ግሬደሩን ብርሃን በሌለበት በምሽት ማንቀሳቀስ የተከለከለ ነው፡፡

## 83. ቡል ዶዘሮችና ትራክተሮች ላይ አደጋን ለመከላከል ሊወሰዱ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች

1. የቀኑ ሥራ ከተጠናቀቀ በኂላ ኦኘሬተሩ፡-
   ሀ. በቅድሚያ ፍሬን መያዝ፣
   ለ. ምላጩን ወደ መሬት ማውረድ፣
   ሐ. ማርሹ ዜሮ ወይም ነፃ መሆኑን ማረጋገጥ፣
   መ. ዶዘሩ ወይም ትራክተሩ የቆመበት ቦታ የተስተካከለ መሆኑንና ቢቻል ልጆች በማይደርሱበትና ከአደጋ የተጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡
2. ዶዘሩ ወይም ትራክተሩ ወደ ዳገት በሚወጣበት ወቅት ምላጩ ወደ መሬት ተጠግቶ ሚዛኑን በጠበቀ መልኩ መንቀሳቀስ አለበት፣
3. ዶዘሩ በቁልቁለታማ ቦታ ላይ በሚሰራበት ወቅት በዶዘሩ ምላጭ ጫፍ ላይ የተወሰነ አመልካች የተቆፈረ አፈር መኖር አለበት፡፡
4. ዶዘር ወደ ቁልቁለት በሚንቀሳቀስበት ወቅት የዶዘሩን ምላጭ ወደታች በማድረግ እንደፍሬን መጠቀም የተከለከለ ነው፣
5. ዶዘር ወይም ትራክተር ከማንቀሳቀስ በፊት በአከባቢው ለአደጋ የተጋለጠ ምንም ነገር ያለመኖሩን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ይህን ለማድረግ ይበልጥ ተመራጩ መሳሪያውን ከማንቀሳቀስ በፊት ዙሪያውን በእግር ዞሮ ማየትና ማረጋገጥ፣
6. በሥራ ወቅት የመሳሪያ አንቀሳቃሹ ብቻ በመሳሪያው ላይ መቀመጥ አለበት ምክንያቱም ከአደጋ ተጠብቆ በተፈለገው መጠን በጥራት ለመስራት የሚሰራበት ቦታ ነፃ መሆን አለበት፡፡
7. ኦኘሬተሩ በመሳሪያው ላይ ማንም እንዲሳፈር መፍቀድ የለበትም፣ ከፈቀደ ለሚደርሰው አደጋና ችግር ተጠያቂ እንደሆነ ሊያውቅ ይገባል፣
8. ኦኘሬተሩ በተራራ ጫፍ ላይ ሆኖ ድንጋይ በሚገፋበት ወቅት ከስሩ ሰውና እንስሳት አለመኖራቸውን ማረጋገጥና ተመልሰው እንዳይገቡ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፡፡

## 84. ክሬንና ሾቭል ላይ አደጋን ለመከላከል ሊወሰዱ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች

1. ክሬን እንዲያነሳ ከተፈቀደለት የክብደት መጠን በላይ ማንሳት የተከለከለ ነው፡፡ መረጃ ሰጪ ጽሁፎችና ምልክቶች የክብደቱን መጠን በተለያዩ አቅጣጫዎች ሊነሱ

የሚገባቸውን ለእይታ ግልጽ በሆነ አቅጣጫ ከክሬኑ ጋር መቀመጥ ወይም መያያዝ አለባቸው፣

2. ደረጃውን የጠበቀና ተቀባይነት ያለው ሁሉም ኦፕሬተሮች ሊረዱት የሚችሉትና የሁሉንም ኦፕሬተሮች ሥራ ሊመራ የሚችል አንድ ሰው ብቻ መመደብ አለበት፡፡ ነገር ግን ጭነቱ አቅጣጫውን እየሳተ ከሆነ ክሬኑን የሚያጠናክረው ሌላ ተጨማሪ አመልካች አንድ ሰው ሊመደብ ይችላል፣
3. ኦፕሬተሩ ክሬን በሚጠቀምበት ወቅት መሬቱ ረግረጋማ ከሆነ ክሬኑን የሚያጠናክረው መርገጫ ግራና ቀኝ ወደታች መሬት ረግጦ እንዲይዝ ማድረግና በተቆለለ አፈር ጠርዝ ላይ ክሬን በምንጠቀምበት ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፣
4. የሚነሳው ጭነት የሚወዛወዝና አቅጣጫውን የማይጠብቅ ከሆነ መስመሩን የሚጠብቅ ታኮ ወይም ገመድ በተወሰነ ቦታ ብቻ ውዝዋዜው እንዲወሰን መቆጣጠር ያስፈልጋል፡፡ ይህም ተግባር እውቀትና ልምድ ባለው ሰው መከናወን ይኖርበታል፣
5. ከክሬን ኦፕሬተሩ በስተቀር በሌላ ሰው ክሬን ማንቀሳቀስ የተከለከለ ነው፣
6. ጭነት በሚነሳበት ወቅት ክሬኑ ተግባሩን በቀላሉ ለማከናወን እንዲያስችለውና የጭነት መንሸራተት እንዳይከሰት የጭነት ማንሻው ሁክ በቀጥታ በሚነሳው ጭነት ትክክል መነሳት አለበት፣
7. የሚነሳው ጭነት በማንኛውም ሰው ላይ መወዛወዝ የለበትም፣
8. ክሬኑ መንቀሳቀስ ያለበት በምልክት ሰጪው ሲመራ ብቻ ነው፡፡ ክሬኑ ጭነት በሚያነሳበት ወቅት በአካበቢው መሬት ላይ ያሉ ሌሎች ሠራተኞችን ጨምሮ ማንኛውንም ሰው ከማሽኑ ማራቅና ክሬኑ በሚዞርበት ወቅት አካባቢው ነፃ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፣
9. ክሬኑ በሚንቀሳቀስበት ወቅት ክሬኑ ላይ መውጣትም ሆነ መውረድ የተከለከለ ነው፡፡
10. የክሬኑ መጨረሻ ከኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ወይም የኤሌክትሪክ ገመድ ቢያንስ ሁለት ሜትር መራቅ አለበት፣ይሁንና ክሬኑ ከኤልክትሪክ ገመድ ጋር ከተገናኘ
    ሀ. የክሬን ማንሻው ከኤሌክትሪክ እስኪላቀቅ ወይም ኤሌክትሪክ እስኪቋረጥ ድረስ በክሬን ውስጥ ያለምንም እንቅስቃሴ መቆየትና እርዳታ ማግኘት የሚቻልበትን መንገድ መፈለግ፣
    ሐ. ከክሬኑ ውስጥ ለመውጣት የሚያስችል ሁኔታ ካለ ዘሎ መውረድ፣ በደረጃ ለመውረድ አለመሞከር፣

## 85. ከባድ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎችን ለማጓጓዝ መወሰድ ያለባቸው ጥንቃቄዎች

ከባድ መሳሪያዎች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ እንደ ርቀቱ መጠን ተጭነው እንዲንቀሳቀሱ በሚፈለግበት ጊዜ እንደዚሁም መሳሪያዎች በሚጫኑበት፣ በሚጓጓዙበትም ሆነ በሚወርዱበት ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚሹ በመሆኑ ስራውን በኃላፊነት የሚመራው አካል በቅድሚያ፡-

1. በጉዞው አቅጣጫ ላይ ባለው የመንገድ ርቀት ውስጥ በክብደት መጠን፣ በስፋትና በከፍታ የማለፊያ ችግር አለመኖሩን ትእዛዝ ሰጪው አካል በቅድሚያ ማጤን አለበት፣
2. በጉዞው ላይ ባሉ ከተሞች ውስጥ የመብራትና የስልክ መስመሮች የከፍታ መጠን ከጭነቱ ከፍታ ጋር እንዴት እንደሆነ በእያንዳንዱ ማቋረጫ ላይ ማስተዋል፣ ጥርጣሬ ካለም ቀድሞ የሚፈትሽ አካል ማዘጋጀት፣
3. የተጫነውን ጭነት ክብደትና ከፍታ በቅድሚያ ማወቅ ችግር ሳይፈጠር፣ ጉዞው ሳይስተጓጎል፣ ሰራተኞች ሳይንገላቱና የስራ እቅድ ሳይፋለስ እንዲከናወን የሚረዳ ሲሆን በጉዞ ላይ ያልታሰበ ችግር ቢፈጠር መሳሪያውን ለማውረድም ሆነ ከመድረሻው ላይ ለማራገፍ መሳሪያውን የሚያንቀሳቅስ ኦፕሬተር አብሮ እንዲጓዝ ሊደረግ ይገባል፡፡
4. ለመጫንም ሆነ ለማውረድ እንዲያገለግል በፕሮጀክት የሥራ አካባቢዎች በተወሰኑ አማካይ ቦታዎች የማውረጃና የመጫኛ ራምፖች ብዙ ወጪን በማይጠይቅ ሁኔታ መዘጋጀት አለባቸው፣
5. በመጀመሪያ ሊጭን የተዘጋጀው ተሽከርካሪ የሚጭነውን የመሳሪያ ክብደት የመጫን አቅም ያለው መሆኑን መረጋገጥ አለበት፣
6. የሚጭነው ተሽከርካሪ በደልዳላ ቦታ ላይ መቆምና ሁሉም የተሽከርካሪው እግሮች የዋናውም ሆነ የተሳቢው በትክክል መሬት የረገጡ መሆን አለባቸው፡፡
7. ሊጫን የሚፈለገው መሳሪያ ያለው ክብደት በጫኝ መሳሪያ አክስሎች ላይ ክብደቱ እኩል ሊከፋፈል በሚችልበትና በሁለቱ ጠርዞች አማካይ እንዲሆን መደረግ አለበት፡፡
8. በጉዞ ወቅት አሽከርካሪው ከጭነቱና ከመንገድ ሁኔታ ጋር የተጣጣመ ጉዞ በማድረግ እንዲያጓጉዝ ለተሰጠው መሳሪያ ደህንነትና በጉዞ ወቅት ለሚደርሰው ጉዳት ተጠያቂ ይሆናል፡፡
9. ለማውረድ በሚፈለግበት ወቅት በተስተካከለ ሁኔታ ወደ ማውረጃ ቦታ መጠጋትና በጥንቃቄ እንዲወርድ ማድረግ አለበት፡፡

## 86. የመንገድ ግንባታና ጥገና በሚከናወንባቸው የሥራ አከባቢዎች ሊደረግ የሚገባ ጥንቃቄ

1. የመንገድ ግንባታው ከመጀመሩ በፊት በለውጥ መንገድ የትራፊከ ፍሰቱ ሊስተናገድ የሚችልበትን አከባቢ መለየት፣ የለውጥ መንገድ መገንባት እና የለውጥ መንገድ አጠቃቀሙን መከታተል ያስፈልጋል።
2. የለውጥ መንገዶች አደጋ እንዳያስከትሉ የመንገድ ደህንነት ምልክቶች በተገቢ ርቀት ላይ በቀንም ሆነ በምሽት የመንገድ ተጠቃሚዎች ሊያዩዋቸው በሚችሉባቸው ቦታዎች መትከል፣
3. ለውጥ መንገዶች አስፈላጊነታቸው ሲያበቃና ዋናው መንገድ ለትራፊክ ክፍት ሲሆን የትራፊክ ምልክቶችን ከማንሳት በተጨማሪ በምሽት አሽከርካሪዎች ላይ ሊፈጥር የሚችለውን ችግር በመረዳት ከመንገድ ጠርዝ ጋር ማመሳሰል፣
4. የሚገነባው መንገድ መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ ምቹ ባለመሆኑ የትራፊክ ፍሰቱ በአንድ አቅጣጫ ብቻ አንድ ተሽከርካሪ እንዲያልፍ አስገዳጅ በሚሆንበት አካባቢ የተቀናጀ ስራ በመስራት መንገዱ በአጭር ጊዜ የሚጠናቀቅበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
5. ከላይ በተጠቀሱት ቦታዎች ላይ ተሽከርካሪዎች የመንገዱን ጠርዞች እንዳይጠጉና ከርቀት ማየት እንዲችሉ ማድረግ፣
6. የትራፊኩን ፍሰት የሚያስተላልፍ ምልክት ሰጪ አራጋቢ (Flag man) መመደብና እንደ ቦታው ርቀት በቅርብ ርቀት በመገናኛ ሬዲዮ እየተገናኙ በጥንቃቄ እንዲያስተላልፉ ማድረግ፣
7. እየተገነባ ባለና አስቸጋሪ በሆነ ጠባብ መንገድ ላይ በምሽት ጊዜ አንዱን አቅጣጫ በተለይም የቁልቁለት ተጠቃሚው ከመነሻ አቅጣጫ ላይ አሽከርካሪዎች ተገቢ ግልጋሎት ሊያገኙ በሚችሉባቸው ቦታዎች እንዲያድሩ በማድረግ መዝጋት፣ ከዝቅተኛ ቦታ ለሚመጡ ተሽከርካሪዎች ብቻ ክፍት ማድረግና ይህንኑ በተገቢ የመገናኛ ዘዴ የመንገድ ተጠቃሚዎች በቅድሚያ እንዲያውቁት ማድረግና ከዝቅተኛ የመንገድ አቅጣጫ የሚመጣ ተጠቃሚ በምሽት ላይ የመንገዱን መሃል ይዞ እንዲጓዝ ማድረግ፣

## 87. ጥገና በሚከናወንባቸው መንገዶች ላይ ሊወሰዱ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች

1. ሰራተኞች በስራ ላይ መሆናቸውን የሚገልጽ ምልክት እንደቦታው ሁኔታ አሽከርካሪዎች ተሽከርካሪዎቻቸውን መቆጣጠር በሚችሉበት ምቹ በሆነ ቦታ ላይ ሊቀመጥ ይገባል፤
2. በጥገና ላይ የተሰማሩ ሰራተኞች በርቀት መታየት እንዲችሉ አንፀባራቂ መስመር ያላቸውን የሴፍቲ ጃኬቶች ለብሰው መስራት አለባቸው፣
3. ለመንገድ ጥገና ስራ ጥቅም ላይ ሊውል የተዘጋጀ ማንኛውም ማቴሪያል የመንገድ ተጠቃሚዎችን ለአደጋ በማያጋልጥ ሁኔታ ከምሽት በፊት ስራ ላይ ውሎ (ተዘርግቶ) ማለቅ በሚያስችል የስራ ዕቅድ መከናወን አለበት፤
4. የመሳሪያዎችን አጠቃቀም ለማጎልበት በጠጠር መንገዶች ላይ በረጅም ርቀት ለጥገና የሚውል ማቴሪያል የመንገዱን ጠርዝ እንዲይዝ መደረግ አለበት፤
5. በአንዳንድ የመንገድ አካባቢዎች በመንገድ ጠርዝ ላይ የጥገና ማቴሪያል ማስቀመጥ አስቸጋሪ በሚሆነባቸው ውስን ቦታዎች ላይ ፈጣን ጥገና በማከናወን የትራፊክ ፍሰቱንና በምሽት ወቅት ተሽከርካሪዎችን ለአደጋ ከመጋለጥ ስለሚያድን በትኩረት ሊሰራበት ይገባል፡፡
6. እንደ መንገዱ መልከአ ምድራዊ አቀማመጥ በዝናባማ ወቅት ተለይተው ለታወቁ የመንገድ ላይ የናዳ ቦታዎች የቅርብ ክትትልና ትኩረት መስጠት፤ እንዲሁም የትራፊክ እይታን የሚከለክሉ የመንገድ አካል ያልሆኑ ባዕድ ነገሮች በየጊዜው ማስወገድ አስፈላጊ ነው፡፡

# ክፍል አምስት

# የባለ ድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

## 88. የኮርፖሬሽኑ ተግባርና ኃላፊነት

1. የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ ሥርዓት በመዘርጋት ስርዓቱ ከዋናው መ/ቤት እስከ ፕሮጀክቶች ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፣

2. ለአካባቢ፣ የሥራ አካባቢ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ ሥራዎች አፈጻጸም አስፈላጊውን ሀብት ይመድባል፣
3. ደረጃውን የጠበቀ የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ ሥርዓት በመዘርጋት የኮርፖሬሽኑን የማስፈፀም አቅም እንዲገነባ ያደርጋል፣
4. የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ ዕቅዶች ሥርዓተ ፆታን፣ የአካባቢ ጥበቃን፣ ኤች አይ ቪ/ኤድስንና ለአደጋ ተጋላጭ ለሆኑ ሠራተኞች ትኩረት የሰጡና ያካተቱ እንዲሆኑ ያደርጋል፣
5. ሞትን ጨምሮ ከሥራ ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ አደጋዎችን፣ በሽታዎችንና ጉዳቶችን ለመከላከልና ለመቀነስ የሚያስችል የተጠያቂነትና የካሳ ሥርዓት ይዘረጋል፣
6. ሰብዓዊና ቁሳዊ ጉዳት የሚያስከትሉ አደጋዎችን፣ የአካባቢ ጉዳትን እና ብክለትን ለመከላከልና ለመግታት የሚያስችል የአደጋ ቅድመ ማስጠንቀቂያ እና ምላሽ መስጫ ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፣
7. ደረጃቸውን የጠበቁ የሥራ ልብሶችና የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎች እንደየሥራው ባህሪ ለሠራተኞች እንዲቀርቡ ያደርጋል፣
8. በሥራ ቦታዎች የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ ከብቁ ባለሙያና ግብአቶች ጋር የማቅረብ፣
9. በፕሮጀክቶች ለድንገተኛ አደጋ አገልግሎት የሚሰጥ የአምቡላንስ መኪና ይመድባል፡፡
10. በርቀት እና በግልፅ ሊታይ የሚችል ለሥራ ኃላፊዎች ነጭ፣ ለጎብኝዎች ቀይ እና ለሰራተኞች ቢጫ የሆነ የኮርፖሬሽኑ **ስምና ዓርማ ያለበት** የአደጋ መከላከያ ልብስ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤
11. ኮርፖሬሽኑ የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅን አስመልክቶ ከንዑስ ተቋራጭ ድርጅቶችና ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፡፡
12. በዚህ ማኑዋል ክፍል 2፣ 3 እና 4 የተጠቀሱ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## 89. የዘርፍ ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት

1. ለአካባቢ፣ የሥራ አካባቢ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ የተመደበው ሀብት በአግባቡ በሥራ ላይ እንዲውል መሰድረግ፡፡
2. በሥራ ቦታ ለሚከሰት አደጋና ጉዳት ወይም በሽታ ተጐጂዎች የህክምና እርዳታ እንዲያገኙና ተጠቃሚ እንዲሆኑ መስራት፡፡

3. በኮርፖሬሽኑ የሚቀርቡትን የመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ መስጠት የሚያስችሉ ግብዓቶችን፣ ባለሙያዎችን፣ የአደጋ መከላከያ ልብሶችንና መሳሪያዎችን ለየፕሮጀክቶች መመደብና በወቅቱ እንዲደርሳቸው በማድረግ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማስቻል፡፡
4. የዘርፉና የፕሮጀክት ሠራተኞች የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ሥልጠና እንዲሰጣቸው ማድረግ፡፡
5. የዘርፉና የፕሮጀክት ሠራተኞች እንደየሥራ ሁኔታቸው ባህሪ በሥራ ቦታቸው ሁልጊዜ የአደጋ መከላከያ አልባሳቶችንና መሳሪያዎችን መጠቀማቸውን መቆጣጠር፡፡
6. የዘርፉ ሠራተኞች ተግባሮቻቸውን በአግባቡ ለማከናወን የሚያስችላቸውን በቂ መረጃና ማኑዋልዎችን እንዲያገኙ ማድረግ፡፡
7. በዚህ ማኑዋል ክፍል 2፣3 እና 4 የተጠቀሱ ተግባራትን ማከናወን፡፡

## 90. የፕሮጀክቶች ተግባርና ኃላፊነት

2. የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ ፖሊሲና ማኑዋሉን በሥራ ላይ የማዋል፣
3. ለአካባቢ፣ የሥራ አካባቢ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ የተመደበውን ኃብት በሥራ ላይ የማዋል፣
4. የደህንነት ምልክቶችን በተገቢው የሥራ ቦታዎች ሁሉ መለጠፉንና ለፕሮጀክቱ ሠራተኞች በቂ የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ ግንዛቤ መሰጠቱን የማረጋገጥ፣
5. ለድንገተኛ አደጋ አገልግሎት የተመደበውን የአምቡላንስ መኪና የማስተዳደር እና ለዚህ ሥራ አገልግሎት የሚሰጥ ስልክ በማዘጋጀት ሠራተኞች እንዲያውቁት ማድረግ፣
6. በሥራ እንቅስቃሴዎቻቸው ወቅት አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ሁኔታዎችን ቀድሞ በመገመት የመከላከል ሥራ የመሥራት፣
7. የፕሮጀክት ሠራተኞች የጥራት፣ የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ ሥልጠና እንዲሰጣቸው የማድረግ፣
8. ለፕሮጀክቱ ሠራተኞች እንደየሥራ ሁኔታቸው ባህሪ አስፈላጊውን የአደጋ መከላከያ አልባሳትና መሳሪያዎች እንዲሰራጩላቸው ማድረግ እና ሠራተኞች

በሥራ ቦታቸው ሁልጊዜ የአደጋ መከላከያ አልባሳቶችንና መሳሪያዎችን በአግባቡ መጠቀማቸውን የመከታተልና የመቆጣጠር፣

9. ተሽከርካሪዎችን፣ ማሽኖችን እና መሳሪያዎችን የሚያንቀሳቅሱ ባለሙያዎች የሰለጠኑ እና ብቃቱ ያላቸው እንዲሆኑ አስፈላጊ ስልጠናዎች እንዲሰጣቸው ማድረግ፣
10. ክሬኖች፣ የማንሻ መሳሪያዎች እና ማንጠልጠያዎች ትክክለኛ የቴክኒክ ብቃት ምርመራ ማለፋቸውን የሚያሳይ የምስክር ወረቀት ማግኘታቸውን የማረጋገጥ፣
11. በሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓት ለሠራተኞች የሥራ ልብስና የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎች መልበሻ መቀየሪያ ክፍል የማዘጋጀት፣
12. የፐሮጀክቱ ሠራተኞች ተግባሮቻቸውን በአግባቡ ለማከናወን የሚያስችላቸውን በቂ መረጃና ማኑዋልዎችን እንዲያገኙ የማድረግ፣
13. በዚህ ማኑዋል ክፍል 2፣3 እና 4 የተጠቀሱ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## 91. የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ የሥራ ክፍል ተግባርና ኃላፊነት

1. የሥራ ቦታዎችና አካባቢዎች ምቹ፣ ጤናማና ከአደጋ የተጠበቁ መሆናቸውን የማረገገጥ፣
2. ጥሬ ዕቃዎች፣ የመገልገያ መሳሪያችና ማሽነሪዎች፣ የሥራ ሂደቶች እና የአሰራር ዘዴዎች አደጋ የማያስከትሉና የአካባቢ ስነ-ምህዳር ደህንነትን የማያዛቡ መሆናቸውን የማረጋገጥ፣
3. ለሠራተኞች የሚቀርቡ የሥራ ልብሶችና የአደጋ መካላከያ መሣሪያዎች ተገቢነት ያላቸውና ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸውን በማረጋገጥ አፈጻጸሙን የመከታተል፣ የመቆጣጠር፣
4. በሥራ ቦታ በሚከሰት አደጋና ጉዳት ወይም በሽታ ተጐጂ የሆኑ ሠራተኞች በተዘረጋው አሰራር ተጠቃሚ መሆናቸውን የማረጋገጥ፣
5. በተለያዩ የሥራ ክፍሎች ያሉ ሰራተኞችና ባለሙያዎች በመጀመሪያ ደረጃ ህክምና ዕርዳታ አሰጣጥ ላይ እንዲሰለጥኑና የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማድረግ፣
6. በሥራ ምክንያት የሚከሰቱ አደጋዎችና ጉዳቶችን የመመዝገብ፣ ተከታትሎ የማጣራት እና ዳግም እንዳይከሰት የእርምት ሃሳብ  የማቅረብ፣

7. ሠራተኞች በመከላከል መርህ ላይ የተመሠረተ የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ ባህል እንዲያዳብሩ የማድረግ፣
8. በተለያዩ የሥራ ክፍሎች የሚገኙትን የሠራተኛ ክበብ ሠራተኞች ወቅታዊ የጤና ምርመራ ማድረጋቸውን እንዲሁም ክበቦቹ የሚሰጡትን አገልግሎት የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ አገልግሎት መስፈርት መሟላቱን የመከታተል፣
9. የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ ጠንቆችንና አደጋዎችን ለመከላከል የሚረዱ ስልጠናዎችን ይሰጣል፣ ጽሁፎች እና ፖስተሮች ተዘጋጅተው እንዲሰራጩ ወይም እንዲለጠፉ የማድረግ፣
10. ለደህንነት እና ጤንነት መጠበቂያ የሚያገለግሉ መሣሪያዎችና ግብዓቶች የአገልግሎት ጊዜያቸው ያላለፈባቸው እና በትክክል አገልግሎት የሚሰጡ መሆናቸውን የማረጋገጥ፣
11. ሌሎች የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅን የሚመለከቱ ሥራዎችን የማከናወን፣ መደገፍ፣ የመከታተልና ሪፖርት የማድረግ፣

## 92. የሠራተኛ ማህበር ተግባርና ኃላፊነት

1. የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ ሥርዓትን በየደረጃው ለመዘርጋትና ምቹ የሥራ ሁኔታ ለመፍጠር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅትና በትብብር የመስራት፣
2. የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅን በተመለከተ ፖሊሲዎችና የህግ ማዕቀፎች ሲዘጋጁና ሲሻሻሉ የመሳተፍ፣ በአባሎቻቸው ዘንድ ግንዛቤ እንዲፈጠር የማድረግና ሥራ ላይ የማዋል፣
3. በየደረጃው በሚቋቋሙ የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ ተከታታይ ኮሚቴዎች ውስጥ በንቃት የመሳተፍ፣
4. በሥራ ቦታ በሚከሰት አደጋ ሳቢያ የጤና ጉዳት፣ የህይወትና የንብረት ጥፋት እንዳይደርስ አስፈላጊውን እገዛ የማድረግ፣ ጉዳቱን ለመቀነስ በሚወሰዱ እርምጃዎች ላይ የመሳተፍ፣
5. የአካባቢ፣ የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤናን ለማስጠበቅ፣ ምርታማነትን ለማሳደግ፣ የሠራተኞችንና የማህበሩን ግንዛቤ እና ተሳትፎ ለማሳደግ የአቅም ግንባታ ተግባራትን የማከናወን፣

6. በየደረጃው የሚካሄዱ የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ ኘሮግራሞች ለሴቶች፣ ለወጣቶች እና ለአካል ጉዳተኞች እንዲሁም ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ በደማቸው ውስጥ ላለባቸው ሠራተኞች ትኩረት እንዲሰጥ የማድረግና የመደገፍ፣

## 93. የሥራ መሪና የሠራተኛው ተግባርና ኃላፊነት

ሁሉም የሥራ መሪና ሠራተኛ የሚከተሉትን ዋና ዋና ተግባራት ማከናወን ይኖርበታል።

1. የሠራተኛውን ደህንነትና ጤንነት እንዲሁም የተፈጥሮ አከባቢን ለመጠበቅ የወጡና የሚወጡ ህጎችን፣ መመሪያዎችን፣ ማኑዋሎችንና አሰራሮችን ተግባራዊ የማድረግ፣
2. በኮርፖሬሽኑ መሣሪያዎች ላይ የሠራተኞችን ደህንነትና ጤንነት የሚጐዱ ጉድለቶች ሲገኙ ለሚመለከታቸው የጤና ባለሙያዎች ወይም ለሥራ ኃላፊዎች በአስቸኳይ የማሳወቅ፣
3. የሠራተኞችንና የሌሎችን ደህንነትና ጤንነት ለመጠበቅ የተሰጡ የአደጋ መከላከያዎችና የደህንነት መጠበቂያ መሣሪያዎችን በአግባቡ የመያዝና የመጠቀም፣
4. ለሥራ የተሰጠውን የጤናና ደህንነት መጠበቂያ ባለመጠቀሙ ምክንያት ለሚደርስ አደጋ ኃላፊነቱን የመውሰድ፣
5. በሥራ ሂደት ወይም ከሥራ ጋር ግንኙነት ባለው ሁኔታ አደጋዎችና የጤና ጠንቆች ሲከሰቱ ሁኔታዎችን ለቅርብ የሥራ ኃላፊ እና ለሚመለከተው አካል የማሳወቅ፣
6. የሥራ እንቅስቃሴዎቻቸው ሁሉ የተፈጥሮ አካባቢን ከግምት ውስጥ ያስገባ እንዲሆን ጥረት ማድረግ እና ኮርፖሬሽኑ በሚያከናውናቸው የአካባቢ እንክብካቤ እንቅስቃሴዎች ላይ በንቃት የመሳተፍ፣
7. በመንገድ፣ በጋራዥ፣ በክሊኒክ እንዲሁም በተለያዩ ቦታ የሚሰሩ የኮርፖሬሽኑ ሠራተኞች ደረቅ ቆሻሻ ወይም ማንኛውም ቆሻሻ ወደ ውኃ አካላት ወይም ወደ ሌላ አካባቢውን ወይም ስነ- ምህዳሩን በሚበክል መልኩ ማስወገድ የለበትም፣
8. የኮርፖሬሽኑ ሠራተኞች ማንኛውንም አየር ሊበክል የሚችል ድርጊት ከማከናወን መቆጠብ አለባቸው፣

## 94. በየደረጃው የሚቋቋሙ የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ ተከታታይ ኮሚቴ አወቃቀር፣ ተግባርና ኃላፊነት

### 1. የኮሚቴው አወቃቀር

በኮርፖሬሽኑ የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ እንዲረጋገጥ፣ የአደጋ ክስተቶች እንዲቀንሱ የሚያግዝ ከሥራ መሪዎችና ከሠራተኞች የተውጣጣ ጉዳዩን የሚከታተል፣ የሚቆጣጠር እና የሚያስተባብር የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ ተከታታይ ኮሚቴ በዋና መ/ቤት፣ በዘርፎችና በፕሮጀክቶች ይዋቀራል፡፡

### 2. የዋና መ/ቤት የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ ተከታታይ ኮሚቴ አባላት

በዋናው መ/ቤት በዋና ሥራ አስፈጻሚ የሚመራ የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ ተከታታይ ኮሚቴ የሚቋቋም ሲሆን አባላቱም፡-

ሀ. ለዋና ሥራ አስፈጻሚ ተጠሪ የሆኑ የሥራ ኃላፊዎች ---------------- አባል

ለ. የመሠረታዊ የሠራተኛ ማህበር ሁለት ተወካይ---------------------------- አባል

ሐ. የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ የሥራ ክፍል….. አባልና ፀሐፊ ናቸው፡፡

### 3. በዘርፍ ተቋሞች ደረጃ የኮሚቴ አባላት

በዘርፎች ደረጃ በም/ዋና ሥራ አስፈጻሚዎች የሚመራ የአካባቢ፣ የሙያ ጤንነትና ደህንነት ተከታታይ ኮሚቴ የሚቋቋም ሲሆን አባላቱም፡-

ሀ. የዘርፍ ተቋሙ ዋና መምሪያ ሥራ አስፈጻሚዎች----------------- አባል

ለ. የዘርፍ ተቋሙ መምሪያ ሥራ አስኪያጆች -------------------------- አባል

ሐ. የመሠረታዊ የሠራተኛ ማህበር አንድ ተወካይ-------------------- አባል

መ. የድጋፍ ሰጪ አገልግሎት ኃላፊ ------------------------------------ አባል

ሠ. የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ የሥራ ክፍል….. አባልና ፀሐፊ ናቸው፡፡

### 4. በፕሮጀክቶች ደረጃ የኮሚቴ አባላት

በፕሮጀክቶች ደረጃ በፕሮጀክት ሥራ አስኪያጆች የሚመራ የአካባቢ፣ የሙያ ጤንነትና ደህንነት ተከታታይ ኮሚቴ የሚቋቋም ሲሆን አባላቱም፡-

ሀ. የፕሮጀክት ቡድን መሪዎች --------------------------------------------- አባል

ለ. የመሠረታዊ የሠራተኛ ማህበር አንድ ተወካይ---------------------------- አባል

ሐ. ከአካባቢው ተጽዕኖ ፈጣሪ ግለሰቦች አንድ ተወካይ --------------------- አባል

መ. ከአካባቢው ወረዳ መስተዳድር (ጉዳዩ የሚመለከተው) አንድ ተወካይ ----- አባል

ረ. የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ ባለሙያ--------አባልና ፀሐፊ ናቸው፡፡

## 5. የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ ተከታታይ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

ሀ. የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ የሥራና የበጀት ዕቅድ ማዘጋጀትና ሲጸድቅም በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ፣

ለ. ልዩ ክትትል የሚያስፈልጋቸውን የሥራ ላይ ጠንቆች፣ የአሰራር ዘዴዎችና ማሽኖችን በመለየት ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት የማድረግ፣

ሐ. ከኃላፊዎችና ከሠራተኞች ጋር በመመካከር የማሻሻያ ሃሳቦችን የማቅረብ፣

መ. የሥራ ላይ አደጋዎችን፣ አደገኛ ክስተቶችን፣ የጤና መታወኮችንና በእነዚህ ምክንያት የወጡ ወጪዎችን፣ የባከኑ የሥራ ሰዓቶችን፣ የባከነ ምርት፣ የምርት ግብዓት እና የሥራ አካባቢ ብክለት መረጃዎችን በትክክል በመሰብሰብ እና በማጠናከር የመከላከያ እርምጃዎችን ለመውሰድ፣ እቅድ ለማዘጋጀት እና በጀትና የሰው ኃይል ለመመደብ በሚያስችል ሁኔታ የማደራጀት፣

ሠ. ስለተከሰቱ ወይም ሊከሰቱ ስለሚችሉ አደጋዎች፣ በሽታዎች ወዘተ… በማጣራት ሁኔታው በድጋሜ እንዳይከሰት የሚያስችል የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን የማመላከት፣

ረ. የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ የትምህርትና ሥልጠና ኘሮግራሞች እንዲዘጋጁ ሃሳብ የማቅረብ፣ ኘሮግራም ማዘጋጀት፣ የኘሮግራሙን ውጤታማነት የመገምገም፣

ሰ. የሥራ ላይ አደጋዎችን ለመከላከል በግልም ሆነ በቡድን በሠራተኞች የሚደረጉ ጥረቶችንና የፈጠራ ሥራዎችን የማበረታታት፣

ሸ. የአካባቢ፣ የሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅን በተመለከተ በማኔጅመንት እና በሠራተኞች መካከል መረጃዎች የሚተላለፉበትን ዘዴ የማመላከትና የውይይት መድረኮችን ወይም ፎረሞችን ማዘጋጀት፣

ቀ. በሥራ ቦታዎች የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ ቀን እንዲከበር የማድረግ፣ በአርአያነት የሚጠቀሱ የሥራ ክፍሎችና ሠራተኞች በሥራዎቻቸው እንዲሸለሙ በማድረግ በጐ የውድድር መንፈስ እንዲፈጠር የማድረግ፣

በ. የኮርፖሬሽኑን የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ የአሠራር ማኑዋል ውጤታማነት በመገምገም የማሻሻያ ሃሳብ የማቅረብ፣

ተ. የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ ሥርዓት አፈፃፀምን ለማሳደግ የሚያግዙ ሌሎች ተግባራትን ማከናወን፣

## 95. የክበብ ኃላፊዎች ተግባርና ኃላፊነት

1. የሥራተኞችን ንፅህና እና የጤና ሁኔታ መቆጣጠርና ማረም፣
2. ሠራተኞች የግል ንብረት ማስቀመጫና ልብስ መቀየሪያ ክፍል እንዲኖራቸው ማድረግ፣
3. ምግብ በሚዘጋጅበት/በሚሰራበት ውስጥና አካባቢ ከአዘጋጆች ውጭ ሌላ ሰው እንዳይገባ ማድረግ እና ይህንንም የተመለከቱ የማስጠንቀቂያ ምልክቶችን እና መረጃ ሰጪ ጽሁፎችን ማስቀመጥ፣
4. ሥራተኞች የጤና ችግር ሲገጥማቸው እንዲያሳውቁ በማድረግ አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ፣
5. ሠራተኞች የበሽታ ምልክት ካለባቸው እንዲታከሙ በማድረግ ህክምናቸውን እስኪጨርሱ ድረስ ከምግብ ጋር ንክኪ በማይኖርባቸው ቦታዎች ላይ ብቻ እንዲሰሩ ማድረግ፣
6. ለሠራተኞች ተገቢ የሥራ ልብሶችንና መሳሪያዎችን በማቅረብ እንዲጠቀሙ ማድረግ፣
7. መታጠቢያ/መፀዳጃ ቤቶች እና የግል ንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች እንዲሟሉ ማድረግ፣
8. ከፕላስቲክ የተሰሩና በእግር የሚከፈቱ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ዕቃዎች እንዲኖሩ ማድረግ፣

9. ክበቡ ተገቢ የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሳሪያ በተገቢው ቦታ ላይ እንዲኖረው ማድረግ፣
10. ክበቡ የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ መስጫ መሳሪያ (First aid kit) እንዲኖረው ማድረግ፣

## 96. የክበብ ሠራተኞች ተግባርና ኃላፊነት

1. በማንኛውም ጊዜ እጅን በውሃና በሳሙና መታጠብ፣
2. በሰውነት ንክኪ ምግብ እንዳይበከል ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ፣
3. ምግብ በሚቀመጥባቸውና በሚዘጋጅባቸው ወንበሮችና ጠረጴዛዎች ላይ አለመቀመጥና የግል ንብረትን አለማስቀመጥ፣
4. ቁስለት ያለበት የሰውነት ክፍል ካለ በሚገባ መሸፈን/ኗንት ማድረግ፣
5. የግል ንጽህናን መጠበቅ እና የስራ ልብስን ንፅህናው የተጠበቀና ጽዱ ማድረግ፣
6. ማስነጠስና ማሳል ከአቅም በላይ ከሆነ በሶፍት አፍንና አፍንጫን መሸፈንና ሶፍቱን በአግባቡ ክዳን ባለው የቆሻሻ ዕቃ ውስጥ መጣልና እጅን በውሃና በሳሙና መታጠብ፣
7. የስራ ልብስን በአግባቡ በመጠቀም ሥራን ማከናወን፣
8. ከታመሙ/የጤና መታወክ ካጋጠመ ለቅርብ ኃላፊ ማሳወቅ፣

## 97. የፕሮጀክት ባለቤት (Client) ተግባርና ኃላፊነት

ሁሉም የሥራ ውሎች በወቅቱ፣ በበጀት እና የሥራ ላይ ጉዳቶች ሳይደርሱ እንዲጠናቀቁ ለማድረግ የፕሮጀክት ባለቤት የሚከተሉትን ማከናወን አለባቸው፡፡

1. የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ አስገዳጅ ሕጎች መከበራቸውን የማረጋገጥ፣
2. የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ መስራት ወይም አግባብ ባላቸው አካላት ማሰራት እና በፕሮጀክት ዲዛይን ወቅት የአካባቢ ደህንነት ሁኔታዎችን ከግምት የማስገባት፣
3. የፕሮጀክቱን የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ ፕሮግራም ለመተግበር የሚያስችል በቂ ጊዜ እና ሀብቶችን (resources) መመደብ፣

## 98. የንዑስ ተቋራጮች (Sub-Contractors) ተግባርና ኃላፊነት

1. ዋናው ሥራ ተቋራጭ እና አሰሪው ተስማምተው ባፀደቁት የጤና እና ደህንነት ዝርዝር እቅድ ላይ በመመርኮዝ ተስማሚ እና ግልፅ የሆነ የደህንነት እና ጤና እቅዶችን ያዘጋጃል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
2. ከላይ በተራ ቁጥር 1 በተገለጸው መሠረት ያቀዳቸውን የጤና እና የደህንነት መረጃዎች ሥራውን ከጀመረ ቀን ጀምሮ በግንባታ ቦታ ላይ በተግባር ያውላል፡፡
3. የጤና እና የደህንነት ዝርዝር መረጃ የያዙ ፋይሎችን ግልፅ በሆነ የግንባታ ቦታ ላይ ሁሉም ሠራተኞች፣ ጐብኝዎች እና ለአሰሪ ተወካይ ወይም ባለቤት በቀላሉ ሊያገኙ በሚችሉበት ቦታ ያስቀምጣል፡፡
4. የጤና እና ደህንነት ዝርዝር እቅዶች በግንባታ ቦታ ላይ እንዲተገበሩ ከዋናው ሥራ ተቋራጭ ከተመደበው ተቆጣጣሪ ባለሙያ ጋር በጋራ ይሠራል፡፡
5. በግንባታ ቦታ ለሚሠሩ ማንኛውም ሠራተኞች የጤና እና የደህንነት ስጋቶችን በመለየት የመፍትሔ እርምጃ ይወስዳል፡፡

# ክፍል ስድስት

# ስለ ሠራተኛና ንብረት ጉዳትና የጉዳት ሪፖርት ይዘት

## 99. በሠራተኛ ላይ ስለደረሰ ጉዳት የሚቀርብ ሪፖርት ይዘት

1. የሥራ ላይ አደጋ ሪፖርት በጊዜው በአፋጣኝ ተዘጋጅቶ የሚከተሉትን መረጃዎች በማሟላት ሊላክ ይገባል፡፡

   ሀ/ የተጎዱውን ሠራተኛ ሙሉ መረጃ፣

   ለ/ ምን በመስራት ላይ እንዳለ ጉዳት የደረሰበት መሆኑን፣

   ሐ/ ይጠቀምበት የነበረው የስራ ማከናወኛና፣ የደረሰው የጉዳት አይነትና ደረጃ፣

   መ/ ጉዳት እንደደረሰበት የተደረገለት የህክምና እርዳታና በቀጣይ ሊደረግለት የሚገባው ህክምና፣

   ሠ/ ተመሳሳይ የስራ ላይ አደጋዎች እንዳይከሰቱ በባለሙያ እይታ ሊደረግ የሚገባውን ጥንቃቄ፣

ረ/ አደጋው የነፍስ ወከፍ የአደጋ መከላከያ መሳሪያን በማድረግ ሊድን ይችል የነበረ መሆን አለመሆኑን፣ ሰራተኛው ስራውን በሚያከናውንበት ወቅት ሊጠቀም የሚገባውን የአደጋ መከላከያ መሳሪያ ማድረግ አለማድረጉን፣ መሠል ዝርዝሮች የያዘ ሆኖ የባለሙያዎችን አስተያየት አካቶ በማዘጋጀት በቂ ኮፒዎችን አሟልቶ ለዋናው መ/ቤት እንዲደርስ መደረግ አለበት፡፡

2. ከላይ ባለው ንዑስ አንቀጽ የሚቀረበውን ሪፖርት መሰረት በማድረግ ጉዳት ላጋጠመው ሰራተኛ  የአሰሪና ሰራተኛ ሕጉንና በኮርፖሬሽኑ እና በኮርፖሬሽኑ የሰራተኛ ማህበር መካከል የተፈረመውን የሕብረት ስምምነት መሰረት በማድረግ ኮርፖሬሽኑ የካሳ ክፍያ ይፈፀማል፡፡

## 100. በተሽከርካሪ ላይ ስለደረሰ ጉዳት

1. በተሽከርካሪው ላይ አደጋው እንደደረሰ ከአቅም በላይ የሆነ ሃይል ካላጋጠመ በስተቀር ወዲያውኑ ለትራፊክ ፖሊስ እና ኢንሹራንስ ኩባንያው ሪፖርት ማድረግና ይሄው መደረጉን ለዋናው መስሪያ ቤት ማሳወቅ፣
2. የትራፊክ ፖሊስና የኢንሹራንስ መርማሪ አደጋውን ለመመርመር በቦታው ሲገኙ ከኮርፖሬሽኑ የመሳሪያዎች የቴክኒክ ባለሙያ ኢንስፔክተር ሴፍቲ ቴክኒሽያን እንዲያገኙ ማድረግ፣
3. ስለ አደጋው አጥጋቢ መረጃ ለማጠናቀር እንዲመች አደጋው የደረሰበትን ተሽከርካሪ በአራት አቅጣጫ ፎቶ ግራፍ አንስቶ መያዝና ይህንኑ ከሪፖርት ጋር ማያያዝ፣
4. የትራፊክ ፖሊስ ኘላን እንዲያነሳ በማድረግ ለቀጣይ ክትትል አድራሻውንና ስሙን መዝግቦ መያዝ፣
5. በአደጋው ክስተት ወቅት በቦታው የነበሩ ሰዎች ካሉ የምስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ ለማድረግ አድራሻቸውን መዝግቦ መያዝ፣
6. በኢንሹራንስ ኩባንያና በትራፊክ ፖሊስ ሊፈጸሙ የሚገቡ ሁሉ የተጠናቀቁ ከሆነ መሳሪያው በመንገድ ላይ ከሆነ ለተጨማሪ አደጋ ምክንያት እንዳይሆን ከቦታው የሚነሳበትን ወይም እስኪነሳ ተገቢው ጥበቃ የሚደረግበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
7. ከህግ አስፈፃሚ አካላት ሊቀርብ የሚገባውን ሪፖርት ተከታትሎ በመቀበል ተገቢውን የአደጋ ሪፖርት አሟልቶ ማስተላለፍ፣
8. ከሚመለከታቸው ጋር ውይይት በማድረግ ጉዳት የደረሰበት ተሽከርካሪ እንደሁኔታው በአፋጣኝ ተጠግኖ ወደ ሥራ ሊገባ የሚችልበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይገባል፡፡

# ክፍል ሰባት

## የዘርፈ ብዙ ጉዳዮች

### 101.ኤች አይ ቪ/ኤድስ ቫይረስ በደማቸው ውስጥ ያለባቸውና የኤድስ ህሙማን የሆኑ ሠራተኞች

1. ኤች አይ ቪ/ኤድስን መከላከልና መቆጣጠር የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችን ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ፣
2. በበሽታው የተጠቁ ሠራተኞች እንክብካቤና ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ፣
3. ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር ተያይዞ የሚፈጠረውን አሉታዊ አመለካከትና መድልዎ ማስወገድ፣
4. ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ያለባቸው ሰራተኞች፣ የኤድስ ህሙማን ሠራተኞችና የተጐጅ ቤተሰቦችን ሰብአዊ መብት፣ ክብርና ጥቅም ማስጠበቅ፣
5. ኤች አይ ቪ/ኤድስ የሥራ ቦታ ችግር መሆኑን የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች እንዲያውቁት ማድረግ፣
6. ለሰራተኞች ስለ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ተከታታይና ወቅታዊ ትምህርትና ስልጠና በመስጠት በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የደም ምርመራ እንዲያደርጉና ራሳቸውን አውቀውና ጠብቀው በጥንቃቄ እንዲኖሩ ማስቻል፣
7. የጤና ሁኔታቸው ለተመደቡበት ሥራና የስራ ቦታ ብቁ የሚያደርጋቸው እስከሆነ ድረስ በተመደቡበት ሥራ የመቆየት መብታቸው የተጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ፣
8. በኮርፖሬሽኑ ክሊኒክ እና ከኮርፖሬሽኑ ጋር ስምምነት ካለቸው ተቋማት ጋር በመዋዋል የህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
9. ኤች አይ ቪ በደማቸው ውስጥ ያለባቸውና የኤድስ ህሙማን የሆኑ ሠራተኞች መስራት እስከቻሉ ድረስ ከጤና ሁኔታቸው ጋር የተጣጣመ ምቹ የስራ ሁኔታ፣ እንክብካቤና ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ፣
10. ኤች አይ ቪ በደማቸው ውስጥ መኖሩን እና የኤድስ ታማሚ መሆናቸውን ይፋ ያደረጉ ሰራተኞች በፀረ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ኘሮግራሞች ላይ በመሳተፍ የቫይረሱን ስርጭት ለመቀነስ የሚያደርጉትን ጥረትና ተሳትፎ መደገፍና ማበረታታት፣

11. ኤች አይ ቪ በደሙ ውስጥ ያለበት ማንኛውም ሠራተኛ ሆን ብሎ ቫይረሱን ወደ ሌሎች የማስተላለፍ ምግባር ከፈፀመ ጉዳዩን አስመልክቶ በሀገሪቱ በወጣው የህግ አግባብ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፣
12. ማንኛውም ሠራተኛ ወይም አመልካች ተቀጣሪ ሠራተኛ ያለፈቃዱ የኤች አይ ቪ ምርመራ እንዲያደርግ አይገደደም፣
13. የማንኛውም ሠራተኛ ወይም የሥራ አመልካች የጤና ምርመራ ውጤት በሚስጥር መጠበቅ አለበት፣
14. ማንኛውም ኤች አይ ቪ በደሙ ውስጥ ያለበት ወይም የኤድስ ህመምተኛ ሠራተኛ እየሰራበት ያለው ሥራ ለጤናው አስጊና ጠንቀኛ መሆኑ ከታወቀ ተመጣጣኝ በሆነ የሥራ መደብ ላይ ተዛውሮ ለጤናው በሚመች አካባቢ እንዲሰራ ይደረጋል፣
15. ማንኛውም ሰራተኛ ቫይረሱ በደሙ ውስጥ በመኖሩ ምክንያት በስራ ቅጥርና ምልመላ ስርዓት፣በደመወዝ ጭማሪና በሌሎች ጥቅማጥቅሞች፣ በሥራ ምደባ፣ በዕድገትና በዝውውር፣ በትምህርትና በስልጠና እድል፣ በህግ ወይም በህብረት ስምምነቶች ወይም በሥራ ደንቦች ለሰራተኞች የተሰጡ መብቶች ላይ እና በሌሎች የሥራ ሁኔታዎች ልዩነት አይደረግም፣

## 102.ስለ ሴት ሠራተኞች ደህንነትና ጤና

1. ሴቶች በተለይም በእርግዝና ወቅት እንዲሁም በሚያጠቡበት ጊዜ የስነ ተዋልዶ ጤና እና ደህንነት ችግር ከሚያስከትሉና የፅንስንና የሕፃንን ተፈጥሯዊ ዕድገትና ሁኔታ ሊያዛቡ ከሚችሉ የስራ ሁኔታዎች ይጠበቃሉ።
2. በኢፌዲሪ ህገ-መንግስት፣ ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም ዐቀፍ ስምምነቶችና በሌሎች የሐገሪቱ ሕጎች ስለ ሴቶች የተደነገጉ መብቶች ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ይከበራሉ።
3. በኮርፖሬሽኑ በተለያዩ የስራ ቦታዎች የተመደቡ ሴት ሰራተኞች በስራ ላይ ሲሰማሩ ከተለያዩ አደጋዎች፣ ጉዳቶችና በስራ ምክንያት ከሚከሰቱ በሽታዎች እንዲሁም ከባድ ከሆኑና ከፍተኛ ጉልበት ከሚጠይቁና አካላዊ ጉዳትና ህመም ሊያስከትሉ ከሚችሉ የስራ ሁኔታዎች መገደብና መጠበቅ አለባቸው።

## 103.ስለ ወጣቶችና አካል ጉዳተኛ ሠራተኞች ደህንነትና ጤና

ኮርፖሬሽኑ ካለው የሥራ ባህርይ አንጻር ለወጣቶችና አካል ጉዳተኛ ሠራተኞች አስጊና ፈታኝ ሥራዎች የሚበዙበት በመሆኑ ልዩ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

ስለዚህ

1. ተፈጥሯዊ የሰውነት አቋማቸውንና ዕድሚያቸውን ያገናዘበ ሥራ እንዲሰሩ ማድረግ፣
2. ቅርብ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣
3. ወጣቶችና አካል ጉዳተኞች ሀገሪቱ ባወጣቻቸው ሕጎችና በተቀበለቻቸው ዓለም ዓቀፍ ስምምነቶች የተጎናፀፏቸው መብቶች ይከበሩላቸዋል፡፡

# ክፍል ስምንት

# ማጠቃለያ

## 104.የክትትል፣የድጋፍና ግምገማ ሥርዓት

1. የማኑዋሉን ይዘት ተረድቶ ተግባራዊ ለማድረግ የተያዘ ዕቅድና ለዕቅድ ማስፈፀሚያ የተመደበ ሀብት በአጠቃላይ ለጉዳዩ የተሰጠው ትኩረትና የቅድመ ዝግጅት እንቅስቃሴ ላይ ተንተርሶ የሚከናወን ይሆናል፡፡
2. የማኑዋሉን አፈፃፀም ደረጃ በደረጃ ለመከታተልና ለመገምገም ወቅታዊ የሪፖርት ልውውጥ አሠራርን ለማጠናከርና ከተለያዩ የስራ ክፍሎች ብሎም ከባለድርሻ አካላት የሚሰጡ ግብረ መልሶችን በግብአትነት ለመጠቀም የሚያስችል ቋሚ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡
3. የክትትል፣ ድጋፍና ግምገማ ሥርዓቱ የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ መረጃ ስርዓት መዘርጋትን፣ በመረጃ በመመስረት የማኑዋሉን የአካባቢ፣ የሥራ ቦታ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ አገልግሎቶችን፣ የሥራ ላይ አደጋዎችን እና የጤና ችግሮችን እንዲሁም የንብረት ውድመት፣ የጊዜና የገንዘብ ብክነትን በመከላከል እና በመቀነስ ረገድ እንዲሁም የሥራ ሁኔታዎችን በማሻሻል ለምርታማነት ማደግ ያበረከቱትን አስተዋጽኦ በመገምገም ፋይዳቸውን ከሚያስከትሉት ወጪ ጋር የሚያነጻጽር ጥናት ይካሄዳል፡፡
4. በክትትል ድጋፍና ግምገማው ውጤት መሠረት ማኑዋሉን ለመከለስና የፕሮግራም አፈጻጸሞችን ለማሻሻል የሚያስችሉ መረጃዎች፣ ሪፖርቶች፣ ጥናቶች እና ምክረ ሀሳቦች በየጊዜው ለኮርፖሬሽኑና ለሚመለከታቸው አካላት እንዲቀርቡ ይደረጋል፡፡
5. ማኑዋሉ በሥራ ላይ ስለመዋሉ የሥራ አካባቢ፣ የሥራ አካባቢ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ አገልግሎት ሥርዓትን ለማሻሻል የሚወሰዱ እርምጃዎችን ውጤታማነት የሚመለከታቸውን የተለያዩ የስራ ክፍሎች እና ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ የማኑዋሉ አፈጻጸም ይገመገማል፡፡
6. ከኮርፖሬሽኑ እስከ ፕሮጀክቶች ባሉ የስራ ክፍሎች በተዘረጋው የክትትልና ግምገማ ስርዓት የአፈጻጸም ማኑዋሉን አፈፃፀም ከስራ ላይ አደጋ መረጃዎች፣ በሥራ ምክንያት ከሚመጡ በሽታዎች፣ ከህክምና፣ ከማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ፣ ከመሳሪያዎችና ከንብረት

ውድመት እንዲሁም ከአካባቢ ስነምህዳር ደህንነት መዛባት ወ.ዘ.ተ… ጋር ተያይዞ የደረሱ አደጋና ጉዳቶችን፣ ችግሮችን እና የሚሰጡ ግብረ መልሶችን ያካተቱ ተጨባጭ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ የመፍትሄ እርምጃ ይወሰዳል::

7. የታቀዱ ሥራዎች በተቀመጣላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት መፈፀማቸውንና እየተፈጸሙ መሆኑን፣ ክለሳ የሚያስፈልጋቸው ዕቅድና ተግባራት መኖራቸውን፣ የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ ለማሳደግና አጠናክሮ ለመቀጠል እየተሰሩ ያሉ ተግባራትን አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ይደረግባቸዋል፡፡
8. በዕቅድም ሆነ ከእቅድ ውጭ በተከናወኑ ተግባራት አፈጻጸም የተገኙ የአጭርና የረጅም ጊዜ ውጤቶችን በመገምገም ተገቢ ግብረ መልስ የመስጠት ሥራ ይከናወናል፡፡
9. የእነዚህን ተግባራት አፈጻጸምና የማኑዋሉን ግቦች እውን ለማድረግ እንዲቻል ልዩ ልዩ የመከታተያ፣ የመቆጣጠሪያና የመገምገሚያ ቅጾችና ፎርሞች ተዘጋጅተው ሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡

## 105. የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ስርዓት

1. ማንኛውም የኮርፖሬሽኑ ሠራተኛ የዚህን ማኑዋል አፈፃፀም በተመለከተ ቅሬታ ከተሰማው በየደረጃው ላለ የንዑስ ኮሚቴ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡ በንዑስ ኮሚቴው ውሳኔ ካልረካ ቅሬታውን ለአብይ ኮሚቴ በጽሑፍ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
2. አብይ ኮሚቴ ቅሬታው በቀረበለት 5 የሥራ ቀናት ውስጥ ለኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡
3. የኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ከአብይ ኮሚቴ የቀርበለትን የውሳኔ ሃሳብ በሶስት የሥራ ቀናት ውስጥ በመመልከት ውሳኔውን ሙሉ በሙሉ ሊያፀናው፤ በከፊል ሊያሻሽለው ወይም ሙሉ በሙሉ ሊሽረው ይችላል ይህም የመጨረሻ ይሆናል፡፡
4. ከዋና ሥራ አስፈጻሚው ውሳኔ በኂላ ቅር የተሰኘ አካል ጉዳዩን ወደ መደበኛ ፍ/ቤት የመውሰድ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

## 106. ማኑዋሉን የመተግበር ኃላፊነት

ይህን ማኑዋል ተግባራዊ የማድረግ ኃላፊነት በዋናነት በየዘርፉ የተመደቡ የአካባቢ፣ የሥራ አካባቢ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ የሥራ ክፍሎች ቢሆኑም በየደረጃው ያሉ የሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች በማኑዋሉ መሠረት የመፈጸምና የማስፈጸም ግዴታ አለባቸው፡፡

## 107.ማኑዋሉ የሚሻሻልበት ሁኔታ

ይህ ማኑዋል በኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሲፈቀድ በማናቸውም ሁኔታ ሊሻሻል ይችላል፡፡

## 108. ማኑዋሉ ሥራ ላይ የሚውልበት ጊዜ

ይህ ማኑዋል በዋና ሥራ አስፈጻሚ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ዮናስ አያሌው (ኢንጂነር)
የኢትዮጵያ ኮንስራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን
ዋና ሥራ አስፈጻሚ